# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

### የሕፃናት ስነፅሁፍ ሂሳዊ ትንተና እና የህፃናት አንባቢያን አስተያየት

በ

አለምሰገድ እሸቱ

በሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ሰኔ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

## የሕፃናት ስነፅሁፍ ሂሳዊ ትንተና እና የህፃናት አንባቢያን አስተያየት

በ

አለምሰገድ እሸቱ

አማካሪ

ዘሪሁን አስፋው

በሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

ሰኔ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የድህረ ምረቃ መርሀግብር

# የሕፃናት ስነፅሁፍ ሂሳዊ ትንተና እና የህፃናት አንባቢያን አስተያየት

በ

አለምሰገድ እሸቱ

ሰኔ 2003 ዓ.ም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ዘሪሁን ካሳሁን

አማካሪ

ፊርማ

ቴዎድሮስ ገብሬ

ፈታኝ

ፊርማ

# ምስጋና

ቀዳሚው የእግዚአብሔር ነው፡፡ በመቀጠል ርዕሱን ከማስተካከል አንስቶ የጥናቱን አቅጣጫ በመወሰንና ፅሁፉን በማረም እንዲሁም የግል መጻሐፋቸውን በማዋስ የተሟላ እገዛ ላደረጉልኝ መምህሬና አማካሪዬ ለአቶ ዘሪሁን አስፋው ስለሁሉም ነገር እግዚአብሔር ይስጥልኝ፡፡

የቦሌ ህብረተሰብ፣ የአሳይ፣ የነፃነት ብርሃንና የአየር አምባ የህዝብ ትምህርት ቤቶች አስተዳደርና መምህራን እንዲሁም የ2003 ዓ.ም የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ለጥናቴ የሚሆን መረጃ ለመሰብሰብ በመጣሁ ጊዜ ላደረጋችሁልኝ ቅን ትብብር ሁሉ በእጅጉ አመሰግናለሁ፡፡

መፃህፍት በማፈላለግ ላገዝከኝ የክፍል ጓደኛዬ ሙሉቀን የአንተን ድጋፍ ማግኘቴ በርካታ ክፍተቶቼን ሞልቶልኛልና የእውነት በሆነ ቃል አመሰግንሀለሁ፡፡ ውዷ ባለቤቴ ወ/ሮ ትዕግስት ደስታ ነዋይ "አይዞህ" ባይነትሽ ጉልበት ሆኖኛል፣ የጥናት ፅሁፌን በትዕግስት በማንበብ የሰጠሽኝ አስተያየቶች ያረምኻቸው የፊደል ስህተቶች የጥናት ጽሑፌን የተሻለ ለማድረግ ስለረዳኝ ከልቤ አመሰግንሻለሁ፡፡ ልጆቼ አቤል፣ ማርያማዊትና ዮሐንስ ለእናንተ ከነበረው ጊዜ ላይ የጥናት ፅሁፉን እንድሰራ ስላዋሳችሁኝ ጊዜ አመሰግናለሁ፤ ብድር መላሽ ያድርገኝ፡፡ ሠላማዊት ንጉሴ ይህንን ጥናት በኮምፒውተር በመፃፍ ያረግሽልኝ አስተዋፅኦ ባለውለታዬ አድርጎሻል፡፡ ጓደኞቼ ደነቁ እና ሳምሶን የእናንተንም ድጋፎች አልረሳቸውም፡፡

# ርዕስ ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ....... i
አጠቃሎ ....... ii
ርዕስ ማውጫ ....... iii
1. መግቢያ ....... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ....... 1
1.2 የጥናቱ አላማ ....... 3
1.3 የምርምር ጥያቄዎች ....... 3
1.4 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....... 3
1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ ....... 4
1.6 የጥናቱ ወሰን ....... 4
1.7 የናሙና አመራረጥ ....... 5
1.8 ያጋጠሙ ችግሮች ....... 8
1.9 የጥናቱ ዘዴ ....... 8
1.10 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ....... 9
2. ክለሳ ድርሳናት ....... 10
2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ....... 10
2.2 የንድፈ ሀሳብ መሰረቶች ....... 14
2.2.1 የህፃንነት ብያኔ ....... 15
2.2.2 የህፃናት ስነፅሁፍ ብያኔ ....... 18
2.2.3 የህፃናት መፃህፍት ዓይነቶች ....... 19
2.2.4 ባህላዊ ስነፅሁፍ ....... 19
2.2.4.1 ፌብል ....... 20
2.2.4.2 ተረት ....... 20
2.2.4.3 ሚት ....... 21

2.2.5 ግጥሞች ....................................................................................21
2.2.6 ኢ.ልብወለድ ..............................................................................22
2.2.7 ልብወለድ ..................................................................................22
2.2.7.1 ዘመናዊ ፋንታሲ ..................................................................22
2.2.7.2 ወቅታዊ እውነታዊ ልብወለድ ..................................................24
2.3 የህፃናት መፃህፍት መለኪያዎች.........................................................25
2.3.1 የህፃናት ልብወለድ አላባውያን...................................................25
2.3.1.1 ትልም ................................................................................26
2.3.1.2 ገፀባህርያት...........................................................................26
2.3.1.3 መቼት ................................................................................27
2.3.1.4 ጭብጥ ................................................................................27
2.3.2 የቃላት አጠቃቀም ....................................................................28
2.4 የአንባቢያን ምላሽ ንድፈ ሀሣብ ..........................................................39
2.4.1 የምላሽ አይነቶች.......................................................................30
2.4.2 የህፃናት አንባቢያን ምላሽ ..........................................................31
3. የተመረጡ መፃህፍት ትንተና...........................................................34
3.1 ብልሁ ጠቋሪት ..............................................................................34
3.2 ቱሲ እና ቼኪ ..............................................................................36
3.3 የአንቺነሽ ተስፋ ..........................................................................38
3.4 የአሰለፈች ሎሚዎች ......................................................................40
3.5 ካሳ ...............................................................................................42
3.6 ሊንቻ እና ቢንቻ ..........................................................................45
4. ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎችና ምላሾቻቸው ...........................................47
4.1. የመላሾች ግላዊ መረጃ ....................................................................47
4.2 በመፃህፍቱ ላይ የተሰጡ ምላሾች......................................................49
4.3. የመላሾች የንባብ ልምድና ፍላጎት ...................................................60
4.4 ከቡድን ውይይት የተገኙ ምላሾች......................................................61
4.4.1 ታሪኩንና ገፀባህሪያቱን በድጋሚ መናገር ጭብጡን መረዳት .........63
4.4.2 የቋንቋ አጠቃቀምን የሚመለከቱ አስተያየቶች ...............................65

4.4.3 ታሪኮቹን ከሌሎች ሁነቶች ጋር ማያያዝ ........................................66
4.4.4 የአንባቢያንን ስሜት የሚያንፃባርቁ መልሶች ................................67
5. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች ......................................................70
5.1 ማጠቃለያ .............................................................................70
5.2 የመፍትሄ ሃሳቦች ...................................................................71
የተጠቀሱ ምንጮች ....................................................................73
አባሪዎች

# አጠቃሎ

“የህፃናት ስነጽሑፍ ሂሳዊ ትንተና እና የህፃናት አንባብያን አስተያየት” በሚል ርዕስ የተደረገው ይህ ጥናት ከ1990 ዓ.ም ወዲህ በታተሙና በተመረጡ ስድስት የህፃናት መፃሕፍት ላይ ሂሳዊ ትንተናን አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በነዚሁ መፃሕፍት ላይ የህፃናትን አስተያየት በመሰብሰብ ተንትኗል፡፡ በመፃሕፍቱ ላይ የተደረገው ሂሳዊ ትንተና ያተኮረው በህፃናት ልቦለድ መፃህፍት አላባውያን ላይ ነው፡፡ በተለይም በመፃሕፍቱ ትልም፣ገፀባህሪያት አገላለፅ፣መቼትና ጭብጥ፣ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡ የመፃሕፍቱ የቃላት አጠቃቀምም ታይቷል፡፡ በተመረጡት የህፃናት መፃህፍት ላይ የአንባቢያኑን አስተያየት ማሰባሰብን እና መተንተንን ዋነኛ አላማው አድርጎ የተነሳው ይህ ጥናት በኢትዮጵያ የሕፃናት መፃሕፍት ታሪክን ለመዳሰስ ቀደም ሲል የተሰሩ ተዛማጅ ሥራዎችን ቃኝቷል፡፡

በሌላ በኩል ስድስቱ የህፃናት መፃሕፍት ከአራት የሕዝብ የትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ 180 ተማሪዎች ተነበዋል፡፡አንዱ መፅሐፍ ለ30 ተማሪዎች የተነበበ ሲሆን የተማሪዎቹን አስተያየት ለመሰብሰብ የሚያስችል መጠይቅ ተበትኖ ተማሪዎቹ በተነበበላቸው መፅሐፍ ላይ ተመስርተው ለጥያቄዎቹ ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡የተተኳሪ ቡድን ውይይት በማድረግም አስተያየት ተሰብስቧል፤ከመፃሕፍቱ መካከል በተዘውታሪ ንግግር ውስጥ ያልተለመዱ እንግዳ ቃላት ከተጠቀመ አንድ መፅሐፍ ላይ ለተውጣጡ ቃላት ትርጉም እንዲፈልጉ መፅሐፉ ለተነበበላቸው ተማሪዎች ፈተና ተሰጥቷል፡፡ የተገኙትም መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡

በሂሳዊ ትንተናው ወቅት በአንዳንድ መፃሕፍት ላይ ትልሙን በጠንካራ ታሪካዊ ትስስር አለማሳደግ፣ ገፀባህሪያትን እና መቼትን በአግባቡ አለመግለፅ እንዲሁም ጭብጥን ለማስተላለፍ በሚደረግ ገለፃ ተፈላጊ ያልሆኑ መልእክቶች በታሪኮቹ ውስጥ እንዳይገቡ ጥንቃቄ ያለማድረግ ችግሮች ታይተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም እንግዳ (ተዘውታሪ ያልሆኑ) ቃላትን በስፋት የተጠቀመ መፅሐፍ መኖሩም ተመልክቷል፡፡በተማሪዎቹ የተሰጡት አስተያየቶችም በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎቹ የሚያሳዝንም ሆነ የሚያዝናና ታሪክ በሚገባቸው ቋንቋ ከቀረበ ማድመጥ እንደሚፈልጉ፣ በሀገር ውስጥ ደራስያን በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ መፃህፍት ማንበባቸውን የገለጹ ሲሆን በተነበቡላቸው መፃህፍት ላይም አሉ ያሏቸውን ችግሮች ገልፀዋል፡፡በመጨረሻም ከተማሪዎቹ አስተያየትና ከሂሳዊ ትንተናው የተገኙ ውጤቶችን በጥናቱ ማጠቃለያ በማመልከት የመፍትሄ ሃሳቦች ተሰጥተዋል፡፡

# 1. መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ለህፃናት ሥነ-ምግባር ለማስተማር፣ እውቀትን ለማስተላለፍና ታሪክን ለመንገር የሥነ-ፅሑፍ አስተዋፅኦ የጎላ ነው፡፡ ይህ የዕውቀት፣ የመልእክትና የመረጃ ማስተላለፊያ መሣሪያ አገልግሎት ላይ ከዋለ ረጅም ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ እንደ (Grenby 2003:2) ገለፃ ከሮማውያን ዘመን ጀምሮ ወይም ከዚህ ጊዜ ቀደም ብሎ ለህፃናት ተብለው የሚፃፉ ምንባቦች ነበሩ፡፡ ከ15ኛ ክፍለ ዘመን አንስቶም በአውሮፓ የቃል ተረቶች ታትመዋል፡፡

በኢትዮጵያም ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንስቶ ለህፃናት ተብለው የሚፃፉ መፃህፍት መታተም ጀምረዋል፡፡ የመጀመሪያው መፅሐፍ በ1916 ዓ.ም የታተመው "የፍቅር መላዕክት ለኢትዮጵያ ልጆች" በሚል ርዕስ በቀለ ኃብተ ሚካኤል በሚባሉ ደረሲ አማካኝነት ነበር፡፡ ከዚህም በማስከተል መርስኤ ኀዘን ወልደቂርቆስ "ትምህርተ ህፃናት" በሚል ርዕስ በ1917 ዓ.ም ሁለተኛውን መፅሐፍ አሳትመዋል፡፡ በኢጣሊያ ወረራና በሌሎች የማይታወቁ ምክንያቶች ለአስራ ሰባት ዓመታት የህፃናት መፃህፍት ሳይታተሙ ቆይተው ጣሊያን ከሀገር በወጣ በዓመቱ በ1934 ዓ.ም ከበደ ሚካኤል ታሪክና ምሳሌ በሚል ርዕስ ሦስት የተለያዩ መፃህፍትን ለሦስተኛ፣ አራተኛና አምስተኛ ክፍሎች ማስተማሪያ ይሆኑ ዘንድ አሳትመዋል፡፡ መፃህፍቱ ስለሀገር፣ ስለባንዲራ፣ ስለዜግነት የሚናገር ተመሳሳይ መግቢያ ያላቸው ናቸው፡፡ መፃህፍቱ ተረቶችን፣ ትረካዎችንና ግጥሞችን የተለያዩ ቁምነገሮችን ለማስተማር በሚያመች መልኩ አካተው ይዘዋል፡፡ በ1938 ዓ.ም "ስለ እንስሳት አገልግሎት ለህፃናት በረከት" በሚል ርዕስ የእንስሳትን አቤቱታ በግጥም ለአንባቢያን ያቀረበው የያሬድ ገብረሚካኤል ሥራም በዚህ መልክ የታተመ ሌላ ተመሣሣይ ሥራ ስለሌለ በሀገሪቱ የህፃናት ስነፅሑፍ ታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ ነው (Dereje 1994፣ 10-26)::

ከ1940ዎቹ እስከ 1960ዎቹ የህፃናት መፅሐፍት ህትመት በፍጥነት ያደገበት ወቅት ሲሆን በተለይም በትርጉም ረገድ "የኤዞፕ ተረቶች" በ1947 ዓ.ም በከበደ መንገሻ ፣ በ1950 "አንድ ሺ ከአንድ ሌሊት" በለማ በላይነህ፣ በ1952 ዓ.ም "አፍንጮ" በለማ ፈይሳ ተተርጉመው ታትመዋል፡፡ በአጠቃላይ ከ1960 እስከ 1984 ዓ.ም 72 የህፃናት መፃህፍት በኢትዮጵያውያን ደራሲያን ተፅፈዋል፡፡ 66 የሚሆኑ ደግሞ ከተለያዩ ቋንቋዎች ወደ አማርኛ ተተርጉመዋል፡፡

በ1970ዎቹ የህፃናት መፃህፍት ህትመት ቀዝቀዝ ያለ ቢሆንም በዚህ አስርት ግን የተለየ ነገር ተከስቷል በ1974 ዓ.ም የተቋቋመው የኩራዝ አሳታሚ በ1978 ዓ.ም የህፃናት መፃህፍት ህትመት ክፍል አቋቁሟል፡፡ እስከ 1983 ዓ.ም ድረስም ይህ ክፍል 19 የህፃናት መፃህፍትን አሳትሟል፡፡ በ1978 ዓ.ም የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ኤጀንሲ በህፃናት ልቦለድ መፃህፍት ላይ ሀገር አቀፍ አውደጥናት አካሂዶ የጥናት ወረቀቶች ቀርበዋል፡፡ በዚህ አውደ ጥናት ላይም በህፃናት ሥነፅሁፍ ዙሪያ ተቀባይነት ያላቸውን መሰረተ ሀሳቦች የሚያብራሩ፣ በህፃናት መፃህፍት ላይ የሥዕል ሚናን የሚጠቁሙና ሌሎችም ለመወያያ የሚሆኑ ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበዋል (ዝኒ ከመሁ 1994፣ 33-9)፡፡

ከ1978 ዓ.ም ወዲህ ይህንን የሥነፅሁፍ ዓይነት ይበልጥ የሚያስተዋውቁ እና ደራሲያኑን የሚያበረታቱ ሁኔታዎች እያደጉ በመምጣታቸው የህትመት ቁጥሩ እድገት አሳይቷል፡፡ ከ1978 እስከ 1995 ዓ.ም በ17 ዓመታት ውስጥ ብቻ 74 የህፃናት መፃህፍት መታተማቸው የተመዘገበ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 41 መፃህፍት የተፃፉት ከ1991 እስከ 1995 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ነው፡፡ ከ1978 እስከ 1990 ዓ.ም ድረስ ባሉት 12 ዓመታት ከታተሙት 33 መፃህፍት ጋር ሲነፃፀር በአምስት አመታት የታተሙት በስምንት መፃህፍት ብልጫ አላቸው (መሰሉ 1996፣ 34)፡፡ በመሆኑም በዚህ የሥነፅሁፍ ዓይነት የሚታተሙት የመፃህፍት ቁጥር እድገት እያሳየ መጥቷል ለማለት ይቻላል፡፡

በየዘመኑ ለህፃናት ተብለው የታተሙት እነዚህ መፃህፍት ይብዛም ይነስም በህፃናቱ አስተዳደግና ሰብእና ላይ የራሳቸውን አስተዋፅዖ ሳያደርጉ እንደማይቀሩ ይገመታል፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን ከግምት ያልዘለለ መላ ምት በጥናት ላይ በተመሰረተ የእውነት መሠረት ላይ እንዲቆም ለማድረግ ምርምሮችን ማካሄድ ግድ ነው፡፡

በእርግጥ ጥሩ የህፃናት ስነፅሁፍ ይህ ነው ብለን ቁርጥ ያለ ሀሳብና ብያኔ የምንሰጥበት ፈጣንና ቀላል መንገድ የለም (Horning 1997:X)፡፡ ይሁን እንጂ ህፃናት አንባቢያኑን በመጠየቅ እና ምላሻቸውን በመመዝገብ መፃሕፍቱ በሕፃናቱ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ ሕፃናቱም ለመፅሀፍቱ ያላቸውን ፍላጎት በተወሰነ መልኩ ማወቅ ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት ይህ ጥናት የህፃናት አነባቢያኑን አስተያየት በግባትነት ይጠቀማል ሂሳዊ ትንተናም ያደርጋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት አቢይ አላማ በሃገራችን ለህፃናት ተብለው በሚታተሙ መጻህፍት ላይ ህጻናት አንባቢያን ያላቸውን አስተያየት መሰብሰብና የተመረጡትን መጻህፍት ከህጻናት ስነጽሁፍ ዋና ዋና ባህሪያት አንጻር መተንተን ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎችም ይኖሩታል፡፡

- ህጻናት በስነጽሁፎቹ ላይ ያላችውን ፍላጎት ማሳየት፤
- ከህጻናቱ አስተያት በመነሳት መዘውተር ያለባችውን ርእሰ ጉዳዮች መጠቆም፤
- ደራሲያኑ የህጻናቱን አጠቃላይ ፍላጎት ለማነሳሳትና ለማሟላት ቢከተሉት የሚመረጠውን ስልት ማመላከት፤
- በህፃናቱ ስነፅሁፎች ላይ የሚታዩትን ዋና ዋና ጠንካራና ደካማ ጎኖች መግለፅ ናቸው፡፡

## 1.3 የምርምር ጥያቄዎች

በዚህ ጥናት ውስጥ የሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ያገኛሉ፡፡

ሀ. ህፃናቱ ለነሱ ተብለው በሚደረሱ መፃህፍት ላይ ያላቸው አጠቃላይ አስተያየት ምን ይመስላል?

ለ. ለህፃናት ተብለው የሚፃፉት መፃህፍት በህፃናት አንባቢያን ያላቸው ተቀባይነት ምን ይመስላል?

ሐ. ህፃናቱ የሚወዷቸው ርዕሰ ጉዳዮች የትኞቹ ናቸው?

መ. ህፃናቱ በደራሲያኑ ቋንቋ አጠቃቀም ላይ ያላቸው አስተያየት ምን ይመስላል?

## 1.4 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በሀገራችን በህፃናት ስነፅሁፍ መስክ ብዙ መሰራት ያሉባቸው ስራዎች እንዳሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር በነበርኩባቸው ጊዜያት የማስባቸው ነገሮች ነበሩ፡፡ ህፃናቱ በቋንቋ ትምህርት ጊዜ ልቦለድ ታሪኮች ሲነበቡላቸው አብዛኛውን ጊዜ በጥሞና ይከታተላሉ፡፡ ታሪኩንም ለረጅም ጊዜ ሳይረሱት ይቆያሉ፡፡ ይሁን እንጂ መፃህፍት እንደልብ ስለማይገኙ በህፃናቱ ፍላጎት ልክ ታሪኩን ማንበብ ቢዛም ላይ ተመስርቶ የመልመጃ ጥያቄዎችን መስጠት የሚቻል አልነበረም፡፡ አንዳንዶቹን መፃህፍትም የመስማት ፍላጎታቸው ውስን ነበር፡፡

ዛሬ በአንፃራዊነት የህፃናት መፃህፍት በብዛት ገበያ ላይ ይታያሉ፤ ነገር ግን ህፃናቱ የተገዙት መጻህፍት ሁሉ እንዲነበቡላቸው እንደማይፈልጉ በራሴ ልጆችና ከሌሎች ወላጆች

ጋር ባደረኩት ውይይት ተረድቻለሁ፡፡ ስለዚህ ህፃናት የሚወዱትን የህፃናት መፅሐፍ አይነት ለማወቅና ህፃናቱ በተነበቡላቸው ወይም በአነበቧቸው መፃህፍት ላይ የሚሰጡትን አጠቃላይ አስተያየት ለመስማት ፍላጎት አደረብኝ፡፡ ይህ ሁኔታ በመስኩ የተሰሩት ጥናቶች ጥቂት መሆናቸውን ከማወቄ ጋር ተዳምሮ በዚህ መስክ ጥናቱን ለማድረግ አስወሰነኝ፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

በሀገራችን በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ መፃህፍት፣ መፅሔቶች፣ ጋዜጦችና ሌሎችም የሚነበቡ ነገሮችን ማሳተምና ማሰራጨት እየተለመደ የመጣ ቢሆንም የአንባቢያን አስተያየትን ማሰባሰብ ግን ብዙ የተተኮረበት ተግባር አይመስለኝም፡፡ ይሁን እንጂ የሚነበበው ነገር የተዘጋጀላቸውን ወገኖች አስተያየት መስማት በተከታታይ የስነፅሁፍ ስራቸውን ለሚያቀርቡም ሆነ ነጠላ ስራ ላበረከቱ ተቋማትና ደራሲያን የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ማንኛውም ፅሁፍ ሲፃፍ በዓላማ ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ የአላማው መሳካት አለመሳካት የሚታወቅበት አንዱ መንገድ ደግሞ አንባቢን ጠይቆ በሚገኝ ምላሽ ነው፡፡ ስለዚህ አንድም የተፃፈው ፅሑፍ መልዕክት ከአንባቢ ዘንድ በወጉ መድረስ አለመድረሱን ለማወቅ አንድም በአንባቢ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ማሻሻያ ለማድረግ አንባቢን መጠየቅና ምላሹን መስማት ጠቃሚ ነው፡፡

በዚህም መሰረት ይህ ጥናት፣

- የህፃናቱን ፍላጎት የሚያሟላ ወደ ዝንባሌያቸው የሚጠጋ ድርሰት ለመፃፍ ይችሉ ዘንድ ለነባር ደራሲያን ብርቱ ጥቅም ይኖረዋል፡፡
- የህፃናት መፃህፍትን በድጋፍ ለሚያሳትሙ በልጆች ጉዳይ ላይ ለሚሰሩ ተቋማት ኢትዮጵያውያን ህፃናት የሚመርጡትን ርእሰ ጉዳይና የአቀራረብ ስልት እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡
- ለአዳዲስ የህፃናት ስነፅሁፍ ደራሲያን የአፃፃፍ አቅጣጫ ይጠቁማል፡፡
- የህፃናትን የንባብ ፍላጎት የሚያጠናክሩ የአፃፃፍ ስልቶችና ይዘትን በተመለከተ ወላጆች ግንዛቤ ሊያገኙበት ይችላሉ፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከ1990 ዓ.ም ወዲህ የታተሙ የህፃናት መፃህፍት ላይ ትኩረት በማድረግ የተሰራ ነው፡፡ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የታተሙት የህፃናት መፃህፍት ቁጥር በአጥኚው ምዝገባ መሰረት 39 የሚደርስ ቢሆንም እንኳ በጥናቱ ውስጥ የተካተቱት ስድስት ብቻ ናቸው፡፡

ምክንያቱም ጥናቱ በፈጠራ ሥራዎች (ልብወለድ) የህፃናት መፃህፍት ላይ በማተኮሩ ነው፡፡ ከውጪ ቋንቋዎች የተተረጎሙና ከነባር ሀገራዊ ተረቶች የተወሰዱ ታሪኮችን የያዙ መፃህፍት አልተካተቱም፡፡ በሌላ በኩል በመፃህፍቱ ላይ ለመሰብሰብ የታሰበውን አስተያየት እንዲሰጡ የተመረጡት የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች በመሆናቸው ለነሱ የሚመጥኑ ድርሰቶች ለመፈለግ በተደረገው ጥረት ሌሎች መፃህፍት እንዳይካተቱ ሆነዋል፡፡ በመጨረሻም አንድ ዓይነት ታሪክ ያላቸውን ከሞላ ጎደል ለህፃናቱ ይመጥናሉ ተብለው ከተመረጡት መፃህፍት መካከል ስድስቱ ብቻ በዚህ ጥናት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

## 1.7 የናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በናሙናነት የተመረጡት ከ1990 ዓ.ም ወዲህ የታተሙና በስድስት ደራሲያን የተደረሱ ስድስት መፃሕፍት ናቸው፡፡ ዘመኑ የተወሰነው በእነዚህ አመታት የሚታተሙት የሕፃናት መፃሕፍት ቁጥር በመበረከቱና ጥናቱም በወቅታዊ ሥራዎች ላይ እንዲያተኩር በማስፈለጉ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ የታተሙና በአጥኚው የተመዘገቡ የህፃናት መፃህፍት ቁጥር 39 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 8 የሚሆኑት ከሌላ ቋንቋ የተተረጎሙ፣ 4 ከተለያዩ ክልሎች የተሰበሰቡ ተረቶች ሲሆኑ ሁለቱ ከተተኳሪው የዕድሜ ወሰን ውጪ በመሆናቸው ቀርተዋል፡፡ 12 ደግሞ ከአንድ በላይ የተለያዩ ታሪኮችን በአንድ ላይ አካተው የያዙ ናቸው፡፡ ከቀሪዎቹ መጻህፍት አንድ ደራሲ ከፃፋቸው ወጥ ሥራዎች ውስጥ አንዱን ብቻ በእጣ በማካተት በስድስቱ መፃህፍት ላይ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ መፃህፍቱ የተመረጡት በሦስት መንገዶች ነው፡፡ የመጀመሪያው ለጥናት የተመረጡት ህፃናት እድሜ ከመፅሀፍቱ ጋር ያለውን ተመጣጣኝነት መሰረት ያደረገ ሲሆን ይህም ከህፃናት ሥነፅሁፍ መስፈርት አንፃር የታየ ነው፡፡ ሁለተኛው የህፃናት መፃህፍቱ መጠን ነው፡፡ በሦስተኛነት ደረጃም የድርሰቶቹን ሁኔታ በመፈተሽ ለመምረጥ ጥረት ተደርጓል፡፡

በአነስተኛ ምእራፎች የተከፋፈሉ የህፃናት መፃህፍት ከ 7-12 አመት ላሉ ህፃናት ሊቀርቡ ይችላሉ (Norton 1999፡68)፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የተካተቱት ተማሪዎች ደግሞ የ5ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ ናቸው፡፡በጥናቱ ውስጥ መረጃ በመስጠት ከተሳተፉት 180 ተማሪዎች መካከል 149 (87.7 በመቶ) የሚሆኑት ተማሪዎች እድሜያቸው ከ 10 እስከ 12 ዓመት መሆኑን ተማሪዎች ከሞሉት መጠይቅ ላይ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም መፃህፍቱ በምዕራፍ የተከፋፈሉ ቢሆኑ ይመረጣ ፡፡ ምንም እንኳን ደራሲያኑ በመፅሀፍቱ ላይ የእድሜ ወሰን ባያስቀምጡም በዚህ እድሜ ላሉት ህፃናት ይመጥናሉ የተባሉት እነዚህ

መፃህፍት የተመረጡበት አንዱ መንገድ ይህ ነው፡፡በሌላ በኩል የተመረጡትን መፃህፍት የቃላትና የገፅ ብዛት ተቀራራቢነት ከግምት ውስጥ ለማስገባት ተሞክሯል፡፡ ስድስቱም መፃህፍት ከ 23 እስከ 37 የገፅ ብዛት ያላቸው ናቸው፡፡ ለጥናት በተመረጠው ዘመን ከተደረሱት የህፃናት መፃህፍት መካከል አንድ ታሪክ ያላቸው ወጥ ድርሰቶች የሆኑ የሚሉት በሦስተኛ ደረጃ መፃህፍቱ ከተመረጡባቸው መስፈርቶች ውስጥ ይካተታሉ፡፡ በዚህ መልክ ከተለዩት መፃህፍት ውስጥ ስድስቱ በእጣ ተመርጠዋል፡፡መፃህፍቱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 1 የተመረጡት መፃህፍት፣ ደራሲያንና የህትመት ዘመን

| ተ.ቁ | የመፃህፍት ርዕስ | ደራሲ | የህትመት ዘመን (ዓ.ም) |
|---|---|---|---|
| 1 | ብልሁ ጠቋሪት | አለም እሸቱ | 2001 |
| 2 | ቱሲና ቹኪ | ተስፋዬ ገ/ማርያም | 1997 |
| 3 | የአንቺነሽ ተስፋ | አብርሀም አሰፋ | 1997 |
| 4 | የአስለፈች ሎሚዎች | ታቦር ገ/መድህን | 1995 |
| 5 | ካሳ | ሚካኤል ዳንኤል | 1996 |
| 6 | ሊንቻ እና ቢንቻ | ሺበሺ ለማ | 1995 |

ለዚህ ጥናት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በአራት የህዝብ ት/ቤቶች ውስጥ ከሚማሩ 180 የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች በጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ የተመረጡበት ዋነኛው ምክንያት በዚህ የክፍል ደረጃ ተማሪዎቹ የተሻለ የማንበብ ልምድ እንዲኖራቸው ለማድረግ ከ5-8ኛ ክፍል ተሻሽሎ በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች ላይ የተለያዩ ንባብን የተመለከቱ የስራ ክንውኖች በመጠቀሳቸው እና በጀማሪ ደረጃ ያለውን የንባብ ልምምድ አጠናቀው "ጥሩ የማንበብ ልምዶችን ያዳብራሉ" በሚል ዓላማ የተለያዩ የንባብ ልምምድ ተግባራት የሚከናወኑበት የክፍል ደረጃ በመሆኑ ነው፡፡ የክፍል ደረጃው በዝግታ፣ በፍጥነትና በአሰሳ አንብቦ መረዳት በሚል ርእስ ከተለያዩ የንባብ አይነቶች ጋር የሚተዋወቁበት ነው፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ የንባብ ልምድን ለማዳበር ብቻ ሳይሆን የንባብ ፍላጎታቸውን ለማሳደግ የሚረዱ የልቦለድ፣ የታሪክ፣ የግጥምና የቴያትር ስነፅሁፎችን እንዲያነቡ በመማር ማስተማር ስራ ክንውኑ ላይ በመጠቀሱ ጥናቱን ለማካሄድ የተሻለ የክፍል ደረጃ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከአንዳንድ የልቦለድ አለባውያን ጋር

በመተዋወቅ ደረጃ በዚሁ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ከታችኛዎቹ ይልቅ በተሻለ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ በአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች ውስጥ የተካተቱት ይዘቶች ያመለክታሉ፡፡ የውይይት ስርአትን እንዲያውቁና ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ተከትለው የመስራት ችሎታ እንዲኖራቸው የሚረዱ ትምህርቶች በዚህ የክፍል ደረጃ ይሰጣሉ (የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች 1994 ዓ.ም ፣ 26-9)፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ ለጥናቱ ይመጥናሉ በሚል በዓላማዊ የናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጠዋል፡፡

የአሳይ፣ የአየር አምባ፣ የነፃነት ብርሃንና የቦሌ ህብረተሰብ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ሁሉም ገንዘብ እያስከፈሉ የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ በትምህርት ቤቶች በአብዛኛው በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ወላጆችና አንዳንዴም ዝቅተኛ የሚባል ገቢ ያላቸው ወላጆች ልጆቻቸውን ያስተምራሉ ስለሆነም በነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች አብዛኛውን ህብተሰብ ሊወክሉ ይችላሉ በሚል ትምህርት ቤቶቹ ተመርጠዋል፡፡ በተጨማሪም በህዝብ ባለቤትነት የሚተዳደሩ ከመሆናቸውም በላይ መምህራንን እና ሠራተኞችን የመቅጠርና የማስተዳደር ተመሳሳይ መብት አላቸው፡፡ ስለሆነም በአንፃራዊነት ተቀራራቢ የሆነ ደረጃ ስላላቸው እና አጥኚው በተወሰኑት ትምህርት ቤቶች በማስተማሩ መረጃ ለመሰብሰብ ለአጥኚው ባላቸው የተመቻቸ ሁኔታ ምክንያትም ትምህርት ቤቶቹ ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡

ከየትምህርት ቤቶቹ የተመረጡት ተማሪዎች ብዛት የተወሰነው በሚማሩት የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ቁጥር ነው፡፡ እስከ 100 የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ከሚያስተምሩት ትምህርት ቤቶች ከእያንዳንዳቸው 30 ተማሪዎች በመረጃ ሰጪነት የተመረጡ ሲሆን 140 በላይ ተማሪዎች ከሏቸው ትምህርት ቤቶች ደግሞ 60 ተማሪዎች በእጣ ተመርጠዋል፡፡

በዚህ መሰረት በ2003 ዓ.ም በቦሌ ህብረተሰብ የህዝብ ትምህርት ቤት ካሉ 103 ተማሪዎች ውስጥ 30 ተማሪዎችን፣ በአሳይ የህዝብ ትምህርት ቤት ከሚማሩት 99 የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል 30 ተማሪዎችን፣ በአየር አምባ የህዝብ ትምህርት ቤት ከሚገኙ 163 ተማሪዎች ውስጥ 60 ተማሪዎች፣ በነፃነት ብርሃን የህዝብ ትምህርት ቤት ካሉት 146 ተማሪዎች ውስጥ 60 ተማሪዎችን በመምረጥ በጥናቱ ውስጥ በመረጃ ሰጪነት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የቃላት ትርጉም እውቀታቸውን ለማወቅ ከቦሌ ህብረተሰብ የህዝብ ትምህርት ቤት በእጣ ለተመረጡ 20 ተማሪዎች የቃላት ማዛመድ ፈተና ቀርቦላቸዋል፡፡እነዚህ ተማሪዎች የተመረጡት የተነበበላቸው መፅሀፍ እንግዳ ቃለት ያሉበት

በመሆኑ ነው፡፡ በመረጃ ሰጪነት ከተሳተፉት እና እያንዳንዱ መፅሀፍ ከተነበበላቸው 30 ተማሪዎች ውስጥ 7 ተማሪዎች በአስተማሪዎቻቸው ጠቋሚነት በተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ተሳትፈዋል፡፡አስተማሪዎቹ እንዲመርጡ የተደረገው በውይይቱ ወቅት ንቁ ተሳታፊዎችን ለማግኘት ሲባል ነው፡፡

## 1.8 ያጋጠሙ ችግሮች

እያንዳንዱን የታሪክ መፅሐፍ ለማንበብ ከ25-30 ደቂቃ ወስዷል፡፡ መረጃውን በተሟላ ሁኔታ ለመሰብሰብ ደግሞ ሌላ 30 ደቂቃ አስፈልጓል፡፡ አንድ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ደግሞ 45 ደቂቃ ነው፡፡ በመሆኑም መረጃውን ለመሰብሰብ ሁለት ተከታታይ የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ያስፈልጋሉ፡፡ መምህራኑ ደግሞ በሳምንታዊ ዕቅዳቸው ውስጥ ክፍለጊዜያቱን ትምህርት ሊሰጡበት የመደቡ በመሆኑ በመጀመሪያው ቀን ክፍለ ጊዜያቱን ለመልቀቅ ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ በዚህ ላይ አንድ መምህር ፈቃደኛ ሲሆን በተከታዩ ክፍለ ጊዜ ያሉት መምህራን ፈቃደኛ ያልሆኑባቸው ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ በዚህ ምክንያት መረጃ የመሰብሰብ ስራው ብዙ ማግባባትን የጠየቀና ወደ ትምህርት ቤቶቹም በተደጋጋሚ እንድመላለስ ያደርገ ነበር፡፡ በመጨረሻ ግን ተከታታይ ክፍለ ጊዜያት ያላቸውን መምህራን ከቀጣይ ሳምንት ክፍለ ጊዜያቸው አመቺ የሆነውን ክፍለ ጊዜ ከእቅዳቸው ውጪ እንዲያደርጉልኝ በማግባባት ታሪኩን ለማንበብና መረጃውን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

በሌላ በኩል በሁለት ትምህርት ቤቶች የቡድን ውይይቱን ለማካሔድ የሚያስችል ነፃ ክፍል የማጣት ችግር አጋጥሞኛል፡፡ ሆኖም ለመምህራን ማንበቢያ ተብሎ የተዘጋጀውን ክፍልና ላይብረሪውን በማስፈቀድ በነዚህ ስፍራዎች ውይይቱን ማካሔድ ችያለሁ በሌሎቹ ትምህርት ቤቶች ግን የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ትምህርት ስላልነበራቸው በነዚሁ መማሪያ ክፍሎች ውስጥ መጠቀም ችያለሁ፡፡

## 1.9 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት የገላጭ የምርምር ዘዴን የሚከተል ነው፡፡ በተመረጡት የህፃናት መፃህፍት ላይ የልቦለድ አላባውያንን መሠረት አድርጎ ለሚካሔደው ጥናት ዘዴው ተመርጧል፡፡ ከዚህም ሌላ በተመረጡት የህፃናት መፃህፍት ላይ የህፃናቱን አስተያየት ለመሰብሰብ ለጥናቱ በተመረጡ አንባቢ እንዲነበብላቸው ተደርጎ በአንባቢያን ምላሽ ንድፈ ሀሳብ መሰረት አስተያየታቸው ተሰብስቧል፡፡ ይህም የህፃናት መፃህፍት የሚገመገሙባቸው ሁለት ዘዴዎች

አሉ፡፡ እነሱም በመፃህፍቱ ላይ ህፃናቱ የሚሰጧቸው ምላሾችና በመፃህፍቱ ላይ የሚደረጉ ምሁራዊ ሒሶች ናቸው (Innis 1967: 2) ከሚለው አስተሳሰብ ጋር የሚዛመድ ነው::

## 1.10 የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ለዚህ ጥናት በግባትነት የሚያገለግሉ መረጃዎች ከቤተመፃህፍትና ከመስክ ተሰብስበዋል፡፡ የቤተመፃህፍት ሥራው በዋናነት ያተኮረው ለጥናቱ የሚሆኑ ንድፈ ሀሳቦችን በመፈለግና የተመረጡትን የህፃናት መፃህፍት በመተንተን ላይ ነው፡፡ ለጥናቱ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የታተሙ የህፃናት መፃህፍትን ከሜጋ መፃህፍት መደብርና ከሌሎችም መፃህፍት መሸጫ ሱቆች በማፈላለግና በግዢ በመሰብሰብ መፃህፍቱ ተመርጠው ሂሳዊ ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡

በመስክ ስራው በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ካሉት የአምስተኛ ክፍሎች መካከል ተከታታይ የክፍለ ጊዜያት ድልድል ያላቸው እና ፈቃደኛ የሆኑ ሁለት መምህራን የተገኙበት ክፍል ተመርጧል፡፡ በየትምህርት ቤቱ በዚህ ሁኔታ በተመረጡ ክፍሎች ውስጥ ለሚማሩ ተማሪዎች መፃህፍቱ ተነበዋል፡፡ በማስከተልም በተማሪዎቹ ቁጥር ልክ የተዘጋጀውን እጣ እንዲያወጡ በማድረግ እጣ የወጣላቸው ልጆች መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ እጣው የተዘጋጀው በተማሪዎቹ ቁጥር ልክ ነው፡፡ ከተዘጋጁት የእጣ ወረቀቶች መካከል በ30ዎቹ ላይ "1" ቁጥር በመፃፍና ሌሎቹን ባዶ በማድረግ "1" ቁጥር የተፃፈበት የደረሳቸውን ተማሪዎች መጠይቁን በማስሞላት መረጃው ተሰብስቧል፡፡ መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች መካከል ሰባት ተማሪዎችን በመምረጥ የተተኳሪ የቡድን ውይይቱን ለማካሔድ በሚያስችል ክፍል ውስጥ ከተማሪዎቹ ጋር ውይይቱ ተካሂዷል፡፡ "የአንቺነሽ ተስፋ" የሚል ርዕስ ያለው መፅሐፍ የተነበበላቸው እና መጠይቁን የሞሉት 20 ተማሪዎች ከመፅሀፉ ውስጥ ተውጣጥተው የቀረቡ 15 ቃላትን ከተመሳሳያቸው ጋር እንዲያዛምዱ ፈተና ቀርቦላቸዋል፡፡

የተለያዩ አንባቢዎች በማንበባቸው ምክንያት በተማሪዎች አስተያየት አሰጣጥ ላይ የሚከሰተውን ችግር ለመቀነስ ይረዳ ዘንድም ለሁሉም ተማሪዎች አንድ አንባቢ በመምረጥ መፃሕፍቱ ተነበዋል፡፡ በተነበበላቸው መፅሀፍ መሰረትም ተማሪዎቹ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

ተማሪዎች ለመጠይቁ የሰጡት ምላሽ፣ በተተኳሪ ውይይቱ የሰጡት አስተያየት እና በፈተናው ያገኙት ውጤት በጥናቱ ውስጥ በግባትነት ተካቷል፡፡ መጠይቅ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይትና ፈተና በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት አገልግለዋል፡፡

## 2. ክለሳ ድርሳናት

ለህፃናት የሚፃፉ መፃሀፍት ቁጥርም ሆነ ጥራት እንዲጨምር በመፃሀፍቱ ዙሪያ የሚደረጉ ጥናቶች አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡ የጥናቶቹ መካሄድም በአንድ በኩል ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጠው የሚጠቁም ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የመፃሀፍቱን ድክመት ጥንካሬ ለመገምገም ይረዳል፡፡ በዚህ ክፍል ቀደም ሲል በህፃናት መፃሀፍት ላይ የተካሔዱ ሀገራዊ ጥናቶች ተዳሰዋል፡፡ አንዳንዶቹም ከኔ ጥናት ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት አሳይቻለሁ፡፡ የህፃናት መፃሀፍት አፃፃፍን በተመለከተም አንድ አይነት ቀመር ባይኖርም በተለያዩ ምሁራን የተፃፉ ንድፈ ሀሳቦች በዚህ የጥናቱ ክፍል ውስጥ በማካተት በህፃናት መፃሀፍቱ ዙሪያ ያሉት አጠቃላይ እሳቤዎች ምን እንደሚመስሉ ለማሳየት ጥረት አድርጌአለሁ፡፡

### 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በሀገራችን በተለይ በ1978 ዓ.ም በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ውስጥ የህፃናት መፃሀፍት የህትመት ክፍል ከተቋቋመ በኋላና በዚሁ ዓመት የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት በህፃናት መፃሀፍት ላይ አውደጥናት ካካሄደ በኋላ ለህፃናት ሥነፅሁፍ ትኩረት እንደተሰጠው ጠቋሚ የሆኑ የህፃናት መፃሀፍት በስፋት በገበያ ላይ መታየት ጀምረዋል፡፡ በዛው መጠን በሚወጡትና በወጡት መፃሀፍት ላይ የሚደረጉ ጥናቶች ቁጥርም እየተበራከተ መጥቷል፡፡ በእርግጥ በህፃናት ሥነፅሁፍ ላይ የመጀመሪያው ጥናት በሰይፉ መታፈሪያ "Oral Literature of Ethiopia as Source of Materials for Children's books, Sample Study." በሚል ርዕስ በ1984 የተሰራው ነው (Derje 1994: 9):: ከዛ በማስከተል በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ትምህርት ክፍል ከቀረቡት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፎች መካከል በህፃናት ሥነፅሑፍ ላይ የተሰሩ 10 ጥናታዊ ፅሁፎች ይገኛሉ፡፡

ከነዚህ መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሰው መስፍን መሰለ በ1978 ዓ.ም "የልጆች ሥነፅሑፍ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ያቀረበው ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ ነው፡፡ መስፍን በጥናቱ 37 የሚደርሱ የህፃናት መፃሀፍት የዘረዘረ ሲሆን በኢትዮጵያ የህፃናት ሥነፅሑፍ መሠረት ህዝባዊ ተረቶች መሆናቸውን በጥናቱ ገልጿል፡፡ በ1984 ዓ.ም ፈቃደ ተፈራ "የልጆች

ሥነፅሁፍ ይዘትና ቋንቋ" በሚል ርዕስ ባጠናው የዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ የተለያዩ መፃህፍትን በናሙናነት ወስዶ ይዞታቸውን ተንትኗል የቋንቋ አጠቃቀማቸውንም ቃኝቷል፡፡ በግኝቱ ላይም ይዘታቸው ከህፃናት የማገናዘብ አቅም በላይ የሆኑ እና ረጃጅም አረፍተ ነገር የሚጠቀሙ፣ የሰዋሰው ችግር ያለባቸው መፃህፍት መኖራቸውን ማረጋገጡን ጠቁሟል፡፡ በ1991 ዓ.ም "በቅዳሜ የልጆች ሬዲዮ ፕሮግራም የሚተላለፉ ተረቶች የቅርፅና የይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ፊቃደ ሞላ በሰራው ጥናት ደግሞ በጥናቱ ውጤት መሠረት ከአባቶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ ተረኮችን ለትውልድ ለማስተላለፍ በሬዲዮ የሚተላለፉት ተረቶች ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳላቸው አስተያየት ሰጥቷል፡፡

አብይ በላቸው "በተስፋዬ ሳህሉ ተከታታይ የተረት መፃህፍት የይዘትና የቋንቋ ትንተና" በሚል ርዕስ በ1965፣ በ1966፣ በ1967 እና በ1995 ዓ.ም ልጆች የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች በሚል ርዕስ አቶ ተስፋዬ ሳህሉ ያሳተሟቸውን መፃህፍት ይዘቶች መርምሯል፡፡ በዚህም ለህፃናት ተገቢ አይደሉም ያላቸውን ይዘቶች እና የቋንቋ አጠቃቀም አሳይቷል፡፡ ለልጆች የሚቀርቡ ሥራዎችም የልጆቹን ፍላጎት፣ ችሎታና ባህሪ መሠረት ያደረጉ መሆን እንዳለባቸውም አሳስቧል፡፡ ዳንኤል ነጋሽ ዋጋዬ "የልጆች ልብወለድ አፃፃፍ በታተሙ የሁለት ደራሲያን የልጆች ልብወለዶች ምሳሌነት" በሚል ርዕስ በ1996 ዓ.ም ባጠናው ጥናት ደግሞ በመፃህፍቱ ውስጥ የሚታዩ የጀብዱ፣ የድንቃይና የዳሴ ስሜቶችን በመዘርዘር አሳይቷል፡፡ ከብካብ አስፋው በዚሁ አመት "ሂዩመር፣ አድቬንቸርና ፋንታዚ በተመረጡ የህፃናት ሥነፅሁፍ ደራሲያን ሥራዎች ውስጥ" በሚል ርዕስ ከዳንኤል ጋር ተመሣሣይነት ያለው ጥናት ሰርታለች፡፡ መሰሉ መዝገቡ "ከ1978 ዓ.ም እስከ 1995 ዓ.ም ታትመው የወጡ የልጆች መፃህፍት መዘርዝር አጫጭር መግለጫዎች" በሚል ርዕስ በ1996 ዓ.ም ባቀረበችው የመመረቂያ ፅሁፍ ላይ በተጠቀሱት አመታት 74 መፃህፍት መታተማቸውን ገልፃለች፡፡ እነዚህና ሌሎችም ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡት ጥናቶች በህፃናት ሥነፅሑፍ

ቅርፅና ይዘት ትንተና፣ ቋንቋ አጠቃቀም ላይ አተኩረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሀገሪቱን የህፃናት ሥነፅሑፍ ታሪክ ለማጥናትና በተወሰነ የጊዜ ገደብ ታትመው የወጡ የህፃናት መፃህፍትን ዝርዝር ያዘጋጁም ይገኙበታል፡፡

በዚህ ጥናት የተቃኙትና ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የህፃናት ሥነፅሁፍን ጉዳያቸው ያደረጉት ሁሉም የጥናት ፅሁፎች ከውጭ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ትምህርት ክፍል የተገኙ ናቸው፡፡ በዚህ ደረጃ ከተቃኙት ጥናቶች ውስጥ ቅድሚያውን የሚይዘው በ1994 ደረጃ መላኩ "The State of Children's Literature in Amharic" በሚል ርዕስ ያጠናው ነው፡፡

ጥናቱ በአማርኛ የተፃፉ የህፃናት መፃህፍት ያሉበትን ሁኔታ የመመርመር ዓላማ ይዞ የተነሳ ነው፡፡ ወደ መዘርዝርነት የሚያደላ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከዘረዘራቸው የህፃናት መፃህፍት መካከል የአንዳንዶቹ ይዘት ለመተንተን የሚሞክርና የሌሎቹን ደግሞ ርዕስ፣ ደራሲ እና የታተሙበትን ዘመን ከመንገር ያለፈ መረጃ የማይሰጥ ነው፡፡

ጠንካራ ጎኑ ቀደም ሲል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት መስፍን መሰለ በ1978 ዓ.ም "የልጆች ሥነ ፅሁፍ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ባጠናው ጥናት የተወሰነ ክፍተት መኖሩን ማመላከቱ ነው፡፡ መስፍን መሰለ በጥናቱ የመጀመሪያው ለህፃናት ተብሎ የተፃፈው መፅሀፍ በ1917 ዓ.ም መታተሙን ቢገልፅም ደረጀ በጥናቱ የመጀመሪያው ለህፃናት ተብሎ በአማርኛ ቋንቋ የተፃፈው መፅሀፍ "ትምህርተ ህፃናት" ሳይሆን በ1916 የታተመው "የፍቅር መላክት ለኢትዮጵያ ልጆች" መሆኑንና ፀሀፊውም በቀለ ወልደማርያም መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡ ይህ ጥናት በአላማውም ሆነ በይዘቱ ከኔ ጥናት ጋር የማይመሳሰል ቢሆንም በመስኩ ለሚደረጉ ጥናቶች ከህፃናት ሥነፅሁፍ አጀማመር ታሪክ ጋር የተያያዙ ጠቃሚ መረጃዎችን የሚያቀብል በመሆኑ ተጠቃሽ ጥናት ሆኗል፡፡

Lensie Bekele በ2005 "Children's Literature : Its Impact on the Mind of the Child Reader" በሚል ርዕስ የህፃናት አንባቢዎችን ምላሽ በማካተት የህፃናት ሥነፅሁፍ በአንባቢዎቹ ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ለመመርመር ጥረት አድርጋለች፡፡ የሌንሴ ጥናት ትኩረት በአብዛኛው ሥነልቦናዊ ትንታኔን በመጠቀም ለልጆች ወይም በልጆች የሚነበቡ ታሪኮች የሚፈጥሩትን አሉታዊ ወይም አወንታዊ ተፅእኖ መመርመር ነው፡፡ የህፃናቱን እድሜ በሦስት በመክፈል ወይም የቀደመ አከፋፈልን በመጠቀም እና እንደየእድሜያቸው ታሪኮችን በመመደብና በማንበብ በመጨረሻም ጥያቄ በማቅረብና ምላሻቸውን በመተንተን

የተደረገው ይህ ጥናት ህፃናት ለታሪኮቹ ያላቸውን ፍላጎት ለማወቅ መምህራንንም አሳትፏል፡፡

በወንድና በሴት መካከል ያለውን የፍላጎትና የታሪኮቹን ተፅዕኖ ፈጣሪነት ደረጃ ለመለየትም ከወንድና ከሴት ተማሪዎች ላይ መረጃ ለማሰባሰብ ጥረት ተደርጓል፡፡ የጥናቱ ግኝትም ሥነፅሁፋዊ ትረካዎች ዕውቀትን ለማስተላለፍ' የተማሪዎችን አእምሮ ለማዝናናትና የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመፍታት የሚያስችል ስልት ለማፈላለግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያደርጉ አመላክቷል፡፡

የሌንሴን ጥናት ምንም እንኳ የአንባቢዎችን ምላሽ በማካተት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ጉዳይ ቢኖርም በሌሎች ጉዳዮች ግን ልዩነት አለው፡፡ በቅድሚያ የዓላማ ልዩነታችን ጎልቶ ይታያል፡፡ የኔ መረጃ የተሰበሰበው በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ላይ ከሚገኙ የተለያዩ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሲሆን ሌንሴ ተፅዕኖውን ለማወቅ በእድሜ መድብ፣ በፆታ ከፍላ ለማየት ሞክራለች፡፡ ዓለም አቀፋዊ እውቅና አላቸው ያለቻቸውን እና በውጭ ቋንቋ የተፃፉትን "Beauty and the Beast" እና "Ali Baba and..." የሚሉ ርዕሶች ያሏቸውን ታሪኮች ተጠቅማባቸዋለች፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ለኢትዮጵያውያን ህፃናት አንባቢዎች የተዘጋጁ ታሪኮች ላይ የተካሄደው የእኔ ጥናት በሀገራዊ ድርሰቶች ላይ የሚያተኩርና በዚህ በኩል ያለውን ክፍተት የሚሞላ ይሆናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ምሥራቅ ጠና 2009 "A Critical Analysis of Children's Story Books of ALEM ESHETU and TESFAYE GEBREMARIAM" በሚል ርዕስ የሰራችው የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ ከኔ ጋር ባለው የተወሰነ ግንኙነት ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ ጥናት ዓለም እሸቱ እና ተስፋዬ ገብረማርያም ባሳተሟቸው አምስት አምስት የህፃናት መፃህፍት ላይ ሂሳዊ ትንተና አድርጓል፡፡ አጥኚዋ የተመረጡትን መፃህፍት ትልም፣ መቼት፣ አንፃር፣ ጭብጥ እና የገፀባህርያት አሳሳል ስልት መርምራለች፡፡ በህፃናት መፃህፍቱ ላይ ባደረገችው ሂሳዊ ትንተናም የመፃህፍቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸውን ገልፃለች፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር የኔን ጥናት የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች ትኩረታቸውን በሀገራዊ ድርሰቶች ላይ ማድረጋቸው እና መፃሕፍቱን ከህፃናት ሥነፅሁፍና ከመሰረታዊ የስነፅሁፍ መስፈርቶች አንፃር ማየታቸው ነው፡፡ ልዩነታቸው የተመረጡት መፃሕፍት የተለያዩ መሆንና በምስራቅ ጥናት ውስጥ ያልተካተተው የህፃናት አንባቢያን አስተያየት በኔ ጥናት ውስጥ መካተቱ ነው፡፡ በመሆኑም ¾እ'@ ጥናት ከዚህ አንፃር ያለውን ክፍተት በመሙላት በኩል በጎ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

ተጠቃሽ ከሆኑ ጥናቶች መካከል ሌላው ራሀመቶ በየነ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የሰራው በአማርኛ የልጆች ተውኔት ላይ ያተኮረ ጥናት ነው። ጥናቱ "Social Issues in Selected Amharic Children's Plays: A Critical Analysis" በሚል ርዕስ የተካሄደ ነው። በአማርኛ ቋንቋ ተፅፈው በመድረክ ለታዳሚ የቀረቡ ተውኔቶች ያነሷቸውን ማህበራዊ ጉዳዮች መርምሯል። ጥናቱ ሠባት የተመረጡ የተውኔት ፅሁፎችን በመመርመር በተውኔቶቹ ውስጥ ጎልተው የሚታዩትን ማህበራዊ ሁኔታዎች አሳይቷል። የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ፣ የመደብ ልዩነት፣ ራስወዳድነት፣ ቅናት፣ ትዕግስት ማታለልና የመሳሰሉትን ርዕሰ ጉዳዮች በተውኔቶቹ ውስጥ በመዳሰስ የህፃናት ተውኔቶቹ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩ ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶችን በማጋለጥና ጥሩ የሚባሉትን በማበረታታት በኩል የጎላ አስተዋፅኦ እንዳላቸው አስረድቷል። ይህ ጥናት በማህበራዊ ሁኔታ ዙሪያ የተውኔት ፅሁፎቹ የሚያስተላልፏቸውን መልዕክቶች፣ የሚያነሷቸውን ጉዳዮች በመመርመር ትኩረቱን ወደ አንድ አቅጣጫ ያደረገ ሲሆን የኔ ጥናት ግን በሥነፅሁፍ ዘርም ይሁን በዓላማ እንዲሁም በዘዴው ከዚህ ይለያል። ከሥነፅሁፍ ዘር አንጻ የሆነውን ተውኔት አንስቶ በህፃናት ላይ ትኩረት ማድረጉ ሊያመሳስለን ቢችልም ነገር ግን ከላይ እንደተጠቀሰው በስነ ፅሁፍ ዘር፣ በዓላማና በአጠናን ዘዴ ያለን ልዩነት የሠፋ ነው።

## 2.2 የንድፈ ሀሳብ መሰረቶች

በህፃናት መፃህፍት ላይ ምሁራን የተለያዩ አስተያየቶች ይሰጣሉ። አንዳንዶች ህፃናት የሚያነቡት እና የሚደሰቱበት ማንኛውም ፅሁፍ የህፃናት ሥነፅሁፍ አካል ሊሆን ይገባል ሲሉ ሌሎች ደግሞ ህፃናት አንበው የሚደሰቱበት ማንኛውም ፅሁፍ ብቻ ሳይሆን ለህፃናት ታስበው የሚፃፉና ከፍተኛ ሥነፅሁፋዊ ጥራት እና ኪነጥበባዊ ፋይዳ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል ይላሉ (Sutherland 1997: 6)። በሌላ በኩል የህፃናት መፃህፍት ይዘት የህፃናቱን ፍላጎት ያገናዘበ፣ ሥነምግባርን የሚያስተምር ዕውቀትንና መረጃን የሚያስተላልፍ እንዲሁም ባህልን ለመጠበቅ የሚረዳ ቢሆን ይመረጣል። የያዙት መረጃ በቀላሉ ለህፃናት የሚገባ እና ለባህሪያቸው መስተካከል አስተዋፅኦ ያለው እንዲሆንም ይጠበቃል (Sanders 1967:22)። ለህፃናት ተብለው ከሚፃፉት መፃህፍት ውስጥ ጥሩ የምንላቸው ይዘታቸው፣ መቼታቸው፣ ገፀባህሪያቸው እና ቋንቋቸው ለህፃናት በሚያመች መልኩ በአንድነት ሲቀርቡ ነው በማለት ምንጭ ጠቅሳ (Misrak 2009: 11) ገልፃለች።

በአጠቃላይ ለህፃናት የሚፃፉ መፃህፍት ለትላልቆቹ እንደሚፃፉት ሁሉ በጥንቃቄ ሊፃፍ እና ሥነፅሁፋዊ ውበት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ምክንያቱም መፃህፍቱ ለሁለቱም (ለህፃናቱም ሆነ ለትልልቆቹ እንደየ እድሜያቸው እና ደረጃቸው እኩል ጥቅም ይሰጣሉና፤

መፅሐፍት ለኑሮ ፍፁም መተኪያ የሌላቸው ናቸው፡፡ የኑሮን አማራጮች ጣፋጭ በሆነ (አሰልቺ ባልሆነ መንገድ) ያመላክታሉ ህይወት በአንድ አቅጣጫ ብቻ ወጥራ ስታስጨንቅ መፅሐፍት የስሜት ህዋሶችን በማነቃቃት የመኖር ጥቅምን እንድናስተውል ያደርጋሉ፡፡ ህይወት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በገባች ጊዜም በጊዜያዊነት ከችግሩ እንድናመልጥ አሊያም መውጫ ቀዳዳችንን የሚጠቁም አዲስ መንገድ እንድንማትር ይረዱናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሚያስፈልገንን እረፍትና ተዝናኖት ከመፃህፍት እናገኛለን፡፡ አጠቃቀማቸውን ላወቀበት መፃህፍት ሁልጊዜም የመረጃ፣ የምቾትና የደስታ ምንጮች ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ለአዋቂዎች እንደሚሰራ ሁሉ ለህፃናትም የሚያገለግል ነው (Arbuthnot 1964:2)::

በመሆኑም ከላይ እንደተገለፀው መፃህፍት ደረጃውና ሁኔታው ቢለያይም ለአዋቂዎችም ሆነ ለህፃናት ተመሣሣይ ጥቅም ይሰጣሉ፡፡ ያም ሆኖ ህፃናት የሚያስደስታቸውን መፅሀፍ ለማቅረብ የማህበረሰቡን አጠቃላይ ልምድ ማወቅና በግለሰብ ደረጃ ጎልቶ የሚታየውን ፍላጎት መለየት አስፈላጊ መሆኑን የመስኩ ምሁራን ይገልፃሉ (Altstetter 1961፡6):: ከዚህም በተጨማሪ የሚፃፈው ፅሁፍ በየትኛው የዕድሜና የእውቀት ደረጃ ላይ ላለው ህፃን ነው? ለሚለው ጥያቄ በቂ ምላሽ ማግኘት ያሻል፡፡ ከዚህ በሚቀጥለው ክፍል ትኩረት ከሚደረግባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ውስጥ አንዱም ይኸው ነው፡፡ በተጨማሪም የህፃናት መፃህፍት ብያኔን፣ አይነትና ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች እንዲሁም የአንባቢያን አስተያየትን በተመለከተ የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦችን ለማየት ጥረት ይደረጋል፡፡

## 2.2.1 የህፃንነት ብያኔ

ለህፃናት የሚቀርበውን የሥነፅሁፍ ይዘት' ባህሪና አጠቃላይ የአቀራረብ ሁኔታውን ከመወሰናችን በፊት ህፃንነትን መበየን፣ የዕድሜ ገደቡንም መወሰን ይኖርብናል፡፡ በሀገራችን ህፃን ወይም ልጅ የሚሉት ቃላት አንዱ ሌላውን እየተኩ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ለህፃንነትም ይሁን ለልጅነት ቁጥር ያለ የእድሜ ገደቡን የሚያመለክት የመዝገብ ቃላት ብያኔ ባለመኖሩም ሁለቱም ቃላት በአጠቃላይ ለአቅመ አዳም/ሄዋን ያላደረሱትን የህብረተሰብ ክፍሎች ለማመልከት የሚረዱ የወል መጠሪያዎች ሆነዋል፡፡ ያም ሆኖ ለዚህ ጥናት አመቺ

የሚሆነውን ቃል ለመምረጥ የቃላቱን የመዝገብ ቃላት ፍቺዎች ማየት ያስፈልጋል፡፡ ልጅ የሚለውን ቃል ብያኔ ለማግኘት በደስታ ተክለወልድና በኪዳነወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ውስጥ አጥኚው ያደረገው ፍለጋ ውጤት ባያስገኝም ደስታ ተክለወልድ በፃፉት መዝገበ ቃላት ውስጥ "ለጋ ልጅ" ለሚለው ሀረግ "ከ15 ዓመት በታች ያለ ልጅ" (ደስታ 1962 ዓ.ም፡706) የሚል ብያኔ ተሰጥቶታል፡፡ ይህ ብያኔ የሚሰራው ግን ልጅ የሚለው ስም ላይ "ለጋ" የሚል ገላጭ ሲታከልበት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ በሌላ በኩል ከሳቴ ብርሃን ተሰማ የዐማርኛ መዝገብበ ቃላት "ልጅ" የሚለውን ቃል ገና ያላደገ ወንድ ልጅ ወይም ሴት (ተሰማ 1951 ዓ.ም፣ 53) በማለት ፍቺ ይሰጡታል፡፡

"ሕፃን" የሚለውን ቃል ደግሞ ኪዳነወልድ ክፍሌ በቁሙ ዐራስ፣ ጨቅላ፣ ጡት ያልተወ፣ ራሱን ያልቻለ ታናሽ፣ ለጋ፣ ርጥብ ልጅ ወንድ ሴት በማለት ይበይኑታል፡፡ "ህፃንነትንም" ዐፍላነት፣ ጉብዝና፣ ልጅነት ነው በማለት ያብራሩታል (ኪዳነወልድ 1948 ዓ.ም፣ 458)፡፡ከዚህ በተጨማሪ "ህፃን" ለሚለው ቃል "ዐቅመ ዓዳም ያላደረሰ በአካል በአይምሮ የሚያድግ ልጅ የሚል ብያኔም ተሰጥቶታል (ተሰማ 1951 ዓ.ም 83)፡፡ ከነዚህ ህፃን እና ልጅ ለሚሉት ቃላት ከተሰጡት ብያኔዎች በመነሳት ህፃን ከዚህ ዕድሜ እስከዚህ ነው ፤ልጅ ደግሞ በዚህ የዕድሜ ወሰን ውስጥ የሚካተት ነው የሚል ቁርጥ ያለ ብያኔ ባናገኝም ህፃን ለሚለው ቃል ከተሰጡት ብያኔዎች በመነሳት ለዚህ ጥናት ቃሉ ተመራጭ ሆኗል፡፡ ምክንቱም ከዐራስነት ጀምሮ ዐካለመጠን ያለደረሰ እስከሚባለው ዕድሜ ድረስ በህፃንነት ውስጥ በመካተቱና የዐፍላነት የጉብዝና እና የልጅነት እድሜ መሆኑ በመጠቀሱ ልጅ ከሚለው ቃል ይልቅ ህፃን የሚለው ስያሜ የተስማማ ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረት የተለያዩ ተቋማት ለህፃንነት የሚሰጧቸው ብያኔዎች በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ታህሳስ 20 ቀን 1989 አፅድቆ ከመስከረም 2 ቀን 1990 ጀምሮ በሥራ ላይ ያዋለው የህፃናት መብት ኮንቬንሽን ህፃን ማለት ከ18 አመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው መሆኑን ያስረዳል፡፡ በኮንቬንሽኑ ክፍል አንድ ምዕራፍ አንድ የሚከተለው ሰፍሯል "በዚህ ኮንቬንሽን ህፃን ማለት በሀገሩ ህግ መሰረት ከዚህ በአነሰ ዕድሜ አካለ መጠን ካላደረሰ በቀር እድሜው ከ 18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው" (የሕፃናት ኮንቬንሽን 1992፡9)፡፡

ይህ ድንጋጌ ለየሀገሩ ህጎች እውቅና የሰጠ ይመስላል፡፡ ሀገራት ከ 18 ዓመት ባነሰ ዕድሜ የሚገኙ ልጆችን ለአካለ መጠን ደርሰዋል የሚል የተለየ ህግ ከሌላቸው በስተቀር ከ18 ዓመት በታች ያሉ ልጆች ሁሉ ህፃናት እንደሚባሉም ደንግጓል፡፡

ወደ ሀገራችን ሁኔታ ስንመለስ አሁን በስራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያው ሪፖብሊክ ህገ መንግስት የህፃናትን መብት የሚዘረዝርበት አንቀፅ 36 የህፃንነትን የእድሜ ገደብ በውል አያስቀምጥም በደፈናው "ማንኛውም ህፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት" (የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያው ሪፖብሊክ ህገ መንግስት 1987 ዓ.ም፣36) ብሎ ነው የሚያልፈው፡፡ በሌላ በኩል የመምረጥና የመመረጥ መብትን የሚያብራራበት አንቀጽ 38 ማንኛውም ዜጋ ዕድሜው 18 ዓመት ሲሞላው በህጉ መሰረት የመምረጥ መብት እንዳለው ይገልፃል፡፡ ህፃን የሚለው ማንን እንደሆነ በግልፅ የእድሜ ገደቡን ባያስቀምጥም ህፃን የሚለውን ቃል የተጠቀመበት መንገድ የመምረጥን መብት ከደነገገበት የእድሜ ገደብ ጋር ተያይዞ በህገ መንግስቱ የህፃንነት እድሜ ገደብ 18 ዓመት እንዲመስል አድርጎታል፡፡

የተሻሻለው የፌዴራል መንግስቱ የቤተሰብ ህግ በምዕራፍ 12 አንቀፅ 215 ላይ አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ፆታ ሳይለይ ዕድሜው አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ልጅ ነው ሲል ከላይ የተገለፀውን ሀሳብ አጠናክሮታል (የተሻሻለው የፌዴራል መንግስቱ የቤተሰብ ህግ 1992 ዓ.ም፣ 62)፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያ ህጎችም ህፃን (ለአካለመጠን ያልደረሰ) የሚባለው ከ18 ዓመት በታች ያለ ሰው ነው የሚል ማጠቃለያ ላይ መድረስ እንችላለን፡፡

በተጨማሪም ኢትዮጵያ የህፃናት መብት ኮንቬንሽን ፈራሚ ከሆኑት ሀገሮች መካከል አንዷ በመሆኗ በኮንቬንሽኑ ለተካተቱት ሁሉም ስምምነቶች ተገዢ ናት ስለሆነም የህፃንነት ዕድሜ ገደብን የምትወስንበት የተለየ ህግ እስከሌላት ድረስ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የህፃናት መብት ኮንቬንሽንን ውሳኔ ታከብራለች፡፡

በተመድ የህፃናት መብት ኮንቬንሽንም ሆነ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የቤተሰብ ህግ ፆታ ሳይለይ እድሜው ከ 18 ዓመት በታች ያለን ሰው ይመለከታል ብለን መውሰድ እንችላለን፡፡ ከነዚህ ብያኔዎችና የእድሜ ወሰኖች በመነሳትም አንድ ሰው ከተወለደበት እስከ 18 ዓመቱ ድረስ ባለው እድሜው ህፃን ተብሎ ይጠራል ብለን ልናጠቃልል እንችላለን፡፡

ሥነልቡና ምሁራንም እስከ 18 ዓመት ያለውን የሰው ልጅ ዕድሜ በተለያየ የእድሜ ደረጃ ይከፍሉታል፡፡ ከነዚህ ምሁራን መካከል Papalia እና Oldes ከቅድመ ወሊድ (prenatal stage) ጀምረው እስከ 18 ዓመት ያለውን ጊዜ በአምስት ክፍል ይመድቡታል፡፡

በህፃናት ላይ የሚታየውን የአእምሮና የአካል ዕድገት መሠረት አድርገው በመደቡት መሰረት

1. Prenatal period ( ቅድመ ወሊድ ) ከመፀነስ እስከ መወለድ
2. Infancy and toddlerhood ከመወለድ እስከ 3 ዓመት
3. Early childhood ከ3 ዓመት እስከ 6 ዓመት
4. Middle childhood ከ6 ዓመት እስከ 12 ዓመት
5. Adolescence ከ12 ዓመት እስከ 18 ዓመት በማለት ከፍለውታል (Papallia እና Oldes 1990፡12)፡፡

በዚህ መሰረት ህፃን ለሚለው እሳቤ የሚመለከተው እስከ 12 ዓመት ያለውን ቢሆንም በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ እንደየዕድሜ ደረጃው የተለያየ አከፋፈል እንዳለ መረዳት እንችላለን፡፡

## 2.2.2 የህፃናት ስነፅሁፍ ብያኔ

ለህፃናት ስነፅሁፍ አንድ ቁርጥ ያለ ብያኔ የለውም፡፡ የተለያዩ አከራካሪ ነጥቦች የሚነሱበት በመሆኑ አንድ ወጥ ትርጉም ሊገኝለት አልቻለም፡፡ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ብዙ ነው፡፡ ከምክንያቶቹ ውስጥም የህፃናት መጽሐፍ የምንለው በልጆች የተፃፈውን ነው ወይስ ለልጆች የተፃፈውን ነው? ለሚለው ጥያቄ ቁርጥ ያለ መልስ አለመገኘቱ ይጠቀሳል፡፡ በእርግጥም እንደ ሲንጋፖር ባሉ አንዳንድ ሀገሮች በትምህርት ቤት ውስጥ በህፃናትና በታዳጊ ወጣቶች የሚፃፉ የፈጠራ ታሪኮች ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸውና ተቀባይነት ያላቸው በመሆኑ ለዚህ የስነፅሁፍ አይነት ህፃናት አስተዋፅኦ ያበረክታሉ (Perumbulavil: 1979:74)::

የተለመደውና ለህፃናት ታስቦ የተደረሰ መጽሐፍ ሁሉ በህፃናት ስነ ጽሁፍነት ሊፈረጅ ይችላል የሚለው ብያኔ አብዛኞዎቹን በመስኩ የተለያየ አቋም ይዘው የሚከራከሩ ወገኖችን ያቀራርባል፡፡ በእርግጥም ልጆችም ፃፉት አዋቂዎች ለህፃናት ተብሎ እስኪተፃፈ ድረስ በዚህ የስነ ፅሁፍ ዘርፍ ቢፈረጅ ሊያስማማ የሚችል ይመስላል፡፡

"የህፃናት ሥነፅሁፍ ለልጆች ከተወለዱበት ቀን እስከ ጉርምስና የዕድሜ ዘመናቸው ድረስ ጠቃሚና ተወዳጅ ታሪኮችን በዝርው፣ በግጥም፣ በልቦለድ ወይም በኢ-ልቦወለድ መልክ

የሚያቀርቡ መፃህፍት ናቸው" (እነ Brown 1999፡1) በማለት የህፃናት መፃህፍትን ምንነት ያስረዳሉ፡፡ የሚገፉትም ህፃናቱን ለማዝናናትና መረጃ ለማቅረብ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

## 2.2.3 የህፃናት መፃህፍት ዓይነቶች

የህፃናት መፃህፍትን የተደራሲያኑን ዕድሜ ወይም የሥነፅሁፉን ርዕስ ጉዳይ በማየት መመደብ ይቻላል፡፡ የተደራሲያኑን ዕድሜ ከግምት ውስጥ በማስገባት የመፃህፍቱን አቀራረብ የታሪኩን ርዝመት፣ ውስብስብነት መወሰን አንዱ የመፃህፍቱን አይነት ለመመደብ የሚያስችል መንገድ ነው፡፡ እንደየ አንባቢያኑ ዕድሜ ታሪኩን በስዕል መልክ በማቅረብ ፣ ምዕራፉን በማስረዘምና በማሳጠር መልዕክቱን በማቅለልና በማክበድ ታሪኩን በማወሳሰብና ግልጽ በማድረግ ለተደራሲያኑ የሚመጥን መጽሐፍ ይዘጋጃል፡፡ የሚዘጋጀው መጽሐፍ ልቦለድም ይሁን ኢልቦለድ ለህፃናቱ ዕድሜ እንዲመጥን አድርጎ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ በተለይም መረጃ ሰጪ ፅሁፎች ከሆኑ በተመሳሳይ ርዕስ አንድ ደራሲ ቢጽፋቸው እንኳ ለ3 ዓመት ህፃንና ለ10 ዓመት ልጅ የሚዘጋጅ መፅሀፍ አቀራረብ ፈጽሞ አንድ ዓይነት ሊሆን አይችልም (Horning 1997:19)፡፡ በማለት የመፃህፍት ይዘትና አቀራረብ በሚቀርብለት ተደራሲ ዕድሜ እንደሚወሰን ያስረዳሉ፡፡

በሌላ በኩል የህፃናት መፃህፍት በያዙት ርእሰ ጉዳይ፣ በሚያስተላልፉት መልዕክት ወይም በሚያተኩሩበት የስነፅሁፍ ዓይነት መመደብ ይቻላል፡፡ አንዳንድ መፃህፍት ስለሰው አኗኗር የሚናገሩ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ በአንድ ወቅት የተፈፀመን ታሪክ በልቦለድ መልክ ወይም እንዳለ ያቀርባሉ፡፡ አንዳንዶቹም ስለ እንስሳት ያወራሉ፡፡ የቀደሙ ተረቶችንም ለአንባቢያቸው የሚያቀርቡም አሉ፡፡ በእነዚህና በሌሎች የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች የተፃፉትን የህፃናት መፃህፍት በበርካታ ንኡሳን ክፍሎች መመደብ የሚቻል ቢሆንም እንደ Arbuthnot, Horning እና Norton የመሳሰሉት ምሁራን ከጠቀሷቸው የመፃሕፍት ዓይነቶች መካከል የሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

## 2.2.4 ባህላዊ ስነፅሁፍ

ባህላዊ የህፃናት ሥነፅሁፍ (Traditional Literature) የሚባሉት በመጀመሪያ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የመጡ የተለያዩ ዝርያዎች ያሏቸው ትረካዎች መሆናቸውን (Horning 1997:46) ያስረዳሉ፡፡

የእነዚህ ትረካዎች ደራሲያን በውል አይታወቁም፣ ይሁን እንጂ የትረካዎቹ ሰብሳቢዎችና የመጀመሪያ አሳታሚዎች እንደ ደራሲያን ስማቸው ይነሳል፡፡ ለዚህም የግሪም ወንድማማቾች

በ19ነኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ባሰባሰቧቸውና ባሳተሟቸው ተረቶች የተነሳ በመላው አውሮፓ እንደትረካዎቹ ባለቤት የሚጠቀሱባቸው ሁኔታዎች ይታያሉ፡፡
ትረካዎቹን ለመሰብሰብ ምክንያት የሆኑት የማህበራዊ፣ የሥነልቦና እና የባህል ጥናት የትምህርት ክፍሎች ናቸው፡፡ እየቆየ ግን ትረካዎቹ ለልጆች የሚሰጡት ጥቅም እየላቀ በመምጣቱ ለህፃናት ተስማሚ በሆነ መልክ በስፋት ታትመዋል፡፡

ትረካዎቹም እንደየ ባህሪያቸው በተለያየ ክፍል ይመደባሉ፡፡ ትረካዎቹንም ለመገምገም የመጀመሪያ ተግባር የሚሆነው በየትኛው የባህላዊ ሥነፅሁፍ ክፍል ውስጥ እንደሚመደቡ መለየት ነው፡፡ ባህላዊ ሥነፅሁፎቹም በተለያዩ ስሞችና አይነቶች የሚመደቡ ቢሆኑም በተለያዩ መፃህፍትና ምሁራን ከተጠቀሱት ውስጥ የተወሰኑት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.2.4.1 ፌብል

ለህፃናት ቀለል ያሉ ሥነ ምግባርን ለማስተማር የሚረዱ ታሪኮች የሚቀርቡበት የሥነፅሁፍ አይነት ነው። ባህላዊ ከሚባሉት የሥነ ፅሁፍ ዓይነቶች የሚመደብ በቃል ከሚተላለፉ ትረካዎች ተርታ የሚሠለፍ የህፃናት ሥነፅሁፍ ወገን ነው። ፌብል አጠር ያሉ ተጨባጭ ያልሆኑ ሀሳቦች የሚገለፁበት ትረካ ነው። ጥሩ ወይም መጥፎ ብልጥ ወይም ሞኝ የመሣሰሉት ባህሪያት የሚገለጹበት በቀላሉ መገንዘብና ለማስታወስ በሚያስችል መልኩ የሚቀርቡበት ትረካ ነው። “ገፀባህሪው ሰው ቢሆን ወይም አውሬ በማንም ተፅዕኖ ስር ሳይወድቅ ለሌሎች ትምህርት በሚሰጥ መልኩ ተግባርን የሚያከናውንበት የትረካ አይነት ነው” (Arbuthnot 1964÷298)። ፌብል ከምሳሌያዊ አነጋገር እና ከመፅሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ጋር የሚመሳሰልበት ባህሪም አለው። ሦስቱም አጠር ብለው የተሟላ መልዕክት ለማስተላለፍ በሚያመች መንገድ የተቀመሩ ሲሆኑ ምሳሌያዊ አነጋገሩ ግን ከሁሉም የሚያጥር ነው፡፡

### 2.2.4.2 ተረት

እንደ Horning 1997:51 ማብራሪያ ከምክንያታዊነት ይልቅ ምናባዊነት ጎልቶ የሚታይበት ገፀባህሪያቱ ሰው ወይም እንስሳት የሆኑበት ፈጣን የታሪክ አወቃቀር ያለውና ጥሩ ያደረገ የሚመሰገንበት መጥፎ የሰራም የሚወቀስበት፣ የሚቀጣበት ታሪክ የያዘ ነው። ከአንድ ትውልድ ወደ ቀጣዩ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ ትረካ ነው፡፡ መጀመሪያ ባህላዊ ስነፅሁፍ ቢሆንም ወደ

ዕህሬት ከመጣ በኋላ በተረት ቅርፅ የተለያዩ የህፃናት መፃህፍት ስገበያ እየቀረቡ ነው። ተዋቂ ደራሲያን የተረት ባህሪያትን ለማሟላት በሚያስችል መልኩ ድርሰታቸውን ያቀርባሉ ይህ የተፃፈው ፎክቴልም ቀደም ሲል በቃል ሲተላለፍ ከመጣው ጋር ለመለየት በሚያስቸግር መልኩ የሚቀናበር ነው (ዝኒ ከመሁ 1997፣ 22) ስለሆነም ተረት የህፃናት ስነፅሁፍ ከሚቀርብበት ስልት አንዱ እየሆነና እየተለመደ የመጣ የስነፅሁፍ አይነት ነው።

## 2.2.4.3 ሚት

"የዓለምን አፈጣጠር የሚያስረዳ፣ የተፈጥሮ ክስተቶችን የሚጠቁም የስነፍጥረት ታሪክ የሚይዝ ተረክ ሚት ይባላል:: የሚት መጀመሪያው የጥንት ሀይማኖታዊ ክዋኔ ነው።" (እነ Brown 1999፡98) በዚህ ትረካ ውስጥ የሚገኙት ገፀባህሪያት አማልክት ሲሆኑ መቼቱም ከመሬት እጅግ የራቀ ወደ ሰማይ የቀረበ ሊሆን ይችላል:: ይህ መለኮታዊ ተግባር የሚገለፅበት ትረካ በሀይማኖታዊ ስነፅሁፍ ውስጥ እንጂ በህፃናት ስነፅሁፍ ውስጥ መካተት እንደሌለበት የሚከራከሩ አሉ። ይሁንእንጂ በርካታ አስደናቂ የሆኑ ሚታዊ የህፃናት ስነፅሁፍ ስብስቦች በአሁኑ ወቅት በስፋት ይገኛሉ። በተጨማሪም ነጠላ የሆኑ ሚታዊ ታሪኮች በስዕላዊ መፅሀፍት ቅርፅ ይታተማሉ።

## 2.2.5 ግጥሞች

"ግጥም ለህፃናት ተፈጥሮአዊ የስነ ጽሁፍ ዘር ነው። በማንኛውም የዕድሜ ክልል ያለ ሰውም በግጥም በእጅጉ ደስ ይለዋል" (እነBrown 1999÷40):: የህፃናት እንቅስቃሴ በራሱ ደግሞ ምታዊ ነው። "የህፃናት የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ የራሱ የሆነ ምታዊነት አለው። ህፃናት ሲወድቁ፣ ሲነሱ፣ ሲራመዱ፣ ሲሮጡ፣ ሲዘሉ፣ ሲንከባለሉ፣ ሲስቁ፣ ሲያለቅሱ እንዲሁም ሲጫወቱ የሚያደርጓቸው ክንዋኔዎች ከአንድ አይነት ምት ጋር የተያያዙ ናቸው" (ዘሪሁን 1986፡99)። ግጥም በአብዛኛው ህፃናት ዘንድ የሚወደድ በመሆኑ በአነስተኛ የእድሜ ክልል ላይ ያሉ ህፃናት ሳይቀሩ ግጥምን ከሰሙ (ካነበቡ) በኋላ በቀላሉ በቃላቸው የመያዝና መልሰው የማንብነብን ባህሪ ያሳያሉ:: ይህም ተፈጥሮአዊነቱን እና ለህፃናት ያለውን ቅርበት ያመለክታል። እናም ግጥም አንዱ ለህፃናት ዕውቀት ማድረሻ መንገድ ደስታ መፍጠሪያ አቅጣጫ ነው ሊባል ይችላል።

### 2.2.6 ኢልብወለድ

ኢልብወለድ መፃህፍት በአብዛኛው የሚነበቡት መረጃ ለማግኘት ነው። የእንስሳት ባህሪያትን ለማወቅ፣ የመኪና ስሞችንና የፍጥነት ወሰናቸውን ለመረዳት፣ ስለ ሩጫና ስለታዋቂ ሯጮች ታሪክ ለማወቅ እና ይህን የመሰሉ ጉዳዮችን ለመረዳት እነዚህ መፃህፍት ተዘውትረው በህፃናት ይነበባሉ። እንደነዚህ አይነት መፃህፍት በዩኤስ አሜሪካ ቤተመፃህፍት በስፋት እንደሚገኙና በህፃናት ተዘውትረው እንደሚነበቡ በቤተ መፃህፍት ውስጥ ለአመታት የሰሩት (Horning 1997: 22) ያስረዳሉ።

### 2.2.7 ልብወለድ

ደራሲያን ለህፃናት የሚመጥኑ፣ የሚያዝናኑና የሚያስደስቱ ታሪኮችን በመፍጠር በመፃህፍት አሳትመው ያሰራጫሉ። እነዚህ መፃህፍት ህፃናቱ የሚኖሩበትን አጠቃላይ ሁኔታ በአዲስ መልክ በማስተዋወቅ ምናባቸውን ለማስፋት አቢይ ሚና አላቸው። "የልጆች ልቦለድ በርካታ የአፃፃፍ ስልት፣ ይዘትና፣ ቅርፅን በመከተል ሊፃፍ ይችላል፤ ይህም የልጆቹን ችሎታ እና ፍላጎት መሰረት በማድረግ ነው" (Horning 1997:149)::

በደራሲያን የሚፈጠሩ ታሪኮችን በሁለት የሚመድቧቸው የዘርፉ ባለሙያዎች አሉ፡፡ ከነዚህ መካከል Norton የተባሉት ፀሐፊ ከልጆች ስነፅሁፍ ጋር የተያያዙ የፈጠራ ስራዎች ወቅታዊ እውነታዊ ልቦለድ እና ዘመናዊ ፋንታሲ ተብለው እንደሚከፈሉ ያስረዳሉ፡፡ እነዚህን ቀጥለን በዝርዝር እንመልከት፡፡

#### 2.2.7.1 ዘመናዊ ፋንታሲ

ዘመናዊ ፋንታሲን አስመልክተው (Norton 1999: 352) እንደሚያብራሩት ምናባዊ በሆነ መልኩ ታሪክን በመፍጠር በእውነተኛው አለም የማይሆነውን ነገር እንደሚታመን አድርጎ የማቅረብ ስልትን የሚከተል ነው፡፡ የዚህ አይነቱ ስነፅሑፍ የማይሰለች፣ የሚስብና የሚታመን ሆኖ እንዲቀርብ የልቦለድ አላባውያን አጠቃቀም ላይ የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ዘመናዊ ፋንታሲ ሁነቶችን ሁሉ በሚያሳምን መልኩ አስመስሎ ማቅረብን ይጠይቃል፡፡ አንባቢን በምናብ ወደ ሌላ አለም በመውሰድ በነባራዊው አለም የማይሆነውን ነገር እየሆነ እንዳለ ሆኖ እንዲሰማው ማድረግ አንባቢውን ለማሳመን ድርሰቱንም ተአማኒ ለማድረግ ይረዳል፡፡ የእንስሳትን ንግግር፣ የሰውን በሰማይ ላይ መብረር፣ የቁስን መብላትና መጠጣት

እና የመሳሰሉትን ተግባራት ልብ በሚሰቅልና ሊሆን ይችላል በሚያስብል መልኩ ቢቀርብ ይመረጣል፡፡ ተፈጥሯዊና ማህበራዊ ህግጋትን እና ደንቦችን በድርሰቱ የሚያፈርስ ፀሐፊ የፈጠራ ስራው የሚገዛበት ሌላ ህግ ማበጀት ይጠበቅበታል፡፡ ባወጣው ህግ መሰረትም ታሪኩ ሊፈፀም የሚችል መሆኑን ማስረዳትና ማሳመንም ይኖርበታል፡፡ ለዚህ ህግም በታሪኩ ውስጥ ተገገርነቱን ማሳየት አለበት፡፡

አላማን የሚያሳካ ተስማሚና ተአማኒ ከባቢና ሁኔታ መፍጠርም ታሪኩን ተነባቢ ከሚያደርጉት ግብአቶች ውስጥ ተጠቃሽ ነው፡፡ በዚህ የስነፅሑፍ አይነት ብዙ ጊዜ የደራሲያን አላማ የሚሆነው የሰውን ሕይወት መግለጥና ሰብአዊነቱን ማሳየት መሆኑን Potricia Wrightson የተባሉ ፀሐፊን ጠቅሰው (Norton 1999:353) ያስረዳሉ፡፡ በዘመናዊ ፋንታሲ ደራሲያን ለታሪካቸው ያልተለመደ አይነት አለም መፍጠር ወይም የእውኑን አለም በምናብ ከፈጠሩት ጋር በማዛመድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚህ በፈጠሩት አለም ውስጥም በታሪካቸው የተካተቱት ሁነቶች መከናወን እንደሚችሉ የሚያሳምኑ ስልቶችን መከተላቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

የገፀባህሪ አሳሳላቸውም ለእንስሳት ሰዋዊ ባህሪ ማላበስ ወይም ቁሳቁስን እንስሳዊ ተግባር እንዲያከናውኑ ማድረግ ቢሆን ተጨባጭ በሆነው በዚህ አለም ይሆናል ተብሎ የማይታመነውንም ነገር ልብን በሚሰቅል የታሪክ መዋቅር ውጤትን በምክንያት እያስደገፉ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡ በገፀባህሪ አሳሳሉ ሰውን የአማልክት ባህሪ በመስጠት ወይም እጅግ ልዩ በሆነ ሁኔታ ውስጥ በማሳለፍ ድርሰቱን በተደራሲያን ዘንድ ተወዳጅ ማድረግ ይቻላል፡፡ በዚህ አይነት ድርሰት ውስጥ በእውነተኛው አለም የማይኖር ግን በታሪኩ የሚታመን የሚወደድ ገፀባህሪ ለመፍጠር ደራሲያን ቋንቋን እንደ ዋነኛ መሳሪያ ይጠቀሙበታል፡፡ በዚህ አይነት ታሪክ ከእውነታዊ ልብወለድ ይልቅ በህፃናት ላይ የሚደርስ ፍርሃትን የመቀነስ ዕድል አለው፡፡ የታሪኩ መቼትና ገፀባህሪያቱ ከእውነተኝነት ወጣ ማለታቸው በአካባቢያቸው እንዳለው እና አስፈሪ ተደርጎ እንደተሳለ ነገር አያስፈራቸውም (Sanders 1967: 18)::እንደ (Norton 1999: 355)ገለጻ ደግሞ የዘመናዊ ፋንታሲ ድርሰት ጭብጥ ብዙውን ጊዜ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያላቸውን የጋራ እሴቶች የሚያበረታታ ቢሆን ይመረጣል፡፡ ዓላማው ስነምግባርን ከሰብዓዊ ስሜት ጋር በማቆራኘት ላይ የሚያተኩር ነው ይላሉ፡፡በአለም ላይ በጥሩና በመጥፎ ተግባር መካከል ዘወትር የሚካሔደው ጦርነት ማህበራዊና ግለሰባዊ ኃላፊነት፣ ፍቅርና ጓደኝነት የመሳሰሉት ጉዳዮች የእነዚህ ድርሰቶች ዋነኛ ጭብጦች መሆናቸውንም ያስረዳሉ፡፡

### 2.2.7.2 ወቅታዊ እውነታዊ ልብወለድ

ወቅታዊ ሁኔታዎችን ከግምት አስገብቶ አሁን ባለው ዓለም የሚፈፀሙ ታሪኮችን ተንተርሶ፣ ይህንኑ የምንኖርበትን ምድር ተጠቅሞ የሚጻፍ ታሪክ ነው፡፡ እውነታን ከዘመኑ ዋና ዋና አሳሳቢ ጉዳዮች ጋር አስተሳስሮ በመያዙ ወቅታዊ እውነታዊ ልቦለድ የሚለው ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ወቅታዊ እውነታዊ ልቦለድ የሚለው ሀረግ የሚያመለክተው መዋቅሩን፣ ገፀባህሪውንና መቼቱን ጨምሮ በሰው ልጅ እውነተኛ አኗኗር ውስጥ አሁን ባለው ዓለም ላይ በቋሚነት የሚታይ መሆኑን ነው፡፡ እውነታዊ የሚለው ቃል ግን ታሪኩ እውነት ነው ማለት ሳይሆን ሊፈፀም የሚችል መሆኑን ለማመልከት የሚረዳ ነው (Norton 1999፡ 458)፡፡

በእውነታዊ ልቦለድ ወቅታዊ የሆኑ ህዝባዊ አጀንዳዎች ተነስተው ተስማሚ የሆኑ ታሪኮች ይፈጠሩላቸዋል፡፡ አጀንዳዎቹ ህብረተሰቡ የሚያውቃቸው የራሱ ጉዳዮች፣ ታሪኩም በእውነት ሊከሰት የሚችል በመሆኑ ደራሲው አንባቢያኑን ለማሳመን የሚፈጥረው የተለየ ነገር (ዓለም) አይኖርም፡፡ በዚህ አይነቱ የታሪክ መዋቅር ውስጥ ሁነቶች በምክንያትና ውጤት ላይ የተመሰረተ ሁነኛ ትልም አላቸው፡፡

እንስሳት ተፈጥሮአዊ (ትክክለኛውን) እንስሳዊ ባህሪ ተሰጥቷቸው በታሪኩ ይካተታሉ፡፡ ሰዎችም በውሃ ውስጥ እንዲኖሩ ወይም በሰማይ እንዲበሩ አይፈቀድላቸውም ሠዋዊ ባህሪ ይሰጣቸዋል እንጂ፡፡ ምክንያቱም ታሪኩ የሚፈጠረው በወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ ሆኖም የተፈጠረው ታሪክ የግድ የተፈፀመ ስለመሆኑ መረጃ ማቅረብ ምስክር መቁጠር አያስፈልግም፡፡ ነገር ግን በነባራዊው አለም በተጨባጭ ሊከሰት የሚችል መሆን ደግሞ አለበት፡፡ በዚህ መልክ ለልጆች የሚዘጋጁ ታሪኮች አንባቢያኑ ህፃናት ተመሳሳይ ዕድሜ ካላቸው ሌሎች ህፃናት ጋር አንድ አይነት ፍላጎቶች እንዳሏቸው ወይም በታሪኩ ውስጥ ካሉት ገፀባህሪያት ጋር ተመሳሳይ ችግር እንዳለባቸው ለመረዳት ያስችላሉ፡፡ ነገሮችን ለመመልከት የተለየ እይታ እንዲኖራቸው፣ ከአዳዲስ ጀብዱዎች (Adventures) ጋር እንዲተዋወቁ፣ የተሰማቸውን ለሌሎች እንዲገልፁ፣ ለችግሮቻቸው በአዲስ መልክ መፍትሔ እንዲያፈላልጉ እና እንዲዝናኑ በማድረግ በኩል በተለይ እውነታዊ ልቦለድ አቢይ ሚና አለው፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ በናሙናነት የተመረጡት መፃህፍትም የእንስሳት ታሪክ የያዙ (ዘመናዊ ፋንታሲ) እና የሠዎችን ታሪክ የሚነግሩን እውነታዊ ልብወለዶች ናቸው፡፡ "ብልሁ ጠቋሪት"፣

“ቱሲ እና ቹኪ” እንዲሁ “ሊንቻ እና ቢንቻ” የሚሉ ርዕሶች ያሏቸው መፃህፍት በዘመናዊ ፋንታሲ መልክ የተፃፉና ገፀባህሪያቱም እንስሳት ሲሆኑ “የአንቿነሽ ተስፋ”፣ “የአሰለፈች ሎሚዎች” እና “ካሳ” የሚሉት መፃህፍት በወቅታዊ ማህበራዊ ችግሮች ላይ ተመስርተው የተፃፉ የፈጠራ ስራዎች ናቸው፡፡ በመፃህፍቱ ላይ የሚደረገው ሂሳዊ ትንተና በልብወለድ አላባውያን እና የቃላት አጠቃቀም ላይ ሊመሰረት ይችላል፡፡ በትኩረት የሚታዩትም ትልም፣ ገፀባህሪይ፣ መቼት እና ጭብጥ ይገኙበታል፡፡ ምክንያቱም የህፃናት ልብወለድ መፃህፍትን በምንገመግምበት ጊዜ ለእነዚህ አላባውያን ትኩረት ሰጥተን ግምገማችንን ማካሄድ እንችላለን (Homing 1997: 152)::

## 2.3 የህፃናት መፃህፍት መለኪያዎች

በኢልቦለድም ሆነ በልቦለድ የህፃናት መፃህፍት ውስጥ የሚፃፉት ርእሰ ጉዳዮች በህፃናት አንባቢያን ሊወደዱ የሚችሉ የአፃፃፍ ስልቶች የተከተሉ ስነዕሁፋዊ ውበትን የተላበሱ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ በመሆኑም እነዚህ የስነፅሁፍ ዘሮች የሚጠይቁትን መስፈርት ያሟሉ የህፃናት መፃህፍት ተፈላጊነትን ለማግኘት ከሚያስችሉ ነገሮች ውስጥ የተወሰኑትን አሟሉ ማለት ነው:: “ልጆች በፈጣን እንቅስቃሴ፣ በጀብደኝነትና በቀላሉ በሚገመቱ ሁነቶች የተሞሉ ታሪኮችን ማንበብ ይፈልጋሉ” (እነ Brown 1999:3)፡፡ጥራትን ለመጠበቅ አንድም የልጆች ፍላጎትን መጠበቅ ሌላም የስነፅሁፍ ዘሩ የሚጠይቀውን መስፈርት ማሟላት ተገቢ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት የህፃናት ልቦለድ መፃህፍት ላይ በመሆኑ ደራሲያን በሚፅፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ትኩረት ሊያደርጉባቸው ይገባል ተብለው ከሚጠቀሱት ውስጥ የተወሰኑትን ዘርዘር አድርጎ መመልከት ይገባል፡፡

### 2.3.1 የህፃናት ልብወለድ አላባውያን

የልቦለድ አላባውያን በልጆች ስነፅሁፍ ውስጥ በአግባቡ ሊገኙ ይገባል፡፡ መፅሀፍቱ ከሚመዘኑባቸው ነገሮች ውስጥም ዋነኛው ይኸው ነው፡፡ እነዚህ አላባውያን የሥነፅሁፉ አይነት በሚፈቅደው መሰረት በድርሰቶቹ ውስጥ መካተት ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም የአላባውያን በወጉ በህፃናት ሥነፅሁፍ (ልቦለድ) ውስጥ መኖር ስነፅሁፉ የታሰበለትን ግብ ይመታ ዘንድ ወሳኝ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡

## 2.3.1.1 ትልም

ትልም የታሪኩን ሁነቶች በቅደም ተከተል በማቅረብ አንባቢን እስከ መጨረሻው የታሪኩ ክፍል ይዞ ለመጓዝ ወሳኝ ድርሻ ያለው ነው። በታሪኩ ውስጥ የሚከሰቱ ሁነቶችን ከነምክንያታቸው ይይዛል፤ ምክንያትና ውጤቱንም ያሳያል፤ ምን ለምን ተደረገ ለሚለው ጥያቄም መልስ ያስገኛል (ዘሪሁን 1992 ዓ.ም፣ 157)።

‹‹ጥሩ ትልም የአንባቢን ልብ ማንጠልጠልና ማስደነቅ የሚችል ግጭት በመፍጠር እስከመጨረሻ በታሪኩ ውስጥ እንዲጓዙ የማድረግ አቅም አለው›› (እነ Brown 1999:26)። ግጭት የሚፈጠርበት የትልሙ መጀመሪያ ክፍል፣ ግጭቱ እያደገ ወደ ንረት (ጡዘት) የሚደርስበት እና ግጭቱ ረፍት የሚያደርግበት የትልሙ መጨረሻ መኖሩም ታሪኩን በአግባቡ ለመረዳትና ለመከታተል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። ትልም በተለያየ መንገድ ሊዋቀር ይችላል። በህፃናት መፃህፍት ግን ተዘውታሪው በቅደም ተከተል የሚቀመጥ የታሪክ መዋቅር ነው። ልጅ ይፀነሳል፣ ይወለዳል፣ ያድጋል ... የሚለው ለዚህ አይነቱ የቅደም ተከተል የታሪክ መዋቅር ጥሩ ምሳሌ ይሆናል። በዚህ መልኩ የሚሄድ ትልም ያላቸው መፃህፍት የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች (ገፆች) ገፀባህሪያቱን ማስተዋወቂያ ናቸው። ደረጃ በደረጃም ግጭቱን ፈጥሮ ታሪኩን እያጣፈጡ ለአንባቢ ማቅረብና በኋላም የግጭቱን ከፍተኛ ደረጃ (ጡዘቱን) በማሳየት ቀስ በቀስም የግጭት አፈታቱን ለአንባቢያን ምቹ በሆነ መልኩ በማቅረብ ታሪኩን ተዓማኒ አጓጊና አስደሳች በሆነ መልኩ ማዋቀር ከደራሲያኑ የሚጠበቅ አቢይ ተግባር ነው። ከዚህ በተጨማሪም ደራሲያን ቀደም ብሎ ከተከናወነው ታሪክ ይልቅ የቅርቡን በማስቀደም ታሪኩን ለአንባቢ የሚያቀርቡበት ስልትም አለ የዚህ አይነቱ አወቃቀር ብዙ ጊዜ የሚያገለግለው በምዕራፍ ለተከፋፈሉ እና እድሜአቸው ከፍ ላለ (ታዳጊ ወጣቶች) ነው።

## 2.3.1.2 ገፀባህርያት

በህፃናት ሥነፅሁፍ ውስጥ ትልቅ ቦታ ከሚሰጣቸው የሥነፅሁፍ አላባውያን መካከል ገፀባህሪ ዋነኛው ነው። በህፃናት መፃሕፍት ውስጥ ገፀባህሪያቱ የህፃናት አንባቢያን ጓደኞች ጊዜያዊ ወዳጆች ያሆናሉ። እንደ ገፀባህሪያቱ ለመሆን ይመኛሉ፤ በእጅጉ ይወዷቸዋል ያስቡላቸዋልም።

ደራሲው ገፀባህሪውን ሲስል አንባቢ በውል እንዲረዳው (እንዲያውቀው) ተክለሰውነቱን፣ ባህሪውን፣ ስሜቱን፣ ሥነምግባሩን ከሌሎች ገፀባህሪያት ጋር ያለውን ግንኙነት መግለፅ ያስፈልጋል። በህፃናቱ በውል የታወቀ ገፀባህሪ በአንባቢ ዘንድ የሚኖረው ስፍራ ትልቅ ነው። ይህ ደግሞ መፅሀፉ ለሚኖረው ተቀባይነት ትልቅ ዋጋ አለው። ገፀባህሪውን የማስተዋወቅ ሥራው በተለያየ ስልት ሊከናወን

ይችላል በትረካ መግለፅ ከሌሎች ገፀባህሪያት ውይይት ማንነቱን ማስረዳት በታሪኩ ውስጥ በሚፈፀመው ተግባር ባህሪውን ማመልከት ይቻላል (Norton 1999:144)።

በህፃናት ሥነፅሁፍ ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚኖሩት ገፀባህሪያት አንድ ወይም ሁለት ዋና ገፀባህሪያት ናቸው። ዋነኛው ገፀባህሪ በአግባቡ ሊገለፅ የሚገባ ከመሆኑም ባሻገር ጥሩ ወይም መጥፎ አለበለዚያም ጥሩና መጥፎ ባህሪያትን አጣምሮ የያዘ ሊሆን ይችላል። ልክ በእውን እንደምናየው ሰው አንዳንድ ጊዜ የሚሸነፍ ሌላ ጊዜ የሚያሸንፍ አንዴ የሚቆጣ ሌላ ጊዜ የሚታገስ ባህሪ ያለው ገፀባህሪ ወጥ ከሆነ (ጥሩ ሆኖ ጀምሮ ከሚጨርሰው) ይልቅ በህፃናት መፃህፍት ውስጥ የሚፈለግ ነው። እነ (Brown 1999:19) እንደሚሉት የልጆች ልቦለድ መፅሀፍ ውስጥ በአግባቡ የተገለፁና እያንዳንዱ ባህሪው የታየ ገፀባህሪ ወጥ ባህሪ ካለውና በዛ ባህሪው ብቻ ከሚታወቅ ገፀባህሪ በተሻለ ተቀባይነት አለው ።

### 2.3.1.3 መቼት

አንባቢያን የሚያዩትና የሚሰሙት መልካምድራዊ አቀማመጥ እና ታሪኩ የተፈፀመበት ጊዜ ፍፁም ታማኝ መቼት ነው ሊባል ይችላል። እንደታሪኩ አይነት መቼቱ በእጅጉ አስፈላጊ ወይም የተወሰነ ጥቅም ያለው ተደርጎ ይወሰዳል። ለምሳሌ በታሪካዊ ልቦለድ ውስጥ ጊዜን ማመልከት የታሪኩን ሁኔታ ለመረዳት ጠቀሜታው የጎላ ነው በመሆኑም በታሪኩ ውስጥ በተሟላ ሁኔታ ጊዜውንና ቦታውን መጥቀስ በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

### 2.3.1.4 ጭብጥ

በማንኛውም ሥነፅሁፍ ውስጥ የሚገኝና ደራሲው ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ጭብጥ ይባላል። ጭብጥን ለማወቅ ደራሲው በዚህ ፅሁፍ ምን ለማለት ነው የፈለገው የሚለውን ጥያቄ አንባቢ ለራሱ ማቅረብ ይኖርበታል። ጭብጥን ለመግለፅም ነጠላ ቃል ከመጠቀም ይልቅ በተሟላ አረፍተ ነገር ማስረዳት ይሻላል (እነ Brown 1999: 27)። በህፃናት መፃህፍት ውስጥ የሚኖረው ጭብጥ የህፃናቱን ትኩረት የሚስብና እውነት ለማስተማር የሚረዳ ከፍተኛ የሞራልና የሥነምግባር ደረጃ ያለው መሆን ይኖርበታል፤ ነገር ግን በትልምና በገፀባህሪያት ላይ ጫና ማሳደር አይኖርበትም። ህፃናት በተለይ ልቦለድ የሚያነቡት ለመደሰትና ለመዝናናት እንጂ ሆን ብለው ያላቸውን እውቀት ለማሳደግ ባለመሆኑ ደራሲያን በዚህ በኩል መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል።

መልዕክት ለማስተላለፍ በማሰብ ስነፅሁፋዊ ውበቱንና ሳቢነቱን ያጣ ፅሁፍ በአንባቢያን ዘንድ ያለው ተፈላጊነት አነስተኛ ስለሚሆን በፈጠራው ታሪክ ውስጥ ፈፅሞ በማያስታውቅ ሁኔታ ለማስተላለፍ

ያስቡትን መልዕክት ማካተት ይኖርባቸዋል። ሁልጊዜ አዋቂዎች በሚፅፉት የህፃናት መፃህፍት ውስጥ የሚታየውን በግልፅ የመምከር ሙከራን ገታ አድርጎ ከፈጠራው ታሪክ በመነሳት ህፃናቱ የትኛው ተግባር ስህተት የትኛው ደግሞ ትክክል እንደሆነ እንዲረዱ ማድረግ ተገቢ ነው። ለህፃናቱ ስለሚተላለፈው መልዕክት ፍንጭ ለመስጠት የገፀባህሪያቱን ተግባር ሀሳብ በማጉላት ማሳየት የትኛው ተግባር እንዳሸለመና የትኛው እንዳስቀጣ በታሪኩ ማካተት ይቻላል። በተጨማሪም ከአጠቃላይ የታሪኩ ውጤት እና ከትረካው እንዲሁም ከርዕሱ ህፃናቱ ስለታሪኩ አጠቃላይ መልዕክት (ስለጭብጡ) ፍንጭ እንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል (Norton 1999:151)::

## 2.3.2 የቃላት አጠቃቀም

ቃላት ዋናውን ታሪክ በአግባቡ ለመንገርና መልዕክቱን ለማስተላለፍ ቁልፍ ሚና አላቸው በመሆኑም የህፃናት ስነፅሁፍ ደራሲያን ለቃላት ምርጫ መጠንቀቅ እንዳለባቸው ይህን ሀሳብ የሚደግፉ ወገኖች ያስረዳሉ፡፡ ". . . ለሚነገረው ታሪክ ተመጣጣኝ የሆኑ ቃላት በእጅጉ አስፈላጊ ናቸው፡፡ አንድ የህፃናት መፃህፍት ገምጋሚ መፃህፍቱን እንዳነበበ ደራሲው እነዚህን ቃላት ለምን መረጠ? በቃላቱ አማካኝነት ለማስተላለፍ ያሰበው ቁምነገር ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት ይኖርበታል" (እነ Brown 1999:31)::

ታሪኩን ለህፃናት በሚያስደስት መልክ ለማቅረብ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የቃላት ምርጫ ሁነኛ ቦታ ሊኖረው ይገባል፡፡ የቃላት ፍቺ ለመፈለግ በሚደረግ ጥረት የታሪኩ መልዕክት ሊዛባ ወይም ሊረሳ ይችላል እና ቀላል ቃላት መጠቀም ታሪኩን በአግባቡ እስካስኬደው ድረስ ተመራጭ ነው፡፡ በመሆኑም ቃላትን ለማስተማር በሚል በቋንቋው ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን መጠቀም ያስፈልጋል (Enrlich 1969: 87) የሚለው አስተሳሰብ ዋናው መልዕክት በአካባቢ እንዳይተላለፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ለህፃናት የሚፃፉ መፃሕፍትን ሳቢ የሚያደርጉ ዋና ዋና ሀሳቦች ብለው Tooze በፃፉት መጣጥፍ የሚከተሉትን ሀሳቦች በማጠቃለያ መልክ አቅርበዋቸዋል፡፡ ታሪኩ ጥሩ ትልም ሊኖረው ይገባል፡፡ በግጭት፣ በተቃርኖ፣ በድግግም የሚያድግ ታሪክ ሳቢና ተወዳጅ መሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ዋናው ታሪክ በምንም ጣልቃ ገብ ጉዳይ መረበሽ አይኖርበትም፡፡

ተራኪው ስለቋንቋ አጠቃቀም ጥሩ ዕውቀት ያለው፣ በቃላት ምርጫ የተካነ መሆንም ይኖርበታል ገፀባህሪያቱ በእውነት ላይ የተመሰረቱ የሚታመኑ ስለነሱ ያወቀ ሁሉ

የሚጠነቀቅላቸው ዓይነት ሆነው መሳል ይጠበቅባቸዋል፡፡ መቼቱ የታሪኩን ዋጋ በሚያሳድግ መልኩ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ትረካው የሚቀርብበት ሁኔታና መቼት ለእውነተኛ ሁነት የተመቸ ሆኖ መሳል ለታሪኩ ተቀባይነት ማግኘት ትልቅ ቦታ አለው፡፡ የአቀራረብ ስልቱም ከታሪኩ ተፈጥሮና ከዓላማው ጋር ተመጣጣኝ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች በውል የተገነዘበ ደራሲ በአንባቢያን ልብና አእምሮ ውስጥ ህይወት ያለው ታሪክ ማኖር የሚችልበትን ትልቅ ተግባር አከናውኗል (Tooze 1961:40-41)::

## 2.4 የአንባቢያን ምላሽ ንድፈ ሀሣብ

የአንባቢያን ምላሽ ንድፈ ሀሣብ (Reader-response theory) አንባቢያንን በሥነ-ፅሁፍ ሥራ ውስጥ እንደዋነኛዎቹ ባለድርሻ አካላት የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሣብ መሠረት የሥነ-ፅሁፍ ሥራ ህልውናም የአንባቢያን ምላሽ (አስተያየት) ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ በተለይም በህፃናት ልብወለድ ውስጥ ዋነኛዎቹ ተተኳሪዎች ተደራሲያኑ በመሆናቸው ይህ ንድፈ ሀሣብ የተለየ ቦታ ይሰጠዋል (Moss 1992: 42)::

በ1960ዎቹና 70ዎቹ በአሜሪካና በጀርመን በዘመናዊ መልክ የተጀመረው ይህ ንድፈ ሀሣብ መነሻው I. A Richards በሚባሉ የሥነ-ፅሁፍ ምሁር አማካይነት እንደነበር በ1924 እና በ1929 የተፃፉ መፃህፍትን ጠቅሰው (Benton 1999፡ 84) ገልፀዋል፡፡ ይህ ንድፈ ሀሣብ መጀመሪያ ለሥነ ትምህርት ዓላማ የታሰበ ቢሆንም እያደር ለሥነ-ፅሁፋዊ ሂስ የሚሠጠው አገልግሎት እያየለ መጥቷል፡፡ይሁን እንጂ ይህ ንድፈ ሀሣብ ለበርካታ ዓመታት ተገቢ ትኩረት ተነፍጎት ቆይቷል፡፡ «አንድ ደራሲ ገፀባህርያቱን በጥንቃቄ እንደሚስል አንባቢያንንም በአግባቡ ግምት ውስጥ ያስገባ ሥራ መስራት ይኖርበታል፡፡ ያን ጊዜ አብዛኛውን ሥራ አንባቢያኑ እራሳቸው ያከናውኑለታል በዚህም ሥራውን ተወዳጅ ማድረግ ይችላል፡፡» (Benton 1999:84)፡፡ በማለት የአንባቢያን አስተዋፅኦ በሥነ-ፅሁፍ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው አስረድተዋል፡፡

ከአንባቢያን ወይም ከተመልካች ምላሽ በመነሳት የሥነ-ፅሁፍ ሥራዎችን ለመገምገም ጥረት የሚያደርገው ይህ ንድፈ ሃሣብ ቀደም ሲል ለደራሲ፣ ለሥነ-ፅሁፋዊ ይዘትና ቅርፅ ትኩረት ሠጥቶ ይከናወን ከነበረው ሂስ ጋር በተወሰነ መልኩ ተቃራኒ አስተሣሠቦችን ያራምዳል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ንድፈ ሀሣብ ዋነኛው የመገምገሚያ መሥፈርትና የሂስ ግብአት የአንባቢያኑ አስተያየት ነው፡፡ ፅሁፉ ወይም ደራሲ አልያም ሥነ-ፅሁፋዊ ቅርፅ የሚታየው ከአንባቢያን

አስተያየት በመነሣት ነው። ፅሁፍ ብቻ በቂ ነው ወይም የደራሲያንን ህይወት ማጥናት አስፈላጊ ነው የሚሉ ንድፈ ሃሣቦች በአንባቢ ምላሽ ብዙም ቦታ የላቸውም። ያም ሆኖ ግን በአንባቢያን ምላሽ ሃያሲያን አስተሳሰብ ፅሁፍ (text) እና አንባቢ (reader) ሁለቱም በእጅጉ አስፈላጊ እና በዚህ ንድፈ ሀሳብ ሒስ ለመስጠት ዋነኛ ግብአቶች ናቸው። በእርግጥም የሚነበብ ነገር እና አንባቢ ሁለቱም ለዚህ ቲዎሪ አስፈላጊ ናቸው አንባቢ ከሌለ ማን ምላሽ ሊሰጥ የሚነበብ ነገር ከሌለ በምን ላይ አስተያየት ሊሰጥ ይችላል?

## 2.4.1 የምላሽ አይነቶች

የአንባቢያን ምላሽ ንድፈ ሀሣብን የሚደግፉ ወገኖች በሥነ-ፅሁፍ ሥራ ውስጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ አካል አንባቢ፣ ለሂስ መነሻ የሚሆነው ሀሣብም የሚገኘው ከአንባቢ ነው ብለው ይከራከራሉ።

ምክንያታቸው ደግሞ ሥነ-ፅሁፍ የሚፃፈው ለአንባቢያን በመሆኑ በትክክል የዓላማውን መሳካት ወይም አለመሳካት ለማወቅ ከነዚህ ወገኖች የሚገኝ አስተያየት ትልቅ ስፍራ አለው የሚል ነው። የትኛውንም መስፈርት ተጠቅሞ ሥነ-ፅሁፍን ከመተቸት ይልቅ የአንባቢያንን አስተያየት ተከትሎ የተገኘውን ውጤት ማሣየት መተርጎም ከሁሉ በላይ ዋጋ እንዳለውም አበክረው ያስረዳሉ።

> የአንባቢያን ምላሽን መሠረት ያደረጉ የሥነ-ፅሁፍ ሃያሲያን ለተፃፈው ታሪክ ሁነኛ ትርጉም የሚገኝለት አንባቢያን በሥነ-ፅሁፍ ሥራው ላይ ተመሥርተው ከሚያከናውኑት ተግባር፣ ከሚሠጡት አስተያየት ነው ሲሉ ይከራከራሉ። አንባቢያንን እንደ ሥነ-ፅሁፍ ሥራ ማዕከላዊ አካል ይመለከቷቸዋል። በመፃህፍት ላይ ልዩ መብት ላላቸው (እንደ ደራሲያን) ላሉ አካላት እንኳ የሚሠጡት ግምት ከአንባቢያን ጋር የሚመጣጠን አይደለም። ግለሠባዊ ንባብ የትኩረት አቅጣጫቸው እየሆነ መጥቷል (Benton 1999:87)።

በማለት ከላይ የተጠቀሱት ፀሐፊ በዚህ ንድፈሀሣብ ተከታዮች ዘንድ የአንባቢያን አስተያየት ያለውን ትልቅ ቦታ አስረድተዋል። ከአንባቢያን በሶስት ዓይነት መንገድ አስተያየት (ምላሽ) ለመሠብሰብ ይቻላል።

የመጀመሪያው ከግለሰብ የንባብ ልምድ ላይ ተመስርቶ የሚሰበሰብ ምላሽ ሲሆን ይህም አንድ አንባቢ ያለውን አጠቃላይ የንባብ ልምድ መነሻ በማድረግ ለሂስ ግብአት የሚሆን ሀሣብ የሚሰበሰብበት ነው። ይህ ሁኔታ በዚህ ንድፈ ሐሳብ ተከታዮች ዘንድ ትልቅ ዋጋ ያለው ነው። እንደውም የምላሽ አይነቶችን ከሚወስኑት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ተደርጎ ይወሰዳል። አንዳንዴ

አዎንታዊ ሌላ ጊዜ ደግሞ አሉታዊ አስተዋፅኦ ሊኖር እንደሚችል ይታመናል፡፡ አንባቢዎች ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ የቀደመ የንባብ ልምዳቸውን አሁን ለማንበብ የሚፈልጉትንና ከተመረጠው ፅሁፍ እናገኛለን ብለው የሚያስቡትን ነገር ይዘው እንደሚመጡ (Norton 1999፥44) በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቀሰው በተወሰነ የታወቀ ቡድን ላይ ተመስርቶ የሙከራ አስተያየት መሰብሰቢያ ስልት ነው፡፡ ይህ ዘዴ ስነልቦናዊ ሙከራ (psychological experiment) የሚካሄድበት የምላሽ ማሰባሰቢያ ነው፡፡ በሶስተኛነት ከሁሉም አንባቢያን ከሚገኝ ምላሽ ላይ ተንተርሶ የሚሰጠው ትንታኔ የሚጠቀስ ነው፡፡ በዚህ ስልት የግለሠብ የንባብ ልምድ ወይም ሥነ-ፅሁፋዊ እውቀት ሣይታይ አንባቢያኑ በተወሰነ መፅሀፍ (text) ላይ የሚሠጡትን ምላሽ መሠረት በማድረግ የሚሰጥ ሂስ ሲሆን በአንፃራዊነት ሚዛናዊ ሊባል የሚችል ምላሽ መሰብሰቢያ ስልት ነው፡፡

በአንባቢያን ምላሽ መሰብሰቢያ መንገዶች ውስጥ መሠረታዊው ልዩነት የሚኖረው ከግለሠባዊ የንባብ ልምድና ከሥነ-ፅሁፍ ንድፈ ሀሣብ እውቀት የተነሳ የሚከሰተው ነው፡፡ ከዚህም ሌላ የህፃናት ምላሽ በእድገታቸው ውስጥ አስተዋፅኦ ባላቸው ሁኔታዎች ይወሰናል፡፡ የልጆች አስተሳሰብ ደረጃ፣ የቋንቋ፣ የሰብእና፣ የማህበራዊ፣ ሞራላዊና አካላዊ እድገት ተማሪዎች ያነበቡትን የሚተረጉሙበትና ለታሪኩ ምላሽ የሚሰጡበትን መንገድ እንደሚወስን ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ በሌላ በኩል የሚነበበው የስነፅሑፍ አይነት በአንባቢያን ምላሽ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ያለው ነው፡፡ የታሪኩ አወቃቀር ቋንቋ የገፀባህሪያት አሳሳል እና በስነፅሁፍ ዘርፍ ልዩነት ምክንያት የመላሾቹ አስተያየት በተለያየ ሁኔታ ውስጥ ሊገባ ይችላል (Norton 1999፡44)፡፡ ያም ሆኖ ሌሎች ግለሰባዊ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው በእድሜና በንባብ ልምድ ግን በአንድ የክፍል ደረጃና በተወሰነ የእድሜ ክልል ያሉ ህፃናት የሚሠጡት ምላሽ ከሞላ ጎደል ተቀራራቢ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል፡፡

## 2.4.2 የህፃናት አንባቢያን ምላሽ

በህፃናት ሥነ-ፅሁፍ ላይ የሚሰጥን ምላሽ አስመልክቶ ስፊ ትንታኔ የሠጡት (Benton 1999፡ 84) "የህፃናት ሥነ-ፅሁፍ አንባቢያን ምላሽ ሂስ በሁለት ጉዳዮች ላይ በተመሠረቱ ጥያቄዎች ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው፡፡ አንዱ ስለ ሥነ-ፅሁፉ ሲሆን ሌላው ደግሞ ስለ ህፃናት አንባቢያኑ ነው" በማለት ያስረዳሉ፡፡

አንባቢያን በስነፅሁፍ ስራ ላይ ምላሽ እንዲሰጡ ተጠይቀው ስለ ስነፅሁፍ የሚሰጡት አስተያየት በትንተና ወቅት እንደግብአት ያገለግላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተሰጣቸው የስነፅሁፍ ሥራ ላይ

መሰረት አድርጎ አንባቢያኑን ለመለካት የሚሰጡ ጥያቄዎች ይኖራሉ። በዚህም የአንባቢያኑ የስነፅሑፍ እውቀት ደረጃ ይለካል። ምላሻቸውም በዚሁ ባላቸው የእውቀት ደረጃ እየተሰፈረ የትንተናው ሥራ ይከናወናል። በዚህም ምክንያት አንባቢያንና ስነፅሁፍ በዚህ ንድፈ ሀሳብ ዋነኞቹ ጉዳዮች ናቸው ሊባሉ ይችላሉ። ከህፃናት አንባቢያን ጋር ተያይዞ የሚደረገውም ጥናት በአስተማሪ አጥኚዎች በክፍል ውስጥ የሚከናወን ሲሆን ምንባቡን (text) አውድ (context) አንባቢና የጥናት ዘዴ የሚባሉት ተለዋዋጮች የሚካተቱበት ነው።

በምንባብ (text) ውስጥ አጫጭር ትረካዎች፣ ግጥሞች፣ ተረቶች እና ሥዕላዊ መፃህፍት ይሸፈናሉ። በአውድ (context) ዳግም ክፍሉና በክፍል ውስጥ ያሉት ሁኔታዎች በምላሽ ላይ የተለያየ ተፅዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉት ሁሉ ይካተታሉ። ከላይ እንደተጠቀሰው የአንባቢያኑም ልምድ በሚሰጡት ምላሽ ላይ የራሱ አስተዋፅዖ አለው። አጥኚው የሚከተለው የጥናት ዘዴም በምላሹ ላይ ተንተርሶ ለሚገኘው ውጤት የራሱ ሚና እንዳለው ይታመናል።

በዚህ ሁሉ ውስጥም ቢሆን አንድ የሥነ-ፅሁፍ ሥራ ጥሩ ወይም መጥፎ የሚባለው አንባቢያኑ ለሥራው ያላቸውን አስተያየት መሰረት በማድረግ ነው። ምንም እንኳ አዋቂዎች ለህፃናት ይስታ የሚሠጧቸውን መፃህፍት በጥራት ለማቅረብ ጥረት ቢያደርጉም እነዚህ የሥነ-ፅሁፍ ሥራዎች ጥሩ ናቸው የሚባሉት በህፃናቱ ሲወደዱ ነው። መጥፎዎች ናቸው የሚባሉትም በአንባቢ ህፃናቱ ተቀባይነት ሲያጡ ነው። አዋቂዎች መፅሀፍቱን ቢያደንቋቸው ህፃናቱ ሊያነቧቸው ካልቻሉና አሰልቺ ከሆኑባቸው ጥሩ ተብለው ሊወደሱ አይችሉም (Arbuthnot 1964:2)። አንባቢያኑ የሚሠጡት ምላሽ የቃል ወይም የፅሁፍ ቢሆን ለብቻቸው ወይም በቡድን ውይይት ድምፃቸው ቢቀረፅ የሚሰበሰበው መረጃ በንባቡ ላይ ያላቸውን አስተያየት የሚጠቁም እስከሆነ ድረስ በሃያሲያኑ እይታ ቀላል የማይባል ቦታ አለው። (Benton 1999: 93)

አንባቢያኑ በመፅሐፍቱ ላይ የሚሰጡት አስተያየት ወይም ምላሽ የሚተነተነው ከመፅሐፉ ይዘት ወይም ከስነፅሑፋዊ ውበቱ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። ይህንን አስመልክተው (Norton 1999፡ 46) እንደሚያስረዱት "የስነፅሑፍ ሀያሲያንና የሚመለከታቸው አካላት በአንባቢያን አስተያየት ዙሪያ ሲወያዩ ደጋግመው የሚያነሷቸው ቢያንስ ሁለት የምላሽ አይነቶች አሉ እነሱም ስነፅሁፋዊ ይዘት (Efferent) እና ስነፅሁፋዊ ውበት (Aesthetic) በመባል ይታወቃሉ" የሁለቱን የምላሽ አይነቶች ልዩነትን ሲያብራሩ በታሪኩ ውስጥ የሚፈፀሙ ተግባራት፣ በሚገኙ መረጃዎች፣ በሚደረስባቸው ማጠቃለያዎች በሚሰጡ የመፍትሔ ሀሳቦች እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ አትኩሮ ከሚደረግ ንባብ የሚገኘው ምላሽ በስነፅሁፍ ይዘት

ላይ ያተኮረ ወይም Efferent ይባላል ብለዋል፡፡ ከታሪኩ ጋር በተያያዘ ከስነፅሁፍ ሥራው ላይ የሚታየንን፣ የሚሰማንን ስሜትና የሚመጣብንን ሀሳብ መሰረት በማድረግ የሚሰጠን ምላሽ ደግሞ ስነፅሑፋዊ ውበት ላይ የሚያተኩር (Aesthetic) ተብሎ እንደሚጠራ ገልፀዋል፡፡

ህፃናት በስነፅሁፍ ሥራ ላይ የሚሰጧቸው ምላሾች እንደ ትምህርት ደረጃቸው ወይም እንደ እድሜያቸው ሊለያዩ ይችላል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት የአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች በመሆናቸው በዚህ የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች የሚሰጡት ምላሽ በምን ላይ ሊያተኩር እንደሚችል ከተገለፀው ውስጥ የሚከተለውን መጥቀስ ይቻላል "በ4ኛ እና በ5ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች የታሪኩን ገፀባህሪ ከራሳቸው ተግባር ጋር እያወዳደሩ በምላሻቸው ሊያብራሩ ይችላሉ" (ዝኒ ከመሁ 1999:47)::

## 3. የተመረጡ መፃህፍት ትንተና

### 3.1 ብልሁ ጠቋሪት

ወደ ትንታኔ ከመግባቴ በፊት "ብልሁ ጠቋሪት" የሚል ርዕስ የተሰጠውን መፅሐፍ ታሪክ በአጭሩ ላቅርብ፤ ዋናው ገፀባህሪ ብልሁ ጠቋሪት የተባለ አህያ ነው። አህያው ከዘመዶቹ ጋር ይኖር ነበር። አንድ እለት ግን ጅቦች በእሱና በዘመዶቹ ላይ ጥቃት ሰነዘሩ። አድፍጠው ይዘው ሊበሏቸው አሳደዷቸው። ጠቋሪትና ዘመዶቹ ተበታተኑ። ጠቋሪት ጅቦቹ ተከትለውኛል ብሎ ሲሸሽ ከአካባቢው ርቆ ተጓዘ። ጎልብማ በሚባል ከጥንቸልና ሚዳቆዎች በስተቀር ሌሎች የዱር እንስሳት የማይኖሩበት ስፍራ ደረሰ። በዛ ጥቂት ጊዜ ቆይቶ የዘመዶቹ ናፍቆት ስለበረታበት ወደድሮው አካባቢ ለመመለስ ወሰነ። በጉዞው ሁለት አይነት ፈተናዎች እንደሚያጋጥሙት ጠንቅቆ ያውቃል። አንዱ ወንዝ ነው። በወንዙ በኩል ለመሔድ ከወሰነ እጅግ አደገኛ በሆኑ አዞዎች ሊበላ ይችላል፤ በሌላ አቅጣጫ ጫካ አለ። በጫካው በኩል ከሔደ ደግሞ ስጋ በል አውሬዎች ሊያጋጥሙት ይችላሉ።

ብዙ ካወጣና ካወረደ በኋላ የጎልብማ ሀገር ሰዎች የገደሏቸውን የዱር አራዊት ቆዳ የሚያስቀምጡበትን ስልቻ ተሸክሞ በጫካው በኩል ጉዞ ጀመረ። በጉዞው ያጋጠሙትን ዝንጀሮዎች፣ ተኩላዎችና ጅቦች የያዘውን የዱር አራዊት ቆዳ እኔ የገደልኳቸው አራዊት ቆዳ ነው እያለ በማስፈራራት ከዘመዶቹ ተቀላቅሎ ኑሮውን በሰላም በጤና መኖር ቀጠለ። ከዚህ በላይ ታሪኩ በአጭሩ ቀርቧል የሚቀጥለው ትንታኔው ነው።

ይህ መፅሐፍ ዘመናዊ ፋንታሲ በሚባለው የህፃናት መፃህፍት አይነት የተፃፈ ነው። ገፀባህሪያቱ እንስሳት ናቸው። ታሪኩ የሚጀምረው የዋናውን ገፀባህሪ አኗኗር በማስተዋወቅ ነው። በርግጥ "የብልሁ ጠቋሪት" አካላዊና ስነልቦናዊ ማንነቱ በውል አይገለፅም። ሆኖም ብልህ ከሚለው ገላጭ ባህሪውን ጠቋሪት ከሚለው ስሙ ደግሞ የመልኩን ቀለም ልንገምት እንችላለን። ገፀባህሪውን ብልህነት ድፍረቱን በመጠኑ የሚያሳይ ገለፃ ቢኖር ተመራጭ ይሆን ነበር።

ደራሲው ታሪኩን በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ የተጠቀመበት ዘዴ አንባቢን "እሁን ደግሞ ምን ይል ይሆን?" በሚል ጥያቄ ለመወጠር ረድቶታል። ብልሁ ጠቋሪት ያለበትን ወቅታዊ ሁኔታ በማስቀደም ከቤተሰቦቹ በመለየቱ ምክንያት ያደረበትን ናፍቆት ለመወጣት በሚወስነው ውሳኔ

ግጭት ውስጥ ይገባል። ምክንያቱ ጠንክር ብሎ ባይገለፅም ብልሁ ጠቋሪት ከሚወዳቸው ቤተሰቦቹ መለየቱ ያሳደረበትን የናፍቆት ሁኔታ የተረዳ ሁሉ መፍትሔውን ለማወቅ ይጓጓልና። በመቀጠልም አንባቢ እየሆነ ያለውን ሁነት ከስር ከስር እየተከተለ ፍፃሜ ድረስ እንዲጓዝ ታሪኩን ያዋቀረበት ዘዴ ረድቶታል። ገፀባህሪው በተከታታይ የሚያጋጥሙትን ህይወት ሊያሳጡ የሚችሉ ከባድ ፈተናዎችን የሚያልፍባቸው ዘዴዎችም ታሪኩን ተነባቢ ሊያደርጉት የሚችሉ ናቸው። ትልሙን ጠንካራ ተያያዥነት ያለው ነው። ሆኖም የብልሁ ጠቋሪት ተግባር በበቂ ምክንያት ላይ የተመሰረተ ለማድረግ የቤተሰቦቹን ናፍቆትና ብቸኝነቱን የበለጠ ምናባዊ ማድረግ ይቻል ነበር። ወደ ጥንቸሎቹና ሚዳቆዎቹ ለመቅረብ የሚያደርገው አንድም ጥረት ሳይኖር "አላስጠጉትም" መባሉ ብቸኝነቱን የሚፈለገውን ያህል አላጠናከረውም። ብልሁ ጠቋሪት መጀመሪያ ጅቦችን ሸሽቶ ከዘመዶቹ ርቆ መሔዱ በኋላም ጅቦቹንም ሆነ ሌሎችን እንስሳት አታሎ ከቤተሰቦቹ መቀላቀሉ በልጆች ስነፅሁፍ ተፈላጊ ገፅታ ነው። ገፀባህሪው ከዚህ አንፃር አንዴ የመውጣት ሌላ ጊዜ ደግሞ የመውረድ ፊርቶ የመሸሽና ደፍሮ የማታለል ባህሪን የሚያሳይ በመሆኑ ተመራጭ የገፀባህሪ አሳሳል ተብሎ የሚገለፀውን ስልት ተከትሏል ለማለት ያስደፍራል። ከሀገር እስከ ወጣ ድረስ በፍርሀት የሸሻቸውን ጅቦች ደፍሮ ለመታገል ማሰቡ የገፀባህሪ አሳሳሉን ወጥነት የጎደለው የሚያስመስለው እንኳ ቢሆንም ከመነሻው የጅቦቹንና የሌሎች አውሬዎችን መኖር አውቆ የስነ ልቦና ዝግጅት አድርጎ መነሳቱ ለዚህ ጥርጣሬ ምላሽ ያስገኝ ነው።

ይሁን እንጂ ታሪኩን የበለጠ አስደናቂ ለማድረግ የተደረገው ጥረት ውስን ነው። ልብን በመስቀል የአንባቢውን ቀልብ ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ልብ ስቃይ ሂደትን ማለፍ የሚኖርባቸው ተግባራት በአጭሩ ተገልፀዋል ለምሳሌ "ለማንኛውም ማደሪያ ቦታ እንስጠውና ይተኛ። እንቅልፍ ሲወስደው ጠብቀን ዘርጥጠን እንበላዋለን ብለው ተማከሩ" (ገፅ 22)። ተኩላዎቹ ብልሁ ጠቋሪትን እንዴት እንደሚበሉት ቢያቅዱ፣ ከዚህ የበዙ ሀሳቦችን ቢለዋወጡ ሁኔታው የተከናወነ ያህል አንባቢን ያንጠለጥል ግጭቱንም በተሻለ ሁኔታ ያከረው ነበር። አሁን ግን በሁለት አረፍተ ነገሮች የተገለፀው ይህ ማእከላዊ የግጭት ስፍራ የሚፈልገውን ያህል የናረ አልሆነም።

ሆኖም አወቃቀሩ በመጨረሻ የተገኘውን እፎይታ ዋጋ ትልቅ ያደርገዋል። ምክንያቱም ብልሁ ጠቋሪት ከዝንጀሮዎች፣ ከተኩላዎችና ከጅቦች አምልጦ ከዘመዶቹ መቀላቀሉ በግጭቱ ወቅት መጣ ሔድ ሲል ለነበረው ልብ አንጠልጣይ ጉዳይ ማለፊያ መቋጫ የሚያበጅለት ሆኗል።

በሌላ በኩል ጥቅም ላይ የዋሉት ቃላት ተዘውትረው ለዕሁፍ አገልግሎት የሚውሉ በተለይም በከተሞች አካባቢ በእለት ከእለት ተግባቦት መጠቀሚያ ናቸው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ተቃራኒ ቃላት አግባብ ባልሆነ መልክ በዕሁፉ ውስጥ ገብተው ይታያሉ።

"እንዴት ዋላችሁ ሲል በትህትናና በኩራት ሰላምታ አቀረበላቸው" (ገፅ 28)። ትህትና ካለ ኩራት እንደምን ይኖራል? እንዴትስ በአንድ ጊዜ ትሁትና ኩሩ መሆን ይቻላል። በትህትና ከሆነ በትህትና በኩራት ከሆነም በኩራት እንጂ በትህትናና በኩራት ሰላምታ ማቅረብ አይቻልም።

በዚህ የህፃናት መፅሀፍ ላይ የሀሳብ ችግርም ይታይበታል። ለምሳሌ በመፅሀፉ ገፅ 1 ላይ ጠቋሪት ይኖርበት በነበረው ጎልብማ አካባቢ የዱር እንስሳት በብዛት አይታዩም ምክንያቱ ደግሞ አካባቢው የአዳኞች መኖሪያ መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ በዛው ገፅ ላይ ጥንቸሎችና ሚዳቆዎች እንደሚኖሩ ይጠቁማል። ይህ አንድም ሚዳቆዎችን የቤት እንስሳት ያስመስላል፤ ሌላም አዳኞች ሚዳቆና ጥንቸልን አያድኑም የሚል ትርጉም ይሰጣል። በሀገራችን ደግሞ አዳኞች ቢያንስ ሚዳቆን ለምግብነት እንደሚያድኗት የታወቀ ነው። በመሆኑም እንዲህ አይነት ሀሳቦች አንድም በታሪኩ ላይ ተፅዕኖ በማይፈጥሩ ሁኔታ ምክንያት ቢፈለግላቸው፣ አልያም መግባታቸው ብዙ ጥቅም ስለሌለው በታሪኩ ውስጥ ባይገቡ ይሻል ነበር። ካልሆነ ግን ደራሲው በዘመናዊ ፋንታሲ ለታሪኩ ሲል ያበጀውን ህጋጋት ማክበር አለበት የሚለውን መስፈርት የሚፃረርና የታሪኩን የመታመን አቅም የሚፈታተን ይሆናል።

ለሚገጥሙ ችግሮች በብልሀት መፍትሄ መፈለግ ያሰቡበት ቦታ ለመድረስ በርካታ ፈተና ማለፍ ግድ መሆኑን ያሳያል። ይህ ድርሰት ማታለልን፣ ማስመሰልን፣ ያልሰሩትን ሰራሁ ብሎ መሸለምን ያበረታታ ይሆን የሚል ስጋትም የሚያሳድር ነው። ምክንያቱም ብልሁ ጠቋሪት ያልገደለውን ገደልኩ እያለ በአውሬዎች መፈራትንና መከበርን አትርፏልና ህፃናቱ አሉታዊ በሆነ መንገድ የዋናውን ገፀባህሪ ድርጊት ሲረዱት ስለሚችሉ ሊተላለፍ ከተፈለገው መልዕክት ውጪ የሆነ ሀሳብ ይዞላቸው ቀርቧል ሊባል ይችላል።

## 3.2 ቱሲ እና ቹኪ

መፅሐፉን ከመተንተኔ በፊት ታሪኩን በሚከተለው መልክ በአጭሩ አቅርቤያለሁ "ቱሲ እና ቹኪ" በሚል ርዕስ የተፃፈው ይህ የህፃናት መፅሀፍ የእንስሳት ታሪክ ነው። ቹኪ የምትባል አይጥ ቱሲ የሚባል ልጅ አላት። ቱሲ ብዙ ማወቅ የሚፈልግ በመሆኑ እናቱን በርካታ ጥያቄዎች ይጠይቃታል። እናትየው ምንም እንኳን በጥያቄው መሰልቸቷን ብትገልዕለትም ለእያንዳንዱ

ጥያቄ ተገቢውን መልስ በመስጠት በአንድ በኩል የልጇን የማወቅ ፍላጎት ለማሟላት በሌላ በኩል ደግሞ ለልጇ ጠቃሚ ምክሮችን ለመለገስ ጥረት ታደርጋለች። ትንሽ በመሆኑም ከጉድጓድ እንዳይወጣ ትመክረዋለች ምክሯን ባለመቀበል ከመውጣቱ አሞራ በጥፍሮቹ ይዞት በረረ። ከዛም ከደረቅ እንጨት ላይ ተቀምጦ ሊበላው ሲል እናቱ ደርሳ ልጇን ከሚበላ እርሷን ቢበላ እንደሚጠቀም አግባብታ ልጇን አስለቅቃ እራሷን ለመስዋትነት አዘጋጀች። በቹኪም ሀሳብ የተስማማው አሞራ ቱሲን ለቆ ትልቋን አይጥ ለመብላት ቋመጠ። ትንሹንም አይጥ ለቀቀ። ልጇ እንደተለቀቀላት ያየችው እናትም ዘላ ወደጉድጓድ በመግባት እሷም አመለጠች፤ ልጇንም አስለቀቀች። ጭልፊቱም በመታለሉ እየተቆጨ ሌላ ምግብ ፍለጋ በረረ።

ትልሙ ተያያዥነት ይጎድለዋል፤ አጫጭር ታሪኮች በአንድ የተሰበሰቡ ስለሚመስሉ ጠንካራ ትልም የለውም፡፡ በፈጣን ምክንያትና ውጤት ወደግጭት ከመሔድ ይልቅ ረዥሙን የታሪክ ክፍል ውይይት ይወስደዋል፡፡ ውጥረቱን ተያያዥ የማድረግ ችግር አለበት፡፡ ግጭቱ ወደ ንረት የሄደበት መንገድም አንባቢን የሚያጓጓ አይደለም፡፡ ዶሮ መስሎት ሊያየው የተጠጋው አሞራ በጥፍሩ እንቅ አድርጎ ሲወስደው የከረረው ይህ ግጭት እናቱ ባመጣችው መላ ይረግባል፡፡ይህም ድንገታዊ እንጂ አነባቢን ይዞ ለመቆየት በሚያስችል መልኩ የተዋቀረ አይደለም፡፡ ቀለል ያሉ ቃላትን በመጠቀሙ ህፃናት አንባቢያኑ በቀላሉ ሊረዱት ይችላሉ፡፡

የቱሲ አካላዊና ህሊናዊ ሁኔታ በውል ተገልጿል። "ቱሲ ከተወለደ ሰባት ሳምንት ሆነው፡፡ ንቁ ስለሆነ ሁሉንም ነገር ማወቅ ይፈልጋል . . . ቱሲ ቀጫጫና ገና ትንሽ ቢሆንም ብዙ ነገር ማወቅ ያምረዋል . . . እንደትንሽነቱ ሳይሆን በሰውነቱ በጣም ጠንካራ ነው" (ገፅ 3)፡፡ የሚሉና ሌሎችም የቱሲን ባህሪና አቋም የሚያሳዩ አገላለፆች በመፅሐፉ ውስጥ በስፋት ይታያሉ በዚህም ምክንያት የቱሲ አካላዊና ህሊናዊ ማንነት ለማወቅ አንባቢው አይቸገርም፡፡

ይሁን እንጂ ቱሲ የሚኖርበት አካባቢ አልተገለፀም፡፡ ምንም እንኳን በህፃናት ስነፅሁፍ የመቼት ገለፃ በመጠኑ ሊሆን ይገባል ቢባልም በተለይ በዘመናዊ ፋንታሲ አፃፃፍ ውስጥ ለታሪኮቹ ያልተለመደ አይነት አለም መፍጠር ወይም የእውነቱን አለም በምናቡ ከፈጠረው ጋር በማዛመድ ማቅረብና አንባቢን ወደዚያ ወደተፈጠረው አለም ይዞ የሚሔድ ገለፃ መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ሁልጊዜ አይጥ በሚኖርበት ጉድጓድ ውስጥ ታሪኩ እንዲፈፀም አድርጎ አይጡን ተናጋሪና አሳቢ ማድረግ በታሪኩ ላይ የእውነተኛነት ጥያቄ ያስነሳል፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ ያለው መቼት ከዚህ የተለየ አይደለም ቱሲና ቹኪ በጉድጓድ የሚኖሩ

መደበኛ አይጦች ናቸው ነገር ግን በስፋት ሲወያዩ ይሰማሉ፡፡በውይይት ሀሳቦች ይለዋወጣሉ፡፡ ከላይ የተገለፀው የቱሲ ሁሉን ነገር የማወቅ ፍላጎት በውይይታቸው ወቅት ጎልቶ ይታያል፡፡ ደራሲው የእናትን ምክር አለመስማት የሚያስከትለውን ችግር ትኩረት በሚስብና ቀለል ባለ መንገድ አቅርቧል፡፡ ህፃናቱ ይህንን መልዕክት ለመረዳት እንዲችሉ በእናትና በልጅ ውይይት መልክ መቅረቡ ተገቢ ነው፡፡ ይሁንና ትልሙን ሲጫነው ታይቷል ለዚህም ነው ውጥረቱ ተያይዞ ማደግ ያልቻለው፡፡

## 3.3 የአንቺነሽ ተስፋ

"የአንቺነሽ ተስፋ" በሚል ርዕስ የተፃፈው ታሪክ በአጭሩ ይህንን ይመስላል፤ ከደብረማርቆስ ከተማ በእግር ከሦስት ሰዓት በላይ በሚያስኬደው ለምለምና የትጉህን ገበሬዎች መኖሪያ በሆነው ስፍራ የሚኖሩ አይዋ አለሙና እመት አልጣሽ የሚባሉ ባልና ሚስት አንቺነሽ የምትባል የአስር አመት ልጅ አላቸው። አንቺነሽ ከከተማ የምትኖር አክስት ስለነበራት ከሰፈሯ ልጆች ተለይታ ትምህርት ቤት ገብታለች የእሷ እኩዮች ግን ተድረው ስለነበር አንቺነሽን "ቆሞ ቀር" በመሆኗና "አስኳላ" (ት/ቤት) በመግባቷ ሸሽተዋታል።

በተማሪዎችና በወላጆች ፊት ቴያትር ለማሳየትና ዘፈን ለመዘፈን ትመረጣለች። በወላጆች ፊት ስለምታቀርባቸው ስለነዚህዝግጅቶች ስትጨነቅ ከቆየች በኋላ ወደ ጓሮ ዞር ብላ ሸንበቆ ተክል ውስጥ በመግባት የምታቀርበውን ዘፈንና የምትሰራውን ቴያትር ብቻዋን መለማመድ ትጀምራለች። አባቷ ለብቻዋ ስትነጋገር ሰምተው ጋኔን ይዟታል በማለት በአካባቢው ጋኔን ያስለቅቃሉ የሚባሉ ሰው ጠርተው በጅራፍ አስገርፈው፣ በጭስ አሳፍነው፣ በጋለ ብረት አስተኩሰዋት ለሞት ይዳርጓትና ታሪኩ በአሳዛኝ ሁኔታ ያበቃል።

በአንድ የገጠር ቀበሌ ውስጥ ከግንዛቤ ማነስ የተነሳ በሚፈጠር አግባብ ያልሆነ ተግባር በሰው ህይወት ላይ ስለደረሰው አደጋ የሚተርከው ይህ መፅሐፍ አንቺነሽ የተባለችው ህፃን ተስፋ በአጭሩ መቀጨቱን ያሳያል። መፅሐፉ በእውነታዊ ወቅታዊ ልብወለድ ውስጥ የሚመደብ ነው። ታሪኩ መግቢያ መሀልና መጨረሻ አለው። ተከታትሎ የሚሔድና ጠንካራ ትስስር ያለው ትልም ሲኖረው የግጭቱ ምክንያትም በገፀባህሪያቱ አሳሳል መሰረት ተቀባይነት ያለው ነው። በተጨማሪም እመት አልጣሽ በጋኔን የተነሳ የሞተባቸው ወንድም እንዳላቸው በታሪኩ ውስጥ መካተቱ ልጃቸውን ለማዳን የሚያደርጉትን መሯሯጥ አሳማኝ ያደርገዋል። የወንድማቸውን

አሟሟት "ባለሰባት ቀንድ ጋኔን ተብትቦት ነዋ ..." (ገፅ 8) በማለት ይገልፁታል ስለዚህ መምሬ ዘርጋውን ለመጥራት አያመነቱም። ልጃቸውን ለማዳን ቤተ ክርስቲያን ገብተው መፀለያቸውና አጠቃላይ የእናትየው ድርጊት ምስል ከሳች በሆኑ ቃላት የተሞላና በእውነተኛው አለም አንድ እናት ልታደርጋቸው የምትችላቸው ተግባራት ስለሆኑ ታሪኩን እውነተኛ ለማስመሰል የተደረገው ጥረት የተሳካ ነው ለማለት ያስደፍራል። ቴያትሩን ስትሞክር በርኩስ መንፈስ የተለከፈ ሰው የሚያደርገውን ድርጊት የምትፈፅም ስለመሰላቸው ግጭቱ ተከስቷል።

ግጭቱ በሁለት ተመጣጣኝ ወገኖች መካከል የተደረገ አይደለም። ባህላዊ እምነት ዘመናዊ ትምህርት ከሚጠይቃቸው ተግባራት የተወሰኑትን ሲጫናቸው ያሳያል። በዚህም ምክንያት ውጤቱ ሞት ይሆናል። የአንቺነሽ እናት፣ አባት፣ መምሬ ዘርጋውና ጎረቤቶች በአንድ በኩል ተሰልፈው በሌላ በኩል አንቺነሽ ያለምንም ረዳት መቆሟ ዘመናዊውን አስተሳሰብ ረዳት አልባ ያስመስለዋል። ግጭቱም ያለምንም ትግል በቀላሉ ወደ ንረት እንዲሔድም አድርጎታል።

በተለየ አቅጣጫ መፍትሔ ያገኛል ተብሎ የሚጠበቀው ታሪክ በአንቺነሽ ሞት መጠናቀቁ ድንገተኛ ነው። የአንባቢን ልብ በሀዘን ይዞ የሚቆይ በቶሎ ስሜቱ እንዳይጠፋ ተደርጎ የተሰራ ታሪክ ነው። የዚህ አይነቱ ታሪክ ደግሞ በህፃናቱ ላይ የደስታ ስሜት ከመፍጠር ይልቅ ሀዘን ውስጥ የሚከት ነው። መልዕክቱም ከህፃናት ይልቅ ለትላልቆች ይመስላል። ማህበራዊ ሂስ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ከህፃናት አእምሮ በላይ ይሆናል የሚል ስጋት ያሳድራል።

ድርጊት አመልካች ቃላቱ ምስል ከሳች የሚባሉ አይነቶች ናቸው ". . . ጆርባዋን በአለንጋ ገለጡዋትና በአስፈሪ ሁኔታ አይናቸውን አፈጠጡባት፤ ሥጋን ሰርስሮ አጥንት ድረስ ዘልቆ የሚሰማ አለንጋቸውን አሳረፉባት" (ገፅ 28)። አንባቢ የግርፋቷ መጠን ይሰማዋል ፣የመምሬ አስፈሪ አይኖችም ያስደነግጡታል። እናም ድርጊትን በሚያመለክቱ ቃላት የተሻለ አጠቃቀም አሳይቷል ልንል እንችላለን፡፡ "ያንን ረጅም አለንጋ ወንጭፈው አንገቷ ላይ ጠመጠሙባት አንቺነሽ በስቃይ አቃተተች" (ገፅ 29) የሚለውም ተጨማሪ ምሳሌ ይሆናል። በገፀባህሪያት ገለፃ ላይ ዋናዋ ባለታሪክ በውል አልተገለፀችም። አንቺነሽ ማናት? ለሚለው ጥያቄ የ10 ዓመት ልጅ ከሚለው መልስ በስተቀር ምንም አይነት አካላዊም ሀሲናዊም ገለፃ አልተደረገም ስለዚህ ገፀባህሪዋን በአግባቡ ለማወቅ ይቸግራል። ከሷ ይልቅ ስለ መምሬ ዘርጋው የተሻለ አካላዊም ሆነ ሀሲናዊ ገለፃ ተሰጥቷል። መምሬ ቁመታቸው አጭር ፣ፊታቸው ላይ የሚያስጠላ ጠባሳ ያለባቸው፣ አጎዛ ከትከሻቸው ላይ የሚለብሱ (ገፅ 13)፣ ጨካኝ (ገፅ 29) ቁጡ፣ አስቀያሚ ጥርስ

ያላቸው (ገፅ 30) የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። አንባቢያን በአግባቡ የተሳለላቸውንና የተገለፀላቸውን አቀንቃኝ ገፀባህሪ በተሻለ ሁኔታ ይረዱታል። በተሻለ መንገድም ይቀርቡታል፣ ሀዘኑ ይሰማቸዋል፣ ደስታው ይጋባባቸዋል፣ ውድቀቱን ውድቀታቸው አድርገው ይቆረቆሩለታል። እድገቱንም እንደእድገታቸው ቆጥረው ይፈነድቁለታል እንደዛ ተደርጎ ካልተሳለና ካልተገለፀ ግን በታሪኩ አማካይነት ሊተላለፍ የሚገባውን መልዕክት ሙሉ በሙሉ ማስተላለፍ የማይቻልበት ሁኔታ ይከሰታል።

አንዳንድ ባህላዊ ድርጊቶች በማህበረሰቡ ላይ የሚያደርሱትን አስከፊ ሁኔታ ማሳየት የደራሲው ዋነኛ ዓላማ ነው። የተላለፈበት መንገድ ፍፁም አሳዛኝ በመሆኑም አብዛኛውን የዚህን መፅሀፍ አንባቢ የችግሩን አስከፊነት ሊረዳ በሚችል መልኩ ታሪኩን አዋቅሮታል። በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ሌላው ጉዳይ የቃላት አጠቃቀም ነው። በከተማ አካባቢ ተዘውትረው ጥቅም ላይ የማይውሉ ቃላት በታሪኩ ውስጥ ይገኛሉ። ምናልባትም ደራሲው መፃሕፍት ውስጥ እንግዳ ቃላትን በማካተት የህፃናቱን የቃላት እውቀት ማሳደግ የሚለው አስተሳሰብ አራማጅ ይሆናል የሚል ግምት አሳድሯል "እኔ ምን አውጬ" (ገፅ 9) "ቀን" ፊደል እንደ "ጨ" እንደሚጠሩ ማብራሪያ የተሰጠበት የዘዬ ቃል ነው። በርካታ ተዘውታሪ ያልሆኑ እንግዳ ቃላት፣ በአንድ አካባቢ ብቻ በስፋት የሚነገሩ ቃላት በመፅሀፉ ውስጥ በስፋት ይገኛሉ። "ምንሜናው" "ችምግ" የሚሉት ቃላትም በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

## 3.4 የአሰለፈች ሎሚዎች

በእውነታዊ ታሪካዊ ልብወለድ መልክ የተፃፈውና "የአሰለፈች ሎሚዎች" የሚል ርዕስ ያለው ይህ መፅሐፍ አሰለፈች የተባለች ህፃንን ታሪክ ይተርካል። ታሪኩ በአጭሩ ሲቀርብም የሚከተለውን ይመስላል።

የአሰለፈች አባት አቶ ደስታ እናቷ ደግሞ ወ/ሮ ስፈልግ ይባሉ ነበር። አነስተኛ ገቢ በሚያስገኝ ስራ የሚተዳደሩ ቢሆንም ልጃቸውን ለማሳደግ በየበኩላቸው ይተጋሉ። ይሁን እንጂ አባቷን አልፎ አልፎ ያማቸው ነበር። ቀስ እያለም ህመማቸው ፀና። ለሦስት ዓመታት የአልጋ ቁራኛ ሆኑ። እናቷ በአንድ በኩል ለኑሮአቸው በሌላ በኩል ለአባቷ ማስታመሚያ የሚሆን ገቢ የሚያስገኝ ስራ እየሰሩ አባቷን አስታመሙ። እሷንም አስተማሩ። የአባቷ ህመም እየፀና መጥቶ በመጨረሻ በማይቀረው ሞት ተወሰዱ። እናቷ ከአባቷ ሞት በኋላ ጤና አላገኙም። ለስድስት

ወራት አልጋ ይዘው ቆዩ። የእነ አሰለፍ ቤት ገቢ ቆመ፣ የሚላስ የሚቀመስ ጠፋ በአንድ በኩል በሽታ በሌላ በኩል ርሀብና ችግር የደቆሳቸው የአሰለፍ እናት ባላቸው በሞቱ በስድስት ወራቸው ተከተሏቸው። ከእናቷ ሞት በኋላ አሰለፍ ከአንድ መነኩሲት ጋር ተጠግታ መኖር ጀምራለች ለእለት መተዳደሪያም ሎሚና ጨሌ (ለጉዝጓዝ የሚሆን ሳር) እየሸጠች ገቢ ታገኛለች። ትምህርቷን አቋማለች። ከሎሚ ደንበኞቿ ውስጥ ቅድስት የተባለችውን በእጅጉ እየቀረበቻት መጥታለች። ከእለት እለት ደንበኝነታቸው ወደ ቅርብ ጓደኝነት እየተቀየረ ነው። ቅድስት ትምህርት ቤት የሚወስዳት ታክሲ እስኪመጣ ድረስ ከአሰለፍ ጋር ትጫወታለች።

አንድ ቀን እንደ ልማዷ ከአሰለፍ ጋር ስትጫወት ቆይታ ለትምህርት ቤት የወር ክፍያ እንድትከፍል የተሰጣትን 100 ብር አሰለፍ ጋር ጥላ ሔደች። አሰለፍም ብሩን ሳንቲም ከምታስቀምጥበት ከረጢት ውስጥ አስቀምጣ ቅድስት ስትመጣ ሰጠቻት። ቅድስት በአሰለፍ ታማኝነት ከመደሰቷ በላይ አሰለፍ ቤተሰብ እንደሌላት ታውቅ ስለነበር ወላጆቿን በማሳመን አሰለፍ አብራቸው እንድትኖር ካደረገች በኋላ ታሪኩ ያበቃል።

በዚህ የህፃናት መፅሐፍ ውስጥ ድርጊቶች በቅደም ተከተል ተዘርዝረዋል። የታሪኩ መግቢያ መሀከል መደምደሚያ ጠንካራ ትስስር ያላቸው ከመሆኑም በላይ ሁነቶች ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ቀርበዋል። ትረካው በጠንካራ ግጭት የተዋቀረ ባይሆንም እንኳን የአሁኖቹ ሁነቶች ከቀደሙት ጋር ያላቸው ተቃርኖ ገፀባህሪዋን ከአንባቢ ጋር ለማስተዋወቅ ረድቷል። የታሪኳን ፍፃሜ ለማወቅ እንዲጓጓ በማድረግ ረገድ አብይ ሚና ተጫውቷል። ይህንን በምሳሌ ለማስረዳት "ቀደም ሲል አሰለፍ እያሉ የሚያቆላምጧት ወላጆችና ጓደኞች ነበሯት። ዛሬ ግን እያቆላመጠ የሚጠራት ጓደኛም ሆነ ወላጅ የላትም" (ገፅ 1-2) ሲል የብቸኝነቷ ነገር ፍፃሜው መቼ ነው የሚል ጉጉት ያጭራል። ገፀ ባህሪዋም በብቸኝነት የምትኖር መሆኗን ያስተዋውቃል። የታሪኩ ሁነቶች በጠንካራ ምክንያትና ውጤት የተሳሰሩ ናቸው። አሰለፊችን ቅድስት ወደ ቤቷ ወስዳ አብረው እንዲኖሩ የምትፈልገው ለአሰለፊች አዝና ብቻ ሳይሆን እህትና ወንድም ስለሌላት ነው። ይህ ደግሞ ምክንያታዊ ነው አሰለፊችም ከቅድስት ጋር ለመኖር የወሰነችው እናትና አባቷ ስለሞቱባት ነው። ሌሎችም ሁነቶች በዚህ አይነት ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የተገለፁ ናቸው።

ታሪኩ የተፈፀመበት ቦታም ተዘርዝሮ ተቀምጧል "ባህርዳር የአማራ ክልል ርዕስ መዲና የሆነች ውብ ከተማ ናት ጣና ለባህርዳር ከተማ የውበቷ ፈርጥ ነው አሰለፍ ትውልዷም ኑሮዋም በዚች ውብ ከተማ ነው" (ገፅ 1) ጊዜው ግን ተለይቶ አልተጠቀሰም። ዋናዋን ገፀባህሪ በማስተዋወቅና

ከሌላ ገፀባህሪ ጋር ለማወዳደር የተደረገው ጥረት የዋናውን ገፀባህሪ አካላዊ መልክ በተሻለ ለማወቅ ረድቷል። "አሰለፍ ቆንጆ ልብሶቿ የተቀደዱና መጫሚያ የሌላት ሳቂታ ልጅ ናት" (ገፅ 4)። በተጨማሪም ለኑሮዋ ታታሪና ታማኝ ስነምግባር ያላት መሆኗንም እንረዳለን።

ይሁን እንጂ በታሪኩ ውስጥ እየጎላ የሚሔደው የአሰለፈች (ዋና ገፀባህሪ) ተግባር ሳይሆን የአሰለፈች ጓደኛ የቅድስት መልካም ምግባር ነው። በመሆኑም ታሪኩ ዋናውን ገፀባህሪ በወጥነት ይዞ ከመጓዝ ይልቅ ቅድስትን እያጎላ በመሔድ የሚጠናቀቅ ነው። ይህም ህፃናቱ ታሪኩ የማን እንደሆነ በውል እንዳይለዩ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ታሪኩ ጠንካራ ስነምግባርን የማስተማር ዝንባሌ ያለው ሲሆን ዋናውን ታሪክ ሲጫነው ይታያል። በቀጥታ ታማኝ መሆን ያስፈልጋል ብሎ የመስበክ አዝማሚያ ይታይበታል። አድሎና መገለልን መአከላዊ ጭብጡ አድርጎ የተፃፈው ይህ ድርሰት ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ በኤችአይቪ/ኤድስ የተጎዱ ወገኖችን ማቅረብ መርዳት አስፈላጊ መሆኑን ነው የሚል መልዕክት ያስተላልፋል።

በታሪኩ ውስጥ የአሰለፈች አባት ከሦስት አመት በፊት በፅኑ ሕመም መሰቃየት የጀመሩ ሲሆን በዚህ ጊዜ አሰለፍ የሥድስት አመት ልጅ ነች። አባትየው ደግሞ ከበሽታቸው ፅናት የተነሳ ከአልጋ ላይ እንኳን በውል አልተነሱም (ገፅ 9) ይሁን እንጂ ወ/ሮ ስፈልግ (ባለቤታቸው) ግን በዚህን ጊዜ አንድ ልጅ ከዚህ ጊዜ በኋላ ሌላ ልጅ ወልደው ሞቶባቸዋል (ገፅ 15)። ይህ ሁኔታ ከእውነታ ጋር የሚፃረር ይመስላል ወ/ሮ ስፈልግ ባልየው እንደዚህ በታመሙበት ወቅት አርግዘው መውለዳቸው ታሪኩ የሚቀርበው ለህፃናት ነው ካልተባለ በስተቀር በአንባቢ ላይ ጥርጥር የሚያጭር ነው። ደራሲው የተጠቀመባቸው ቃላት ተዘውትረው ለመግባቢያነት የሚውሉ ቃላት ናቸው።

## 3.5 ካሳ

"ካሳ" የሚል ርዕስ ያለውን መፅሐፍ ከመተንተኔ በፊት ታሪኩን በአጭሩ ላቅርብ። "ካሳ" በሚል ርዕስ የታተመው ይህ ድርሰት የውጭ ሀገር ዜጎች ጥለውት ሄዳው ኢትዮጵያዊት እናት ስላሳደገችው ህፃን ይተርካል። የሰው ታሪክ የያዘ እውነታዊ ልብወለድ ነው።

የልጁ ወላጆች ሚሽነሪዎች ሆነው ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ላይ ባለ ገጠር ውስጥ ተመድበው ሲሰሩ ሽፍቶች ካሉበት ስፍራ ያባርሯቸዋል። ነፍሳቸውን ለማትረፍ ሲሸሹ ህፃኑን በተኛበት ጥለውት ይሄዳሉ። የህፃኑ ሞግዚት ደግሞ ህፃኑን ወደጫካ ይዛ በመሸሸ የህፃኑን ህይወት

ከሽፍቶቹ ታድናለች። ሚሽነሪዎቹ ጣልያናውያን ስለነበሩ ወደሀገራቸው ይሄዳሉ። እሷም ልጃቸውን ካሳ ብላ ስም ሰጥታ ታሳድገዋለች። ካሳ አሳዳጊውን (መአዛን) እናቱ እንደሆነች ነው የሚያውቀው። የመልኩ ቀለም ቢነጣም ሀበሻ መሆኑን ነው የሚረዳው። ልጆች በሰውነቱ ቀለም ሲያበሽቁት እናቱ ታፅናናዋለች። እሱ የሚሰድቡትን ልጆች ይደበድባቸዋል። ዋናው ስራው በግ መጠበቅ ነው። ጓደኞቹ ትምህርት ቤት ቢገቡም እናቱ ካሳን ወደትምህርት ቤት አልሰደደችውም። በዚህም ምክንያት ከጓደኞቹ ያነሰ ሆኖ ይሰማዋል።

ሚሽነሪዎቹ የሚሰሩበት ት/ቤት እና የሚኖሩበት ካምፕ ለሦስት አመት ተዘግቶ ከቆየ በኋላ ተከፍቶ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፤ ይሁን እንጂ የከሳ ወላጆች ዳግም አልመጡም። በሚሽነሪው ቅጥር ጊቢ ውስጥ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ የካሳ ሰፈር ልጆች ስለ ትምህርት ቤቱ ለካሳ ይነግሩት ስለነበር አንድ ቀን ትምህርት ቤቱን ለማየት ወደዛው ገሰገሰ። ትምህርት ቤት ሲደርስም አባ ኮንቲ የሚባሉ ፈረንጅ አገኙት ታሪኩን ነግረውት ወደ ጣሊያን እንዲሄድ ቢያግባቡትም እሱ ግን እናቱን ጥሎ ላለመሔድ ወስኖ እዚሁ ከእናቱ ጋራ ኑሮውን ይቀጥላል።

ይህ ድርሰት ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ የታሪኩን ሁነቶች በቅደም ተከተል አስቀምጧል። ካሳ አሁን ወዳለበት ሁኔታ እንዴት እንደመጣ ታሪኩን ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ተርኳል። በዚህም ህፃናት አንባቢያን በቀላሉ ታሪኩን እንዲረዱት የሚያስችል ስልት ተጠቅሟል ማለት ይቻላል። ትልሙም ተያያዥ እንዲሆንና ውጤቱም በአሳማኝ ምክንያት እተደገፈ ታሪኩ እንዲቀጥል ረድቷል።ለምሳሌ የካሳ ጓደኞች ስለ ትምህርት ቤት የነገሩት ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄድ ገፋፍቶታል ፤በዛም አባ ኮንቲን ለመገኘት፤ ችሏል እሳቸው የነገሩት ታሪክ በውስጡ ለሚፈጠረው ግጭት ምክንያት ሆኗል፤ ይህ ደግሞ ስለ ራሱ እውነቱን እንዲወቅ ረድቶታል፤ እውነቱን ማወቁም በውስጡ የተፈጠረው ግጭት እረፍት እንዲያገኝ አስችሏል።

በዚህ ታሪክ ውስጥ ሰው ከራሱ እና ከሌሎች ጋር ግጭት ውስጥ ሲገባ ይታያል ካሳ በቀለሙ ምክንያት ከጓደኞቹ ጋር ሲጋጭ ደራሲው በግልፅ ያመለከተ ሲሆን አባ ኮንቱ ለካሳ በነገሩት ታሪክ ምክንያት ካሳ የማንነት ጥያቄ በውስጡ ተፈጥሮ በሁለት ሀሳብ ሲያመነታ ይታያል። በአንድ በኩል ሀብታም የተባሉ ቤተሰቦቹን ለማግኘት ወደ ሮም በመሄድ፣ በሌላ በኩል እናቱ ከሚላት ከአሳዳጊው ጋር አገሩ ላይ በመቅረት ሀሳብ ሲምታታ ታይቷል።

ከጓደኞቹ ጋር የሚገባበት ግጭት እርሱ በሚወስደው ርምጃ እየሰከነ ሲሄድ፣ ከራሱ ጋር ከገባበት ግጭት ለመውጣት ግን ጊዜ ወስዶበታል። በመጨረሻም አሁን ያለውን ማንነቱን ተቀብሎ

በአበሻነቱ ተማምኖ ከእናቱ ጋር ለመኖር የወሰነው ውሳኔ አሸንፏል። አንባቢዎቹን ምን ይወስን ይሆን ብለው ልባቸው እንዲንጠለጠል በተለይ ከራሱ ጋር የገባበት ግጭት ትልቅ አስተዋፅኦ ነበረው።

የካሳ ዋነኛ ሥራው በግ ማገድ ነው። እናቱ በጨቅላነቱ የሞተችበትን የበግ ግልገል ወደ ሌላ እናት በግ በመውሰድ እንዲጠባ በማድረግ የግልገሉን ህይወት አትርፏል። ከዚህም ሌላ ያቺ በግ ግልገሉን እንደልጇ ስትንከባከበውም አይቷል። ይህንን በእንስሳቱ ላይ የተመለከተውን ሁኔታ በምሳሌነት በመውሰድ የራሱን ህይወት አነጻፅሮበታል። በዚህም ኑሮውን ካልወለደችው ግን እንደ እናት ካሳደገችው ሞግዚቱ ጋር ለማድረግ ወስኗል። ይህ ተምሳሌታዊ አገላለፅ ታሪኩን አሳማኝ ለማድረግ በጎ አስተዋፅኦ አለው። በካሳ ውስጥ የተፈጠረው ግጭትም አሳማኝ በሚመስል መንገድ እንዲጠናቀቅም ረድቷል። ሆኖም ሃሳቡን አንባቢያኑ የመረዳታቸው ነገር ያጠራጥራል። ተምሳሌትን የመተርጎም ብቃት ይጠይቃቸው ይሆናል።

የዋናው ገፀባህሪ አካላዊ መልክም በውል ተገልጿል፡፡ "አቤት ቅላቱ፡ አፍንጫው ሰልካካ ፀጉሩ ሉጫ አይኖቹ፡ ትልልቅ . . . (ገፅ 4)፡፡ የሚያበሽቁትን ልጆችም በመደብደብ ሀይለኛነቱን አሳይቷል (ገፅ 3) እድሜው 12 ዓመት ሲሆነው ስራውም እረኝነት ነው " (ገፅ 4)፡፡ ይሁን እንጂ የልጆች እጅና እግር እስከመስበር ድረስ ድብደባ ማካሄድና ያም ድርጊቱ በሌሎች መፈራትን ያስገኘለት መሆኑ መገለፁ ለአንባቢ ህፃናቱ የሚያስተላልፈው መልዕክት ገንቢ አይደለም፡፡ ቢያንስ ለዚህ ተግባሩ ቅጣት ይገባው ነበር፡፡ ይህም ተግባሩ ስህተት መሆኑንም ለማስተማር ይጠቅም ነበር፡፡

ታሪኩ የተከናወነበት ቦታ ከአዲስ አበባ ቅርብ ርቀት ላይ ያለች ከዋናው መንገድ ተገንጥላ የምትገኝ መንደር ናት ሆኖም በአዲስ አበባ በየትኛው አቅጣጫ ለሚለው ጥያቄ በቂ መልስ የለውም በዚህም የታሪኩ ስፍራ በተሟላ ሁኔታ ተገልጿል ማለት አይቻልም፡፡

የቃላት አጠቃቀሙ አብዛኛው የቋንቋ ተናጋሪ ያለችግር ሊረዳው የሚችል ነው፡፡ በዚህ ታሪክ አማካኝነት የቀለም ልዩነት አብሮ ለመኖርም ሆነ ማንነትን ለመወሰን ምንም አይነት አሉታዊ ተፅእኖ እንደሌለው ሰው በቀለሙ ምክንያት መለያየት እንደሌለበት የሚያስተምር ነው፡፡

በታሪኩ ውስጥ አብዝቶ የሚታየው ገለፃ ድርጊትን ለማሳየት ከመሞከር ይልቅ የሚተርክ ነው ስለዚህም ድርሰቱ ምስል የመከሰት አቅሙ አነስተኛ ነው፡፡ "ቀዩ፣ ሊጥ፣ ፈረንጁ እያሉ ያበሽቁት ነበር . . . እንደሱ ሲሉት በዱላም በቦክስም መማታት ጀመረ" (ገፅ 3) እነሱ ሲያበሽቁት እሱም ሲደባደብ በማሳየት የበለጠ የሚታይ ማድረግ ይቻል ነበር፡፡

## 3.6 ሊንቻ እና ቢንቻ

ትንታኔውን ከመጀመሬ በፊት የመፅሐፉን ታሪክ በአጭሩ ላቅርብ፡፡ ታሪኩ ዘመናዊ ፋንታሲ ከሚባሉት ተርታ የሚመደብ የእንስሳት ታሪክ ነው፡፡ገጸኞቹ ሊንቻና ቢንቻ በሚኖሩበት ከተማ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ንብረት በማጥፋት ይታወቃሉ፡፡ ሊንቻ ሆዱ እንዳይጎድል የምትፈልግ ሁል ጊዜ ምግብ በመፈለግ ላይ የተሰማራች ሴት አይጥ ስትሆን ቢንቻ ግን ሰነፍና እንቅልፋም ወንድ አይጥ ነው፡፡ በአንድ የክረምት ወቅት ሁለቱ አይጦች ያገኙትን ትኩስ ዳቦ መብላት ሲጀምሩ የዳቦው ጋጋሪ ደርሶባቸው ሊገላቸው ነበር፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ በአትክልት መሸጫ ሱቅ ውስጥ ቢንቻ ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ ቲማቲም ለመብላት ባደረገው ሙከራ የአትክልት ቤቷ ባለቤት ነቅታ ልትገላቸው ነበር፡፡ ቢንቻ በመፃህፍት ቤት ውስጥ የተጠመደ ወጥመድ ጭራውን ስለቆረጠው በእጅጉ አዘነ፡፡ ከሊንቻም ጋር በዚሁ የተነሳ ተኮራረፈ ሆኖም ጥፋተኛ ራሱ ስለነበር ሽማግሌ ልኮ ሊንቻን ታረቃት፡፡

እነሱ በሚኖሩበት ከተማ ያሉ ሰዎች ሰርግ እንደሚደግሱ በሰሙበት እለት ሊንቻና ቢንቻም ሊጋቡ ወሰኑ ሰርጋቸውንም ሰዎቹ በሚጋቡበት እለት ለማድረግ ቀን ቆረጡ፡፡ በሰርጉ እለት ሊንቻና ቢንቻ ከነአጃቢዎቻቸው በሰዎች ቤት ገብተው ያገኙትን ሁሉ ሲበሉ ቆዩ ቢንቻ ግን መጠጥ ልጠጣ ብሎ አስቸገረ ሙሽራዋ ሊንቻ ብትመከረውም አሻፈረኝ አለ፡፡ መጠጡን ጠጥቶ ሰከረ፤ ከዚያም በተቆረጠ እንጀራ መሀል ገብቶ ተኛ፤ እንቅልፍም ወሰደው፡፡ የቤቱ ባለቤቶች አይጦች በምግቡ ስለተጫወቱበት በእጅጉ ተቆጡ፡፡ በተቆረጠ እንጀራ መሀል ቢንቻን ስላገኙት ገለው ጣሉት፡፡

ትንታኔው በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡ ትልሙ ተከታታይ ከመምሰል ይልቅ የተለያዩ ታሪኮች የተገጣጠሙ ይመስላል፡፡ አንድ ቀን የዳቦ ቤት ታሪክ፣ ሌላ ቀን አትክልት ቤት ታሪክ፣ በሌላ ቀን ደግሞ የመፅሐፍት ቤቱ ታሪኮች በመጨረሻም በሰርግ ቤቱ የተፈፀመው ድርጊት ጠንካራ ትስስር የላቸውም የተለያዩ ታሪኮች ተገጣጥመው የቀረቡ ይመስላል በድርጊት ሳይሆን በዘገባ መልክ የቀረበ ነው፡፡ግጭቱም በአግባቡ ሲንር አይታይም፡፡

አንባቢን ከታሪኩ ጋር ለማስኬድ ታሪኩን ምናባዊ ከማድረግ ይልቅ በዘገባ መልክ በመቅረቡ የአሰልቺነት ባህሪ ታይቶበታል፡፡

የታሪኩ ባለቤቶች አካላዊና ህሊናዊ ሁኔታ ተገልጿል፡፡ ሊንቻ ብልጣብልጥ እና ድንቡጭ ያለች ጓደኛዋ ቢንቻ ደግሞ ኮሳሳ እና ገራገር ብጤ ነው (ገፅ1)፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን ሰነፍ፣ እንቅልፋም፣ ሆዳም በሚሉ ቃላት የገፀባህሪያቱ ሁኔታ ተገልጿል፡፡ ይህ ደግሞ አንባቢ የገፀባህሪያቱን ማንነት በማወቅ በታሪኩ ውስጥ የሚፈፅሙት ተግባር ምክንያታዊ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ገራገሩ ቢንቻ ደጋግሞ አደጋ ይደርስበታል፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ ከባህሪው በመነሳት ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረጉ ነው፡፡ ታሪኩ የተፈፀመበት ስፍራ ገለፃ በባህላዊ ተረቶች ተዘውትሮ የሚታየው ዓይነት ነው፡፡ በፈጠራ የልጆች ሥነፅሁፍ ውስጥ በተለይ በዘመናዊ ፋንታሲ መቼት ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ በአግባቡ ቢገለፅ ታሪኩ በአንባቢያን ዘንድ ያለው ተቀባይነት እንዲጨምር አስተዋፅኦው የጎላ ነው፡፡ሆኖም በዚህ ድርሰት መቼቱ በአግባቡ ተገልጿል ለማለት አይቻልም፡፡ሊንቻ እና ቢንቻ በአንድ ከተማ ውስጥ ከመኖራቸው የዘለለ ምንም አየነት ገለፃ አይታም፡፡

ታሪኩ ጎበዝ ንቁና ሁሌም ጠንቃቃ መሆን አስፈላጊ ነው የሚል መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ መልካም ምክርን አለመቀበልም መስዋትነት ሊያስከፍል እንደሚችል፣ አደጋንም የሚጋብዝ ነገር ከማድረግ ዘወትር መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባል።ይህ ደግሞ ለህፃናት ተገቢ ነው ከሚባሉት መልእክቶች መካከል ይመደባል።

በድርጊት አመልካች ቃላት አጠቃቀም በኩልም የተሟላ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ "ቢንቻ በዚህ አደጋ የደሃ ጭራውን በማጣቱ ምርር ብሎ ያለቅስ ጀመር" (ገፅ 11)፡፡ የህመሙን መጠን፣ በአደጋው ወቅት የተሰማውን ስሜት፣ ስቃዩን፣ የደሙን ብዛት፣ ጭራውን በማጣቱ የሚያጋጥመው ችግር ቢገለፅ አንባቢን ከታሪኩና ከባለታሪኩ ጋር የበለጠ ለማቀራረብ ይረዳ ነበር፡፡ ይህ ባለመሆኑ ከገፀባህሪያቱ ጋር ያለው የአንባቢ ቁርኝት የጠበቀ እንዲሆን አላስቻለም፡፡

# 4. ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎችና ምላሾቻቸው

ለተማሪዎች የተበተነው መጠይቅ ሦስት ክፍሎች ያሉት ነው፡፡ የመጀመሪያው የመላሾቹ ግላዊ መረጃ የሚሰበሰብበት ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል በተነበበው ታሪክ ላይ ተመስርቶ ተማሪዎቹ ጠቅለል ያለ መልስ የሚሰጡባቸው ዝግ ጥያቄዎችን የያዘ ክፍል ነው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ አስር ጥያቄዎች በአንባቢያን ይመለሱ ዘንድ በመጠይቁ ሰፍረዋል፡፡ በሦስተኛው ክፍል የተማሪዎቹን የንባብ ልምድና ፍላጎት ለማወቅ የሚረዱ ሁለት ክፍት ጥያቄዎች ተካተዋል፡፡ አንዱ የተማሪዎቹን የቀደመ የንባብ ልምድ ሌላኛውም ለማንበብ የሚፈልጓቸውን የመፃህፍት ዓይነቶች ለማወቅ ይረዳሉ ተብለው የቀረቡ ናቸው፡፡

## 4.1. የመላሾች ግላዊ መረጃ

ከላይ እንደተገለጸው በዚህ ክፍል የቀረቡ ጥያቄዎች የተማሪዎቹን እድሜ፣ ጾታና የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲሁም የሚማሩበትን ትምህርት ቤት ለማወቅ የሚረዱ ጥያቄዎችን የያዙ ናቸዉ፡፡ የእነዚህ ጥያቄዎች አላማም የመላሾች ግላዊ ሁኔታ በሚሰጡት መልስ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል በሚል ሃሳብ ነው፡፡ በተጨማሪ የእነዚህ ጥያቄዎች አላማ የመላሾዎቹን ቋንቋና እድሜ መቀራረብ ለመፈተሽና የጾታ ስብጥሩን ለማወቅ ነው፡፡ በዚህም በእድሜ አብዝቶ መለያየት ሳቢያ የሚከሰተውንም ሆነ በቋንቋ ችግር ምክንያት ሊያጋጥም የሚችለው ችግር ከወዲሁ ከግምት ውስጥ ለማስገባት ጥያቄዎቹ አይነተኛ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል፡፡

ሰንጠረዥ 1 የመላሾቹ ግላዊ መረጃ

| ትምህርት ቤት | ጾታ | | ዕድሜ | | | | | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | 10 | 11 | 12 | 13 | 14-16 | አማርኛ | ኦሮምኛ | ትግርኛ | ጉራግኛ | ሌላ |
| አሳይ | 10 | 20 | 8 | 17 | 5 | | | 30 | | | | |
| አየር አምባ | 26 | 34 | 8 | 24 | 13 | 6 | 9 | 56 | 2 | | 2 | |
| ቦሌ ህብረተሰብ | 12 | 18 | 5 | 13 | 5 | 4 | 3 | 28 | 2 | | | |
| ነፃነት ብርሃን | 29 | 31 | 8 | 26 | 17 | 5 | 4 | 58 | 1 | 1 | | |
| ድምር ብዛት | 77 | 103 | 29 | 80 | 40 | 15 | 16 | 172 | 5 | 1 | 2 | |
| በመቶኛ | 42.8 | 57.2 | 16.1 | 44.4 | 22.2 | 8.3 | 8.9 | 95.5 | 2.7 | 0.6 | 1.1 | |

ሰንጠረዥ 1 በመጠይቁ ክፍል አንድ ውስጥ ለተጠየቁት አራት ጥያቄዎች በተማሪዎቹ የተሰጠውን ምላሽ የሚያመለክት ነው፡፡ ከተሰጠው ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው ከተመረጡት ተማሪዎች 77ቱ ወንዶች ሲሆኑ 103 የሚሆኑት ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ ይህም መረጃውን ካቀበሉት ውስጥ 42.8 በመቶው የሚሆኑት ወንዶች እንደሆኑና 57.2 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ሴቶች መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ የተካፈሉት ናሙናዎች በእጣ የተመረጡ ቢሆንም እንኳ የሴት ተማሪዎቹ ቁጥር ከወንዶቹ በልጢል ያም ሆኖ መረጃ አቀባዮቹ ከሁለቱም ጾታ የተውጣጡና ጥናቱም በአንድ ጾታ ላይ ብቻ ያተኮረ አለመሆኑ ከተማሪዎች ምላሽ መረዳት ይቻላል፡፡

የተማሪዎቹ እድሜ ከ10 ዓመት የሚጀምር ሲሆን አብዛኛዎቹ ተማሪዎችም በቁጥር 80 (44.4 በመቶ) የሚሆኑት እድሜያቸው 11 ዓመት መሆኑን በምላሻቸው አስታውቀዋል፡፡ 40 ተማሪዎች (22.2 በመቶ) የሚሆኑት ደግሞ 12 ዓመታቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ 29 ተማሪዎች (16.1 በመቶ) 10 ዓመት እድሜ ላይ ያሉ ሲሆን ከ14 እስከ 16 ዓመት እድሜ ያላቸው 16 ወይም 8.9 በመቶ የሚሆኑት ናቸው፡፡ 15 ተማሪዎችም (8.3 በመቶ) እድሜያቸው 13 ዓመት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ይህ መረጃ እንደሚያስረዳውም ሁሉም መረጃ አቀባዮች በአለም አቀፍ መስፈርት መሰረት ህፃን በሚባለው የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ መሆኑን ነው፡፡ 31 ተማሪዎች (17.2 በመቶ) የሚሆኑት ከ7 እስከ 12 ዓመት ከሚለው የህፃንነት ቡድን በላይ ናቸው፡፡ ሆኖም ከ80 በመቶው በላይ የሆኑት መረጃ አቀባዮች ከተመረጡት መፃህፍት ይዘትና ቅርፅ ጋር የሚመጣጠን እድሜ ላይ ያሉ መሆኑን የሰጡት ምላሽ ይጠቁማል፡፡ አብዛኛዎቹ መላሾች በትክክለኛ የእድሜ ወሰን ውስጥ ያሉ በመሆኑ ምላሻቸው በእድሜ ምክንያት የማይሰናከል መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

172 ወይም (95.6 በመቶ) የሚሆኑት መረጃ አቀባዮች አፋቸውን የፈቱት በአማርኛ ቋንቋ ሲሆን ስምንቱ (4.4 በመቶ) በሌሎች የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች አፋቸውን መፍታታቸውን በሰጡት ምላሽ አመልክተዋል፡፡ ይህም አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የተፃፈ ታሪክ ለማንበብም ይሁን ለማዳመጥ ቋንቋውን ባለመቻላቸው ምክንያት የሚያጋጥማቸው ችግር የለም ብሎ ለመናገር የሚያስችል ነው፡፡

በአጠቃላይ በክፍል አንድ ውስጥ ከቀረቡት ጥያቄዎችና ከተሰጡት ምላሾች ምንም እንኳ የቁጥር ልዩነት ቢኖርም ጥናቱ ወንዶችና ሴቶችን ያለምንም ልዩ ትኩረት እንዳሳተፈ መረዳት እንችላለን፡፡ 82.8 በመቶው የሚሆኑት ተማሪዎች እድሜ ከ10 እስከ 12 ዓመት

በመሆኑ የተመረጡት የህጻናት መጻህፍት ለአብዛኛዎቹ ናሙናዎች የሚመጥኑ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 4.2 በመፃህፍቱ ላይ የተሰጡ ምላሾች

በዚህ ክፍል ተማሪዎቹ የተነበቡላቸው ታሪኮች ገፀባህሪያትን ማስታወስ አለማስታወሳቸውን ለማወቅ፤ የሚፈልጉትን የታሪክ አይነት ለመምረጥና ታሪኩ ያሳደረባቸውን ስሜት ለመረዳት የሚጠቅሙ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ጥያቄ አንድ መላሾቹ የተነበበላቸው ታሪክ ስለምን እንደሚናገር ምላሽ እንዲሰጡ የቀረበላቸው ነው፡፡ ለተማሪዎቹ ከተነበቡት 6 መጻህፍት ውስጥ ሦስቱ የእንስሳት ታሪኮች ሲሆኑ ሦስቱ ደግሞ የሰው ታሪኮች ናቸው፡፡ የእንስሳት ታሪክ የሆኑት መፃህፍት ብልሁ ጠቋሪት፣ ቱሲ እና ቹኪ፣ ሊንቻ እና ቢንቻ ሲሆኑ የሰው ታሪክ የያዙት ደግሞ የአንቺነሽ ተስፋ፣ ካሳ እና የአሰለፈች ሎሚዎች ናቸው፡፡ መፃህፍቱ በምእራፍ ሁለት በተገለፀው መሰረት በዘመናዊ ፋንታሲና በወቅታዊ እውነታዊ ልቦለድ ውስጥ የሚመደቡ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ መጽሀፍ ለ30 ተማሪዎች ተነቧል፡፡

ሰንጠረዥ 2 ታሪኮቹ ስለምን እንደሚናገሩ ማስታወስ

| የመፅሐፉ ርዕስ | 1. የተነበበልህ/ሽ/ ታሪክ ስለምን የሚናገር ነው? | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሀ. ስለ እንስሳ | | ለ. ስለ ሰው | | ሐ. ስለ ቁሳቁስ | | መ. ስለ አምላክ | |
| | ድግግም | በመቶኛ | ድግግም | በመቶኛ | ድግግም | በመቶኛ | ድግግም | በመቶኛ |
| ብልሁ ጠቋሪት | 29 | 96.7 | | | 1 | 3.3 | | |
| ቱሲ እና ቹኪ | 28 | 93.3 | 2 | 6.7 | | | | |
| የአንቺነሽ ተስፋ | | | 28 | 93.3 | | | 2 | 6.7 |
| ካሳ | | | 27 | 90 | | | 3 | 10 |
| የአሰለፈች ሎሚዎች | | | 30 | 100 | | | | |
| ሊንቻ እና ቢንቻ | 27 | 90 | 3 | 10 | | | | |

ሰንጠረዥ2 ለተማሪዎች የተነበበላቸውን ታሪክ ዋና ዋና ገፀባህሪያት ማስታወስ መቻላቸውን ለማረጋገጥ ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎቹ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ነው፡፡ የዚህ ጥያቄ ዋና አላማ ተማሪዎቹ ታሪኩን በደንብ መከታተላቸውን ማወቅ ነው፡፡ ታሪካቸው የተነገረላቸውን ባለታሪኮች ለይተን እንዲያመለክቱ በሚረዳው በዚህ ጥያቄም ተማሪዎች በቁጥር 168 የሚሆኑት (93.3 በመቶ) መፃህፍቱ የምን ታሪክ እንደያዙ በአግባቡ አመልክተዋል፡፡ በየታሪኮቹ ውስጥ በዋናነት ያልተጠቀሱ ባለታሪኮችን በምላሻቸው ያመለከቱት 12 ተማሪዎች

(6.7 በመቶ)የሚያህሉት ናቸው፡፡ ይህም ከ 12ቱ በስተቀር በክፍሉ ውስጥ የተነበበላቸውን ታሪክ ሁሉም ተማሪዎች በአግባቡ መከታተላቸውን ወይም የምን ታሪክ እነደሆን መገንዘባቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ለተማሪዎቹ የተነበቡት ታሪኮች በአድማጮቻቸው ላይ የሚያሳድሩት የራሳቸው የሆነ ስሜት አለ፡፡ ይህ ስሜት አንባቢ ወይም አድማጭ ካየው፣ ካሰበውና ከተሰማው ስሜት በመነሳት የሚሰጠው የምላሽ ዓይነት ነው፡፡ የአንባቢያን ምላሽ ንድፈ ሀሳብ በተቃኘበት በዚህ ጥናት ውስጥ የዚህ አይነቱ ምላሽ ኤስቴቲክ (Aesthetic) ተብሎ እንደሚጠራ ተገልጿል፡፡ የተነበቡት ታሪኮች በተማሪዎቹ ላይ ያሳደሩትን ስሜት ለማወቅ በመጠይቁ የቀረበው ጥያቄ እና መላሾቹ የሰጡት መልስ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 3 ታሪኮቹ በተማሪዎች ላይ ያሳደሩት ስሜት

| ጥ.ቁ | የጥያቄ ይዘት | የመላሾች ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድግግም | | | | | | ድምር | በመቶኛ |
| | | ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | | |
| 2 | ታሪኩ ምን አይነት ስሜት አሳደረብህ/ሽ/ | | | | | | | | |
| | ሀ. አስደሰተኝ አሳቀኝ | 3 | 7 | | | | 1 | 11 | 6.1 |
| | ለ. አሳዘነኝ | | | 30 | 27 | 20 | 20 | 97 | 53.9 |
| | ሐ. አስገረመኝ | 27 | 20 | | 3 | 10 | 9 | 69 | 38.3 |
| | መ. አናደደኝ | | 3 | | | | | 3 | 1.7 |
| | ድምር | 30 | 30 | 30 | 30 | 30 | 30 | 180 | 100 |

<u>መግለጫ</u>

፩ = ብልሁ ጠቋሪት ፪ = ቱሲና ቹኪ ፫ = የአንቺነሽ ተስፋ

፬ = የአሰለፈች ሎሚዎች ፭ = ካሳ ፮ = ሲንቻና ቢንቻ

በክፍል ውስጥ የተነበቡላቸው ታሪኮች ያሳደሩባቸውን ስሜት አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ከጠቅላላ መላሾቹ ከግማሽ በላይ የሆኑት በቁጥር 97 (53.9 በመቶ) ታሪኮቹ እንዳሳዘናቸው አስታውቀዋል፡፡ 69 ተማሪዎች (38.3 በመቶ) የሚሆኑት ደግሞ በታሪኮቹ መገረማቸውን ሲገልፁ 11 (6.1 በመቶ) ተማሪዎች ግን ታሪኮቹ አስቀውናል ብለዋል፡፡ በታሪኮቹ የተናደዱት ደግሞ ከመላሾቹ 3 (1.7 በመቶ) ብቻ ናቸው፡፡ በዘመናዊ ፋንታሲ መልክ ከቀረቡት መፃህፍት ውስጥ ሁለቱ ብልሁ ጠቋሪት እና ቱሲ እና ቹኪ በመላሾቹ ላይ

የመገረም ስሜት አሳድረዋል፡፡ የአንቺነሽ ተስፋ የተነበበላቸው ሁሉም መላሾች፣ የአሰለፈች ሎሚዎች ከተነበበላቸው 27 መላሾች፣ ካሳ ከተነበበላቸው 20 መላሾች፣ ሊንቻና ቢንቻ ከተነበበላቸው 20 መላሾች ደግሞ ታሪኮቹ አሳዝነዋቸዋል፡፡

ይህ ጥያቄ በዋናነት የቀረበው ታሪኮቹ በተማሪዎቹ ላይ ያሳደሩትን ስሜት (ኤስቴቲካዊ) ምላሽ ለማወቅ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ታሪኮቹ በአብዛኛዎቹ በ97 ተማሪዎች ላይ የሀዘን እና በ69 ተማሪዎች ላይ ደግሞ የመገረም ስሜት ማሳደራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም ምክንያት ከተመረጡት መፃህፍት አራቱ የማይረሳ አሳዛኝ ታሪክ (Tragedy) ያላቸው እና ሁለቱ ደግሞ በጀብዱ (Adventure) የተሞሉ መሆናቸውን የተማሪዎች ምላሽ ያስረዳል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 2 ከዚህ በተጨማሪም ከጥያቄ ቁጥር 3 ጋር በሚተነተንበት ወቅት ተማሪዎቹ ምን አይነት ስሜት የሚያሳድርባቸውን ታሪክ አብልጠው ይወዳሉ ለሚለው ጥያቄ መልስ ማስገኘት የሚያስችል ነው፡፡ በመቀጠልም ደግሞ መላሾቹ ለተነበቡት ታሪኮች ያላቸውን ፍላጎት ያሳያል በሚል የተጠየቀው ጥያቄና የተማሪዎቹ ምላሽ ይቀርባል፡፡

ሰንጠረዥ 4 ተማሪዎች ለተነበቡት መፃህፍት ያሳዩት ፍላጎት

| ተ.ቁጥር | የጥያቄ ይዘት | የመላሾች ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድግግም | | | | | | ድምር | በመቶኛ |
| | | ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | | |
| 3 | የተነበበልህ/ሽ/ ታሪክ ምን ያህል ወደድከው/ሽው/ | | | | | | | | |
| | ሀ. ወድጄዋለሁ | | 13 | 1 | | 8 | 3 | 25 | 13.9 |
| | ለ. እጅግ በጣም ወድጄዋለሁ | 30 | 15 | 25 | 30 | 20 | 26 | 144 | 80 |
| | ሐ. አልወደድኩትም | | 2 | 6 | | 2 | 1 | 11 | 6.1 |
| | መ.እጅግ በጣም አልወደድኩትም | | | | | | | | |
| ድምር | | 30 | 30 | 30 | 30 | 30 | 30 | 180 | 100 |

<u>መግለጫ</u>

፩ = ብልሁ ጠቋሪት
፪ = ቱሲና ቹኪ
፫ = የአንቺነሽ ተስፋ
፬ = የአሰለፈች ሎሚዎች
፭ = ካሳ
፮ = ሊንቻና ቢንቻ

በሰንጠረዥ 4 ተማሪዎቹ ለታሪኮቹ ያላቸውን ፍላጎት ለማሳየት የሚረዳ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ብልሁ ጠቋሪት እና የአንቺነሽ ተስፋ የተነበቡላቸው ሁሉም ተማሪዎች ታሪኮቹን እጅግ በጣም የወደዷቸው ሲሆን የአንቺነሽ ተስፋ፣ ካሳ እና ሊንቻ እና ቢንቻ ከ20 በላይ

በሚሆኑ መላሾች እጅግ በጣም ተወደዋል፡፡ የተነበቡት ታሪኮች የተለያየ ይዘት ያላቸው ቢሆኑም እንኳ ከጠቅላላ መላሾች ውስጥ 144 (80 በመቶ) የሚሆኑት ተማሪዎች የተነበቡላቸውን ታሪኮች እጅግ በጣም እንደወደዷቸው በምላሻቸው ገልፀዋል፡፡ ከጠቅላላ መላሾች 25 ተማሪዎች ታሪኩን የወደዱት መሆኑን ሲያስታውቁ ይህም ከተማሪዎቹ የ13.9 በመቶ ድርሻ አለው፡፡ ታሪኮቹን እንዳልወደዷቸው የገለፁት ደግሞ ከጠቅላላ መላሾች ውስጥ 11 ተማሪዎች (6.1 በመቶ) የሚሆኑት ናቸው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ታሪኮቹን ለምን እንዳልወደዷቸው በጥያቄ አራት ላይ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ምክንያቶቻቸውን አስታውቀዋል፡፡ ከ11 ተማሪዎች መካከል 4 ከጠቅላላ መላሾቹ 2.2 በመቶ የሚሆኑት ታሪኩ እውነት ስላልመሰሏቸው እንዳልወደዷቸው ገልፀዋል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ 3 ተማሪዎች (1.7 በመቶ) በታሪኮቹ ይዘት እና አጨራረስ ምክንያት ታሪኮቹን እንዳልወደዷቸው በምላሻቸው ጠቁመዋል፡፡ 2 ተማሪዎች ምክንያታቸውን ያልጠቀሱ ሲሆን አንዱ ቋንቋው አልገባኝም ሌላው ደግሞ ሙሉ በሙሉ ታሪኩን አልወደድኩትም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህ ውጤት የሚሳየው የተነበቡት መፃህፍት በ169 መላሾች መወደዳቸውን ነው፡፡ ስለዚህም ደራሲያኑ ህፃናቱ የሚወዷቸው ዓይነት መፃህፍት መፃፋቸውን የሚጠቁም ነው፡፡

ተማሪዎቹ የሚወዱት ምን አይነት ስሜት የሚያሳድርባቸውን ታሪክ እንደሆነ ለመረዳት ጥያቄ ቁጥር 2 እና ጥያቄ ቁጥር 3 ይህንን መረጃ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

ሠንጠረዥ 5 በተማሪዎች የሚወደዱ ታሪኮች ይዘት

| ታሪኩን ምንያህል ወደዱት | ታሪኩ ያሳደረባቸው ስሜት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሀ. አሳቀኝ | | ለ. አሳዘነኝ | | ሐ. አስገረመኝ | | መ. አናደደኝ | |
| | ድግግም | በመቶ | ድግግም | በመቶ | ድግግም | በመቶ | ድግግም | በመቶ |
| ሀ.ወድጄዋለሁ | 3 | 1.7 | 14 | 7.8 | 7 | 3.9 | 1 | 0.6 |
| ለ. እ.በጣም ወድጄዋለሁ | 8 | 4.4 | 77 | 42.8 | 57 | 31.7 | 2 | 1.1 |
| ሐ. አልወደድኩትም | | | 6 | 3.3 | 5 | 2.8 | | |
| መ. እ.በ አልወደድኩትም | | | | | | | | |

ይህ ሰንጠረዥ የሚያሳየው ለጥያቄ ቁጥር 2 የተሰጠው ምላሽ ከጥያቄ ቁጥር 3 ጋር ሲተያይ በጥናቱ የተሳተፉ የጠቅላላ ተማሪዎቹ ምላሽ ምን እንደሚመስል ነው፡፡ የተነበቡት ታሪኮች

አሳዝነውኛል ካሉት መካከል 77 (42.8 በመቶ) የሚሆኑት ታሪኩን በእጅጉ እንደወደዱት ገልፀዋል፡፡ በቁጥር 14 ተማሪዎች (7.8 በመቶ) የሚሆኑት ደግሞ ወደነዋል ያሉ ሲሆን አሳዘነኝ ካሉት 6 (3.3 በመቶ) የሚሆኑት ግን ታሪኮቹን አልወደድናቸውም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተቀራራቢ በሆነ መንገድ ታሪኮቹ አስገርመውናል ብለው መልስ ከሰጡት መካከል 57 ተማሪዎች (31.7 በመቶ) የሆኑት ታሪኮቹን እጅግ በጣም ወደናቸዋል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ 7 መላሾች (13.9 በመቶ) ደግሞ ታሪኮቹን እንደወደዷቸው ገልፀዋል፡፡ 5 ተማሪዎች ግን አስገርመውናል ያሏቸውን ታሪኮች አልወደድናቸውም ብለዋል፡፡ እነዚህ መላሾች ከጠቅላላ መረጃ አቀባዮች 2.8 በመቶ ይሆናሉ፡፡ ታሪኮቹ አሳቁኝ ካሉት 11 መላሾች ውስጥ 8 (4.4 በመቶ) የሚሆኑት ታሪኮቹን እጅግ በጣም የወደዷቸው መሆኑንና 3 (1.7 በመቶ) የሚሆኑት ደግሞ እንደወደዷቸው በሰጡት ምላሽ አመልክተዋል፡፡እናዶናል ካሉት ውስጥ ሁለት (1.1 በመቶ) መላሾች ታሪኩን እጅግ በጣም የወደዱት መሆኑን ሲገልፁ አንዱ (0.6 በመቶ) መላሽ ደግሞ ወድጄዋለሁ፡፡ ሲል አመልክቷል፡፡

ይህ የተማሪዎቹ ምላሽ የሚያስረዳን የሚያሳዝንም ሆነ የሚያስገርም ይዘት ያለው ታሪክ በተማሪዎቹ ዘንድ በእጅጉ ሊወደድ የሚችል መሆኑን ነው፡፡ የተነበቡላቸውን ታሪኮች በተለያዩ ምክንያቶች ተማሪዎቹ ላይወዷቸው ይችላሉ፡፡ በምላሻቸው ታሪኮቹን እንዳልወደዷቸው ከገለፁት 11 መላሾች መካከል በመጠይቁ ክፍል ሁለት ጥያቄ ቁጥር 4 ላይ ምክንያታቸውን እንዲሰጡ በተጠየቁት መሠረት አራቱ ወይም ከጠቅላላ መላሾች ውስጥ 2.2 በመቶ የሚሆኑት ታሪኩ እውነት ስላልመሰላቸው እንዳልወደዱት ገልፀዋል፡፡ ከጠቅላላ መላሾች ውስጥ 1.7 በመቶ ድርሻ ያላቸው ሦስት ተማሪዎች ደግሞ የታሪኮቹ አጨራረስና ይዘት ታሪኮቹን እንዳይወዷቸው ምክንያት መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡ ከጠቅላላ መላሾች ውስጥ ሁለቱ (1.1 በመቶ) የሚሆኑት ተማሪዎች ምክንያታቸውን ያልገለፁ ሲሆን አንድ መላሽ (0.6 በመቶ) ቋንቋው አልገባኝም በተመሳሳይ ሌላ አንድ ተማሪ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ታሪኩን እንዳልወደደው አስታውቋል፡፡ ስለዚህ ያታሪኩ እውነት አለመምሰል የታሪኮቹ አጨራረስና የቋንቋው ግልፅ አለመሆን ለታሪኮቹ አለመወደድ ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ ምላሾቹ ይጠቁማሉ፡፡

ቀጥሎ የቀረበው ጥያቄ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የተነበበላቸው ታሪክ በምን ያህል መጠን እንደገባቸው ወይም እንዳልገባቸው ለማወቅ የሚረዳ ነው፡፡

ለንጠረዥ 6 ታሪኩ ምን ያህል ገብቷችኋል

| ጥያቄ ቁጥር | የጥያቄው ይዘት | የመላሾች ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድግግም | | | | | | ድምር | በመቶኛ |
| | | ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | | |
| 5 | የተነበበው ታሪክ | | | | | | | | |
| | ሀ. የሚገባ ነው | 3 | | 12 | 8 | 13 | 9 | 45 | 25 |
| | ለ. በመጠኑ የሚገባ ነው | | 10 | 1 | 4 | 3 | 6 | 24 | 13.3 |
| | ሐ. በጣም የሚገባ ነው | 27 | 19 | 15 | 18 | 14 | 15 | 108 | 60 |
| | መ. በጭራሽ የማይገባ ነው | | | | | | | - | - |
| | መልስ ያልሰጡ | | 1 | 2 | | | | 3 | 1.7 |
| ድምር | | 30 | 30 | 30 | 30 | 30 | 30 | 180 | 100 |

መግለጫ

፩ = ብልሁ ጠቋሪት ፪ = ቱሲና ቹኪ ፫ = የአንቺነሽ ተስፋ

፬ = የአሰለፈች ሎሚዎች ፭ = ካሳ ፮ = ሊንቻና ቢንቻ

ለተማሪዎች የተነበቡት ታሪኮች ገብተዋቸው ወይም አልገቧቸው እንደሆነ ለማወቅ ለቀረበው ለዚህ ጥያቄ መልስ ካልሰጡት ሦስት መላሾች በስተቀር ሁሉም በተለያየ ደረጃ የገባቸው መሆኑን የሚጠቁም ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከጠቅላላ መላሾች ውስጥ 108 (60 በመቶ) የሚሆኑት የተነበቡት ታሪኮች በጣም የሚገቡ መሆናቸውን፣ 45 (25 በመቶዎቹ) ደግሞ ታሪኮቹ በቀላሉ እንደገቧቸውና 24 (13.3 በመቶ) የሚሆኑት በመጠኑ የገቧቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህ ምላሽ ለህፃናት ተብለው የሚፃፉት ታሪኮች ህፃናቱ በቀላሉ እንዲገነዘቧቸው ተደርገው የሚፃፉ መሆናቸውን ሊጠቁም የሚችል ነው፡፡ በዚህም የህፃናት መፃህፍት ህፃናቱን ለማስደሰት የሚችሉት ሲገቧቸውና ታሪኮቹን በቀላሉ ሲገነዘቧቸው ነው የሚለውን የምሁራኑን ንድፈ ሃሳብ የተከተሉ ወይም የሚያሟሉ ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡

በተጨማሪም ከተማሪዎቹ ውስጥ (95 በመቶ) የሚሆኑት ታሪኮቹ በተነበቡላቸው ቋንቋ አፉቸውን የፈቱ፣ በመሆኑ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሚነገራቸውን ተረት ወይም የሚነበብላቸውን መፅሐፍ በቀላሉ መገንዘብ መቻላቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

የሚቀጥለው ጥያቄ ተማሪዎቹ ተመሳሳይ ታሪኮች ለመስማት ምን ያህል ፍላጎት እንዳላቸው ለማወቅ የሚረዳ ነው፡፡ ይህ ጥያቄ ሲዘጋጅ ታሳቢ የተደረገው የተነበበላቸውን ታሪክ ካልወደዱት ወይም ከሰለቻቸው ሌላ ተመሳሳይ ታሪክ እንዲነበብላቸው ሲጠይቁ የሚኖራቸው ዝንባሌ አነስተኛ ይሆናል የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የተነበበላችሁን ታሪክ

ምን ያህል ወዳችሁታል በሚል በዚሁ ክፍል ጥያቄ ቁጥር 3 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ ከሰጡት መልስ ጋር ሊነፃፀር የሚችል ነው፡፡

ሰንጠረዥ 7 ለተመሳሳይ ታሪኮች ያላቸው ፍላጎት

| ጥያቄ ቁጥር | የጥያቄው ይዘት | የመላሾች ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድግግም | | | | | | ድምር | በመቶኛ |
| | | ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | | |
| 6 | ተመሳሳይ ታሪክ መስማት ትፈልጋለህ/ሽ/ | | | | | | | | |
| | ሀ. እጅግ በጣም እፈልጋለሁ | 28 | | 16 | 25 | 27 | 15 | 111 | 61.7 |
| | ለ. በጣም እፈልጋለሁ | | 19 | | | | 2 | 21 | 11.7 |
| | ሐ. በመጠኑ እፈልጋለሁ | 2 | 10 | 9 | 5 | 2 | 13 | 41 | 22.7 |
| | መ. በፍፁም አልፈልግም | | | 5 | | 1 | | 6 | 3.3 |
| | ምላሽ ያልሰጡ | | 1 | | | | | 1 | 0.6 |
| | ድምር | 30 | 30 | 30 | 30 | 30 | 30 | 180 | 100 |

መግለጫ

፩ = ብልሁ ጠቋሪት ፪ = ቱሲና ቹኪ ፫ = የአንቺነሽ ተስፋ

፬ = የአሰለፈች ሎሚዎች ፭ = ካሳ ፮ = ሊንቻና ቢንቻ

ለዚህ ጥያቄ መልስ ከሰጡት ከጠቅላላ መላሾች መካከል 111 የሚሆኑት ሌላ ተመሳሳይ ታሪክ ቢነበብላቸው ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡ ይህ ደግሞ ከጠቅላላ መላሾች ውስጥ 61.7 በመቶውን የሚወክል ነው፡፡ በመጠኑ እፈልጋለሁ ያሉት ከጠቅላላ መላሾች ውስጥ ቁጥራቸው 41 (22.7 በመቶዎች) ናቸው ፡፡እነዚህ ባለታሪኮች አነስተኛ ፍላጎት አሳይተዋል ከሚባሉት ውስጥ የሚካተቱ ሲሆን ታሪኩ እንዲነበብላቸው በጣም የሚፈልጉት 21 ተማሪዎች ደግሞ ከጠቅላላው መላሾች 11.7 በመቶውን የሚወክሉ ናቸው፡፡ ተመሳሳይ ታሪክ ፈፅሞ እንዲነበብላቸው ያልፈለጉት ስድስት (3.3 በመቶ) ተማሪዎች ታሪኩን አልወደድነውም ብለው በጥያቄ ቁጥር 3 ላይ በመለሱት 11 ተማሪዎች ጋር ሲነፃፀሩ መጠነኛ መቀነስ አሳይተዋል፡፡ መቼም የተነበበላቸውን ታሪክ ሳይወዱት ተመሳሳይ ታሪክ እንዲነበብላቸው ቢጠየቁ በፍፁም ደስታ "እፈልጋለሁ" የሚል ምላሽ ይሰጣሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡ አንድ

መላሽ መልስ ለመስጠት አልፈለገም ይህም ከጠቅላላ መልስ ሰጪዎች ውስጥ (0.6 በመቶውን) የሚወክል ነው፡፡

በሌላ በኩል ለዚህ ጥያቄ ተመሳሳይ ታሪክ እንዲነበብላቸው እጅግ በጣም እንደሚፈልጉ ገልፀው ምላሽ የሰጡት ተማሪዎች ቁጥር ታሪኩን እጅግ በጣም እንወደዋለን ብለው ለጥያቄ ቁጥር 3 መልስ ከሰጡት ጋር ሲነፃፀሩ በ33 መላሾች (በ18.3 በመቶ) ያነሱ ናቸው፡፡ ልዩነቱ ግን ቀድመው ከሰጡት መላሾች ጋር ፍፁም የተራራቀ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ በመሆኑም አብዛኛዎቹ መላሾች የተነበበላቸውንና እጅግ በጣም የወደዱትን ታሪክ የሚመስል ሌላ ታሪክ ቢነበብላቸው እጅግ በጣም ደስተኛ መሆናቸውን በጥያቄ ቁጥር 6 ከሰጡት ምላሽ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በመቀጠል መልስ እንዲሰጡበት ለተማሪዎች የቀረበላቸው ጥያቄ ከተነበቡላቸው ታሪኮች መጠን ጋር ተያያዥነት ያለው ነው፡፡ የታሪኩ መርዘም ወይም ማጠር ታሪኩን ከመውደድና አለመውደድ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማወቅ ይረዳ ዘንድ በዚሁ ክፍል በጥያቄ ቁጥር 6 ከሰጡት ምላሽ ጋር ለማስተያየት ጥረት ይደረጋል፡፡

ሰንጠረዥ 8 የታሪኮቹን መጠን በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ

| ጥያቄ ቁጥር | የጥያቄው ይዘት | የመላሾች ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድግግም | | | | | | ድምር | በመቶኛ |
| | | ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | | |
| 7 | የተነበበው ታሪክ | | | | | | | | |
| | ሀ. በጣም ረጅም ነው | 8 | 3 | 5 | | 7 | 12 | 36 | 20 |
| | ለ. ረጅም ነው | 17 | 10 | 20 | 30 | 21 | 18 | 116 | 64.4 |
| | ሐ. መካከለኛ ነው | 4 | 8 | | | 1 | | 13 | 7.2 |
| | መ. አጭር ነው | 1 | 9 | 4 | | | | 14 | 7.8 |
| | ሠ. በጣም አጭር ነው | | | | | 1 | | 1 | 0.6 |
| | መልስ ያልሰጡ | | | | | | | - | - |
| | ድምር | 30 | 30 | 30 | 30 | 30 | 30 | 180 | 100 |

መግለጫ

፩ = ብልሁ ጠቋሪት ፪ = ቱሲና ቹኪ ፫ = የአንቺነሽ ተስፋ

፬ = የአስለፈች ሎሚዎች ፭ = ካሳ ፮ = ሊንቻና ቢንቻ

የተነበቡላቸውን ታሪኮች አስመልክቶ ለተሰጠው ለዚህ ጥያቄ ከጠቅላላ መላሾች ውስጥ 116 የሚሆኑትን ረጅም ነው የሚል መልስ የሰጡ ሲሆን እነዚህ መላሾች 64.4 በመቶ ድርሻ ያላቸው ናቸው፡፡ በጣም ረጅም ነው ያሉት ከጠቅላላ መላሾች ውስጥ 36 (20 በመቶ) የሚሆኑ መላሾች ሲሆኑ አጥጋቢ ያሉት ደግሞ 14 መላሾች (7.8 በመቶ) የሚሆኑት ናቸው አንዱ መላሽ ብቻ ታሪኩ በጣም አጭር ነው ሲል መልስ ሰጥቷል፡፡

ይህንን ምላሽ ለጥያቄ ቁጥር 6 ከተሰጠው ምላሽ ጋር ስናነጻጽረው ከጠቅላላ መረጃ አቀባዮች ውስጥ 80 በመቶ የሚሆኑት ታሪኮቹን ወደዋቸዋል የተነበቡት ታሪኮች በጣም ረጅምና ረጅም ናቸው ያሉት ደግሞ ከጠቅላላ መላሾች 152 (84.4 በመቶ) የሚሆኑት ናቸው፡፡ ከመላሾቹ የተገኙት መረጃዎች የሚያመለክቱት ምንም እንኳን ታሪኮቹ በጣም ረጅም ወይም ረጅም ቢሆኑም እጅግ በጣም ተወዳጅ መሆናቸውን ነው፡፡

በሌላ በኩል ከ7 - 12 ዓመት ዕድሜ ላላቸው ልጆች እንደ እድሜያቸው የሚጻፉላቸው ታሪኮች በምዕራፍ የተከፋፈሉ ቢሆኑ ይመረጣል የሚል ንድፈ ሀሳብ አለ፡፡ በዚህ ጥናት ከተሳተፉት ህፃናት 149 (82.8 በመቶ) የሚሆኑት እድሜያቸው ከ10 - 12 አመት ቢሆንም እንኳን ታሪኮቹ ለአብዛኛዎቹ ተማሪዎች ረጅም ወይም በጣም ረጅም የሆኑባቸው መሆኑን ምላሻቸው ያመለክታል፡፡

ግለሰባዊ የንባብ ልምድ በአንባቢያን ምላሽ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ከአንባቢያን በሚገኝ መልስ ላይ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ አንባቢያን ከልምዳቸው ተነስተው የሚወዱትንና የማይወዱትን ርዕሰ ጉዳይ ከወዲሁ ለመለየትም ያስችላቸዋል፡፡ በመቀጠል የሚቀርቡት ጥያቄዎች በአንድ በኩል መላሾቹ የቀደመ የንባብ ልምድ እንዳላቸውና እንደሌላቸው ለማወቅ የሚረዱ በሌላ በኩል የሚመርጡትን ርዕሰ ጉዳይ ለማወቅ የሚጠቅሙ ናቸው፡፡

ሰንጠረዥ 9 የመላሾች የንባብ ልምድና ፍላጎት

| ጥያቄ ቁጥር | የጥያቄ ይዘት | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | ድግግም | በመቶኛ |
| 8 | ሌላ የተረት መፅሐፍ አንብበህ/ሽ/ ታውቃለህ/ሽ/ | | |
| | ሀ. አውቃለሁ ----------- | 167 | 92.8 |
| | ለ. አላውቅም ----------- | 10 | 5.5 |
| | መልስ ያልሰጡ ---------- | 3 | 1.7 |
| | ድምር | 180 | 100 |
| 9 | ምን አይነት ታሪክ ማንበብ ትወዳለህ/ጃለሽ/ | | |
| | ሀ. የእንስሳት የሚያስደስት ታሪክ ------ | 26 | 14.5 |
| | ለ. የእንስሳት የሚያሳዝን ታሪክ ------- | 9 | 5 |
| | ሐ. የሰው የሚያስደስት ታሪክ -------- | 17 | 9.4 |
| | መ. ሰው ሚያሳዝን ታሪክ ------------ | 41 | 22.8 |
| | ሠ. ሁሉም ------------------------------ | 85 | 47.2 |
| | መልስ ያልሰጡ ------------------------ | 2 | 1.1 |
| | ድምር | 180 | 100 |

ለጥያቄ ቁጥር 8 በተሰጠ ምላሽ 167 (92.8 በመቶ) ተማሪዎች ቀደም ሲል ሌሎች የህፃናት መፃህፍትን ማንበባቸውን አስታውቀዋል፡፡ በመሆኑም ይብዛም ይነስም መላሾቹ ከቀደመ የንባብ ልምዳቸው የተነሳ ለአወንታዊ ወይም ለአሉታዊ ተፅዕኖ የተጋለጡ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ የሚያነቡትን የታሪክ አይነት ለመምረጥ እድል የሚሰጣቸው ነው፡፡ ከዚህ ልምዳቸው በመነሳት ለጥያቄ ቁጥር 9 በሰጡት ምላሽ አብዛኛዎቹ በቁጥር 85 (47.2 በመቶ) የሚሆኑት በምርጫ ውስጥ የተዘረዘሩትን ሁሉንም ዓይነት ታሪኮች ማንበብ እንደሚወዱ ገልፀዋል፡፡

የሰው የሚያሳዝን ታሪክ ማንበብ እንደሚወዱ የገለፁት ደግሞ 41 መላሾች (22.8 በመቶ) የሚሆኑት ናቸው፡፡ ይህም ለህፃናት ሊቀርብ የሚገባው ታሪክ ሀዘን ውስጥ የማይከታቸው መሆን አለበት የሚለውን ሃሳብ በተወሰነ መልክ የሚፃረርና የሚያሳዝን ታሪክ እንኳ ቢሆን በህፃናቱ ሊወደድ ይችላል የሚለውን የሚደግፍ ግኝት ነው፡፡ በመሆኑም ህፃናት አንባቢያኑ የሠው የሚያሳዝን ታሪኮችን ከሚያዝናኑና ከሚያሳዝኑ የእንስሳት ታሪክ በበለጠ ማንበብ ወይም ማድመጥ እንደሚፈልጉ በምላሻቸው አረጋግጠዋል፡፡

ከመላሾቹ ውስጥ 26 (14.5 በመቶ) የሚሆኑት አስቂኝ የእንስሳት ታሪኮችን፣ 17 (9.4 በመቶ) ደግሞ የሰው ሚያስቁ ታሪኮችን ማንበብ እንደሚያስደስታቸው ገልፀዋል፡፡ የእንስሳት

የሚያሳዝን ታሪክ ማንበብ የሚፈልጉት 9 (5 በመቶ) ሲሆኑ 2 መላሾች መልስ ከመስጠት ተቆጥበዋል፡፡ መጠኑ ቢለያይም መላሾቹ የተዘረዘሩትን ሁሉንም የታሪክ አይነቶች ማንበብ እንደሚወዱ ገልፀዋል፡፡ አብዛኛዎቹም በቁጥር 85 (47.2 በመቶ) ሁሉንም የሚለውን መርጠዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ የተለያዩ ይዘቶች ያሏቸውን ታሪኮች ማንበብ የሚፈልጉ መሆኑን ከዚህ ከሰጡት ምላሽ መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በመቀጠል የሚቀርበው ጥያቄ ይዘት ለህፃናት የሚገዙ መፅሐፍት በማን ምርጫ እንደሚገዙ ለማወቅ ዕድል የሚሰጥ ነው፡፡ የዚህ ጥያቄ ዓላማም ተማሪዎቹ የሚመርጧቸውን ዓይነት ታሪኮች የያዙ መፃህፍትን ለማግኘት የሚያስችል ዕድል መኖር አለመኖሩን መመልከት ነው፡፡

ሰንጠረዥ 10 የህጻናት መፃህፍት መራጮች

| ጥያቄ ቁጥር | የጥያቄው ይዘት | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | ድግግም | በመቶኛ |
| 10 | የተረት መፃህፍት የሚገዙልህ/ሽ/ በማን ምርጫ ነው | | |
| | ሀ. በራሴ ምርጫ | 78 | 43.4 |
| | ለ. በራሴና በወላጆቼ ምርጫ | 85 | 47.2 |
| | ሐ. በወላጆቼ ምርጫ | 2 | 1.1 |
| | መ. በሚገዙልኝ ሠዎች ምርጫ | 11 | 6.1 |
| | መልስ ያልሰጡ | 4 | 2.2 |
| | ድምር | 180 | 100 |

ከጠቅላላ መላሾች ውስጥ በቁጥር 85 የሚሆኑት ተማሪዎች በራሳቸውና በወላጆቻቸው ምርጫ መፅሐፍ እንደሚገዛላቸው ገልፀዋል እነዚህ መላሾች የ47.2 በመቶ ድርሻ ያላቸው ናቸው፡፡ ከነዚህ ጋር የሚመጣጠኑ ተማሪዎች ደግሞ የሚገዙላቸው መፃህፍት በራሳቸው ምርጫ ላይ የተመሰረተ፣ መሆናቸውን ገልፀዋል የነዚህ ተማሪዎች ቁጥርም 78 (43.4 በመቶ) የሚሆን ነው፡፡ ይህም በሚገዙላቸው መፃህፍት ምርጫ ላይ ተማሪዎች ያላቸውን ትልቅ ስፍራ የሚያሳይ ነው፡፡ 11ተማሪዎች (6.1 በመቶ) ምርጫው የሚገዙላቸው ሠዎች መሆኑን የሚያመላክት ምላሽ ሲሰጡ፣ 4 የሚሆኑት መላሾች ግን ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት አልፈቀዱም፡፡ ከ180 መላሾች ውስጥ 2 ብቻ (1.1 በመቶ) የሚሆኑት መፃህፍቱ በወላጆቻቸው ምርጫ እንደሚገዙላቸው ገልፀዋል፡፡ ከዚህ ምላሽ ወላጆች አብዛኛውን የታሪክ

መፃህፍት የሚገዙት በራሳቸው ፍላጎት ላይ ብቻ ተመስርተው ሳይሆን የልጆቹንም ምርጫ በስፋት ግምት ውስጥ ባስገባ መንገድ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

## 4.3 የመላሾች የንባብ ልምድና ፍላጎት

በዚህ ክፍል ውስጥ ለመላሾች የቀረቡት ሁለት ጥያቄዎች የንባብ ልምዳቸውንና የሚፈልጓቸውን መጻህፍት ለማወቅ የሚጠቅሙ ናቸው፡፡ ከአንባቢዎቹ ምላሽ በመነሳትም በብዛት በህፃናቱ የሚነበቡትን መፃህፍት አይነቶች ለማወቅ ይቻላል፡፡የጥያቄዎቹም ዋነኛ ዓላማ ይኸው ነው፡፡

ሰንጠረዥ 11 መላሾች ያነበቧቸው መፃህፍት

| ጥያቄ ቁጥር | የጥያቄ ይዘት | የተጠቀሱ የመፃህፍ ርዕሶች ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ያነበብካቸውን/ሻቸውን የተረት መፃህፍት ርዕስ ዘርዝሩ | |
| | - ከባህላዊ ሥነፅሁፍ | 40 |
| | - ከተተረጎሙ መፅሀፍቶች | 274 |
| | - በአማርኛ ቋንቋ ከተደረሱ | 283 |
| | - ካልታወቁ | 73 |
| | ድምር | 670 |
| 2 | ሁለት በጣም የምትወዳቸውን/ጃቸውን የተረት መፃህፍት ርዕስ ፃፍ | |
| | - ከባህላዊ ሥነፅሁፍ | 17 |
| | - ከተተረጎሙ መፅሀፍቶች | 108 |
| | - በአማርኛ ቋንቋ ከተደረሱ | 123 |
| | ካልታወቁ | 41 |
| | ድምር | 289 |

መላሾቹ የዘረዘሯቸውን የመጻህፍት ርዕሶች በማየት የመጻህፍቱን ዓይነት አራት ቦታ በመክፈል ለመመደብ ጥረት ተደርጓል፡፡ የተጠቀሱት አንዳንዶቹ መጻህፍት ከተለያዩ ክልሎች የተሰበሰቡ እና የታተሙ ሀገራዊ ተረቶች የያዙ ናቸው ፡፡ እነዚህ መጻህፍት ባህላዊ ሰነጽሁፍ በሚል ርዕስ ስር እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡ ሌሎች ደግሞ በውጪ ሀገር ለህጻናት ከተዘጋጁ መጻህፍት ወደ አማርኛ የተተረጎሙ ናቸው፡፡ እነዚህ ከተተረጎሙ መጻህፍት በሚል ርዕስ ስር የተመደቡ ሲሆን ኢትዮጵያውያን ደራሲያን በአማርኛ ቋንቋ የጻፏቸው ታሪኮች ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ከተደረሱ በሚል ርዕስ ስር ተመድበው እንዲቆጠሩ

ተደረጓል፡፡ ርዕሳቸውን በማየት በውል ለመለየት ያዳገቱት ደግሞ ያልታወቱ የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል፡፡

ለመጀመሪው ጥያቄ ከተሰጡት ምላሾች መካከል 670 የሚሆኑትን ማንበብ ተችሏል፡፡ እነዚህም እንደየ ምድባቸው ተደልድለው የተቆጠሩ ሲሆን ለዚህ ጥያቄ የተሰጠው መልስ በአማካኝ አንድ ምላሽ ሶስት መፅሀፎችን አንብቧል የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ ያስችላል፡፡የአንዳንድ መፃህፍት ርእሶች በእጅጉ ተደጋግመው ይጠቀሳሉ በዚህም ምክንያት ከአንድ ጊዜ በላይ ተደጋግሞ የመቆጠር ዕድል ያጋጥማቸዋል፡፡የዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚያመለክተው የተተረጎሙና በአማርኛ ቋንቋ የተደረሱ መፃህፍት በብዙ መላሾች የተነበቡ መሆኑን ነው፡፡ የመፃህፍቱ ርዕስ ተጠቅሶ በአጥኚው ከየትኛው ክፍል እንደሚመደቡ ያልታወቁ መፅሀፎች “ያልታወቁ” ተብለው ተገልጸዋል፡፡

በሁለተኛ ጥያቄ ላይ እንደሚታየውም የተተረጎሙና በአማርኛ ቋንቋ የተደረሱ መፃህፍት በተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ እንደሚወደዱ ተገልጿል፡፡ የባህላዊ ሥነፅሁፍ ከነዚህ የመፃህፍት አይነቶች ጋር ሲወዳደር በብዛት የመነበብም ይሁን የመወደድ እድል አለማግኘቱ ምክንያቱ ምን ይሆን ከዚህ ጥናት ወሰን ውጪ ቢሆንም ጥያቄው ግን ምላሽ የሚፈልግ ነው፡፡

## 4.4 ከቡድን ውይይት የተገኙ ምላሾች

የተማሪዎች ምላሽ ከተሰበሰበባቸው መንገዶች አንዱ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ነው፡፡ በዚህ ዘዴ ምላሾችን ለማሰባሰብ የተደረገው በመጠይቁ ላልቀረቡ ጥያቄዎች ተጨማሪ ምላሽ ለማግኘት ያስችላል በሚል ነው፡፡ በመጠይቁ የተመለሱ ነጥቦችን ለማረጋገጥ ከመርዳቱም በላይ በሙሉ ነፃነት ተማሪዎች ምላሾችን በተነበቡላቸው ታሪኮች ዙሪያ ለመስጠት እንዲችሉ ሁነኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ ከየትምህርት ቤቱ ሰባት ተማሪዎች ተሳትፈዋል በስድስቱ መፃህፍት ላይ 42 ተማሪዎች በተተኳሪ የቡድን ውይይቱ ላይ የተሳተፉ ሲሆን 25 ሴቶች 17 ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑት ተማሪዎች የክፍል ደረጃ ያሉ ህፃናት በአግባቡ የተቀረፁ ገፀባህሪያት ባላቸው ታሪኮች ውስጥ ካሉ ባለታሪኮች ጋር ራሳቸውን በማወዳደር አስተያየት እንደሚሰጡ በምዕራፍ ሁለት ተገልጿል፡፡ ይህ ሁኔታም በተተኳሪ የቡድን ውይይት ወቅት ተደጋግሞ መታየቱን ከተማሪዎች ጋር ውይይቱን ባካሔድኩበት ወቅት ለመገንዘብ ችያለሁ፡፡

ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ የተሰጡት መልሶች 3 መልክ ያላቸው ናቸው፡፡ በታሪኩ ውስጥ ያሉትን ገፀባህሪያት መልካም ተግባር ከራሳቸው ባህሪ ጋር በማወዳደር ይህንን ተግባር "እኔም ብሆን አደርገው ነበር" በማለት የሚሰጡት ምላሽ ብዙ ጊዜ በምክንያት የተደገፈ ነው፡፡ የዚህ አይነቱን ምላሽ አስመልክቶ የሚከተለው ምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ "የአሰለፈች ሎሚዎች" የሚል ርዕስ ባለው ታሪክ ውስጥ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እናትና አባቷ የሞቱባትን አሰለፍን አብራት እንድትኖር ለማድረግ ቅድስት የተባለችው ገፀባህሪ የምታከናውነው ተግባር ለብዙዎች ተደራሲያን በጥሩ አርአያነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ይህቺን ገፀባህሪ አስመልክተው አስተያየት ከሰጡት ተማሪዎች መካከል ምህረት ደስታ የተባለችው የአሳይ የህዝብ ትምህርት ቤት ተማሪ "ቅድስት ቦታ ብሆን እኔም አደርገዋለሁ ወላጆቻቸውን ላጡ ህፃናት ማዘን ያስፈልጋልና. . ." በማለት ተናግራለች፡፡ ይህች ተማሪ ራሷን በገፀባህሪዋ ቦታ በመተካት ቸርነት ለማድረግ ዝግጁ መሆኗን ገልፃለች፡፡ ምክንያቷ ደግሞ እናትና አባት ለሌላቸው ልጆች ማዘን አስፈላጊ በመሆኑን ነው፡፡

በሌላ በኩል "እንደገፀባህሪያቱ መሆን አለብን" የሚል ስሜት ያለው ምላሽ የሚሰጡ የውይይቱ ተሳታፊዎች አሉ፡፡ ይህም በታሪኩ ውስጥ የሚታየውን መልካም የገፀባህሪ ሁኔታ ለራሳቸው ከመመኘት የሚሰጡት አስተያየት ነው፡፡ "ሊንቻና ቢንቻ" ከተባለው ታሪክ መፅሀፍ ውስጥ የሊንቻን ገፀባህሪ አስመልክቶ "ሊንቻ አስተዋይ ናት፤ ስለዚህ እኛም እንደሷ ማንኛውንም ነገር ስንሰራ አስተውለን ረጋ ብለን መሆን አለበት፡፡" የሚል አስተያየት የሰነዘረችው የነፃነት ብርሃን ተማሪ እየሩስ ታሪኩ ናት፡፡". . . ታሪኩ አስተማሪ ስለሆነ ለኛ ስናድግም የሚጠቅም ስለሆነ ቤተሰቦቼን ጥዬ መሄድ እንደሌለብኝ ሲያረጁ ራሱ አብ ሆኜ መጦር እንዳለብኝ ነው" "ካሳ" የሚል ርእስ ያለውን ታሪክ ካዳመጠች በኋላ ታሪኳ አብርሀም የተባለች ተማሪ የሰጠችው አስተያየት ነው፡፡ ከነዚህ አስተያየቶች መረዳት እንደምንችለው እንደገፀባህሪዋ የመሆን ፍላጎት ቢያንስ ይህንን አስተያየት በሰጡትው ተማሪዎች ላይ መታየቱን ነው፡፡

በሦስተኛ ደረጃ በገፀባህሪያቱ ላይ የሚደርሱ አስከፊ ሁኔታዎች "በኔ ላይ ቢደርስስ" በሚል ስጋት የሚሰጠው አስተያየት ይጠቀሳል፡ አስተያየቱ ብዙ ጊዜ ሌሎችን ምሳሌ በማድረግ የሚሰነዘር አይነት ነው፡፡ "የአሰለፈች ሎሚዎች በጣም አሳዛኝ ታሪክ ነው፡፡ እንደዚህ ቢሆንስ ብለው ልጆች እነሱ ላይ እንደሚደርስ በማሰብ ሊጨነቁ ይችላሉ፡፡ ያስጨንቃል፡፡" ሄኖክ ታደሰ የተባለው የአሳይ ትምህርት ቤት ተማሪ የሰነዘረው ይህ አስተያየት በአሰለፈች ላይ

የደረሰው መከራ እኔ ላይ ቢደርስ ብለው ሌሎች እንደሚጨነቁ የሚጠቁም ቢሆንም ታሪኩን ግን አሳዛኝ፣ የሚያስጨንቅ ሲል ገልፆታል፡፡ በመሆኑም ክፉው ነገር ራሱ ላይ እንዳይደርስ ወደሌሎች ቢገፋውም ጭንቀቱ ግን የሱም መሆኑን ከንግግሩ መረዳት ይቻላል፡፡ "ሊንቻ እና ቢንቻ" በሚለው መጽሐፍ ላይ አስተያየት የሰጠው ናትናኤል ደግሞ ". . . ትንሹ አይጥ እናቱ የምትለውን ነገር ባለመስማቱ ለሞት ሊዳረግ ነበር እናት የምትለንን ሁሉ ነገር እሺ ማለት አለብን" ብሏል፡፡ ይህም ምክርን ባለመቀበል የሚመጣን አደጋ ለመከላከል የተሰጠ አስተያየት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከእነዚህ አስተያየቶች የምንረዳው መላሾቹ ከመፅሀፍቱ ውስጥ ያሉትን ገፀባህሪያት ከራሳቸው ጋር በተለያየ መንገድ በማዛመድ ምላሽ እንደሚሰጡ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአንባቢያን ምላሽ ንድፈ ሀሳብ በዚህ የክፍል ደረጃ ካሉ ተማሪዎች የሚጠበቅ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት የተሳተፉት ተማሪዎች በሰቱጡት ምላሽ ከነሱ የሚጠበቀውን አከናውነዋል ለማለት የሚያስችል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ነው፡፡ምክንያቱም እራሳቸውን በገፀባህሪያቱ ቦታ አስቀምጠው እንደነሱ ሆነው አስተያየት ለመስጠት ችለዋልና፡፡ ከህፃናት አስተያየት ሰጪዎች የሚገኙ ምላሾችን ከፋፍሎ /መድቦ/ ማየት የአስተያየት ሰጪዎቹን የትኩረት ነጥቦች በውል ለማመልከት ይረዳል፡፡ ከዚህ ሌላም በመላሾቹ አስተያየት የመጻህፍቱን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ለመጠቆም ይጠቅማል፡፡ በዚህ መሰረትም ምላሾቹን በክፍል በክፍል በመመደብ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

### 4.4.1 ታሪኩንና ገፀባህሪያቱን በድጋሚ መናገር ጭብጡን መረዳት

የተነበቡትን ታሪኮች በተቱኳረ የቡድን ውይይት ወቅት እንዲናገሩ ተጠይቀው ሁሉም የተጠየቁት የውይይቱ ተሳታፊዎች ታሪኮቹን በአጭሩ ማስቀመጥ ችለዋል፡፡ በውይይቱ ወቅት የመጀመሪያው ተናጋሪ የዘለላቸው አበይት ነጥቦች ቢኖሩም በሌሎች የውይይት ተሳታፊዎች ተሟልተዋል፣ ይሁን እንጂ አንዳንድ ተመሳሳይ ገፀባህሪያት ስሞች ሲዘበራረቁና የፆታ መለዋወጥ ሲደረግባቸው ማስተዋል ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ሽዊት የምትባል ተማሪ "ሊንቻ እና ቢንቻን" ታሪክ ስትናገር "ሁለት አይጦች ነበሩ አንዷ ሞኝ ናት ሌላዋ ብልጥ ናት" ብላለች፡፡ በዚህ ሀሳብ መሰረት ሁለቱም አይጦች ሴቶች ናቸው፡፡ በታሪኩ ውስጥ ያሉት አይጦች ግን ወንድና ሴት አይጦች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ተደጋግመው የማይጠሩ ስሞችን የመርሳት ሁኔታ ታይቷል፡፡ "ካሳ" የሚል ርዕስ ያለው የታሪክ መፅሀፍ የተነበበላቸው ተማሪዎች የካሳ የቀድሞ ስሙ ማን እንደነበር ተጠይቀው ሁሉም የውይይቱ ተሳታፊዎች ሊመልሱት አልቻሉም፡፡ ይህ ስም "አሊክስአንድሮ" ሲሆን በመፅሐፉ ውስጥ ተደጋግሞ ባለመጠራቱ ሊያስታውሱት እንዳልቻሉ ተገምቷል፡፡ በተጨማሪም ፅጌረዳ የተባለች የተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ተሳታፊ "የእንቺነሽ ተስፋ" የሚለውን መጽሐፍ ርእስ "እቴነሽ ተስፋዬ" እንቺነሽን "እቴነሽ" እያለች አስተያየት ሰጥታለች ይህም በአንባብያን ምላሽ ውስጥ ካሉት ተለዋዋጮች በአውድ ሳቢያ ሊከሰት የሚችል ነው፡፡ በሌሎቹ ታሪኮች ውስጥ ያሉትን የዋና ዋና ገፀባህሪያትን ስም ግን በአግባቡ እየጠሩ ታሪኩን በድጋሚ እንዲናገሩ የተጠየቁ የውይይቱ ተሳታፊዎች ምላሻቸውን መስጠት ችለዋል፡፡

የውይይቱ ተሳታፊዎች በሁሉም መፃሕፍት ውስጥ ሊተላለፉ የተፈለጉትን መልዕክቶች ለመናገር ችለዋል፡፡ ሃይማኖት የተባለች የተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ተሳታፊ ከ"ሊንቻ እና ቢንቻ" ታሪክ የተማረችውን ስትናገር "አንድ ያወቀ ሰው ያላወቀ ሰውን በትዕግስት መቀየር እነደሚችል ተረድቻለሁ" ብላለች፡፡ ሰሚራ ደግሞ ከዚሁ ታሪክ የተማረችውን ስታስረዳ "የሰው ምክር መስማት እንዳለብን ምክንያቱም ሁሉም ሰው መጥፎ ምክር አይመክርም" ብላለች፡፡ ሙሉጌታ ደግሞ "ቋንቋው አይከብድም ጥሩ ትምህርት ይሰጣል ሰነፍ የሆነ ሰውንም ያበረታታል" ሲል በዚሁ ታሪክ ላይ አስተያየት ሰጥቷል "ቱሲ እና ቱኪ" በተባለው መጽሐፍ ላይ እጸ ሕይወት የተባለች የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳተፊ ስትናገር "ከተረቱ የተማርኩት አይጡ የእናቱን ምክር ባለመቀበሉ ለጉዳት ሊዳረግ እንደነበር ነው እኛም የእናታችንን ምክር መቀበል አለብን . . . " ስትል አስተያየት ሰጥታለች "አሁን እኛም አንደዚህ እናታችን የምትለንን በሁሉም ነገር እሺ ማለት አለብን ይህ ተረት ደግሞ አስተማሪ ነበር" ናትናኤል የሰጠው አስተያየት ነው፡፡ "በአሰለፈች ሎሚዎች" ላይ ከተሰነዘሩት አስተያቶች መካከል እማሆይ የተናገሯቸው ለልጆች ጥሩ ነገር ነው ሰው የነገረንን ነገር ተግባራዊ ማድረግ ለልጆች ጥሩ ነው እላለሁ፡፡" የሚለው ሮምሃይ የሚባል የውይይቱ ተሳታፊ ነው፡፡ "ይህቺ ሴት መጥታ መጥታ አንስታ በደንብ አድርጋ እንደልጇ አድርጋ አሳድጋዋለች ያንን ነገር በጎ ያደረገልን ሰው ጥሩ አጋጣሚ ስናገኝ ያንን ነገር መርሳት የለብም ያንን ሰው ማስታወስ አለብን . . . " ባላ አስተያየት የሰጠችው ሃያት የተባለች የውይይቱ ተሳታፊ "ካሳ" የሚል ርዕስ ባለው መጽሐፍ ላይ ነው፡፡ በብልሀ ጠቋሪት

ላይ ከተሰጡት አስተያየቶች መካከል "ብልጥ ነው እሱ ብልጥ ባይሆን ብልጥ ከሆንን እኛም ብዙ ችግር እናልፋለን ካሆንን ግን ለምሳሌ ልንበላ እንችላለን፡፡" በማለት አስተያየት የሰጠው ዮናስ የተባለ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሳታፊ ነው፡፡

### 4.4.2 የቋንቋ አጠቃቀምን የሚመለከቱ አስተያየቶች

በቋንቋ አጠቃቀም ረገድ 2 አይነት አመለካከቶች አሉ አንደኛ ለህፃናት የሚቀርብ ስነፅሁፍ በቀላልና ግልፅ በሆነ ቋንቋ መቅረብ አለበት የሚል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የህፃናቱን ቋንቋ ብቃት ለማሳደግ የሚረዱ እንግዳ ቃላትን መጠቀም ያስፈልጋል የሚል እሳቤ ነው፡፡

ለዚህ ጥናት ከተመረጡት የህፃናት መፃህፍት ውስጥ "የአንቺን ተስፋ" የሚል ርዕስ ያለው መጽሐፍ በተዘውታሪ ንግግር ውስጥ ያልተለመዱ (ቀበልኛ) እንግዳ ቃላትን ይዟል፡፡ ይህ መፅሐፍ የተነበበላቸው ተማሪዎች በዕህፈትና በእለት ተእለት ንግግር በስፋት ተዘውታሪ ያልሆኑ እንግዳ ቃላት በመኖራቸው ምክንያት ታሪኩን ለመረዳት አለመቸገራቸውን በተተኳሪ የቡድን ውይይት ወቅት አረጋግጫለሁ፡፡ ታሪኩ ከተነበበላቸው ተማሪዎች መካከል እንግዳ ቃላቱን ከተመሳሳያቸው ጋር እንዲያዛምዱ ፈተና ከተሰጣቸው 20 ተማሪዎች ውስጥ 12ቱ ከማለፊያ ነጥብ (50 በመቶ) በታች አምጥተዋል፡፡ 15 ቃላትን በማዛመድ ተመሳሳያቸውን እንዲፈልጉ የተፈተኑ 20 ተማሪዎች ያገኙት ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ 12 የቃላት ትርጉም ፈተና ውጤት

| ተ.ቁ | ውጤት | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | ድግግም | በመቶኛ |
| 1 | ከ80% በላይ | 5 | 25 |
| 2 | ከ50 — 79% | 3 | 15 |
| 3 | ከ30 — 49% | 3 | 15 |
| 4 | ከ29% በታች | 9 | 45 |
| | ድምር | 20 | 100 |

ከዚህ ውጤት ለማየት እንደሚቻለው ከ50 በመቶ በታች ያመጡት መላሾች ቁጥር 12 (60 በመቶ) ናቸው፡፡ ከ50 በመቶ በላይ ያመጡት ደግሞ 8 መላሾች (40 በመቶ) የሚሆኑት ናቸው፡፡ ስለዚህ ምንም እንኳ አጠቃላይ የታሪኩን ሀሳብ ለመረዳት ችግር አልተፈጠረባቸውም ቢባሉም በታሪኩ ውስጥ ግን በርካታ ትርጉማቸውን በውል የማይረዷቸው ቃላት ስለመኖራቸው የተገኘው ውጤት ያመለክታል፡፡ ያም ሆኖ በውይይቱ

ላይ የተሳተፉት ተማሪዎች በሰጡት አስተያየት መፃህፍቱ በቋንቋ አጠቃቀም ረገድ ብዙ ችግር እንደሌለባቸው የሚጠቁም ነው፡፡ የአብዛኞዎቹ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋና ታሪኩ የተነበበት ቋንቋ አንድ በመሆኑም የታሪኩን አጠቃላይ ይዘት ለመረዳት አልተቸገሩም፡፡ ሙሉጌታ ቀና "በሊንቻ እና ቢንቻ" በሚል ርዕስ በተፃፈው መፅሐፍ ላይ በሰጠው አስተያየት "ቋንቋው አይከብድም ጥሩ ትምህርት ይሰጣል" ብሏል፡፡

ሌሎች ተሳታፊዎችም በውይይቱ ወቅት የሰጧቸው አስተያቶችም ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ "ቋንቋው በጣም አሪፍ ነው"፡፡ ለኛ በሚገባን ሁኔታ ተፅፏል፡፡" እየሩስ ዳኛቸው "ሊንቻና ቢንቻ" በተባለው መፅሐፍ ላይ የሰጠችው አስተያየት "ቋንቋው ለህፃናት ግልፅ በሆነ ቋንቋ የተፃፈ ነው ለኔ በጥሩ ሁኔታ ያለቀ ነው" ሰሚራ ከማል "ቱሲና ቹኪ" በሚል ርእስ በተፃፈው ታሪክ ላይ የሰጠችው አስተያየት እነዚህ ምላሾች በመፅሐፍቱ ቋንቋ አጠቃቀም ላይ የተሰነዘሩ ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ ቀበልኛና እንግዳ ቃላት የያዘው "የአንቺንሽ ተስፋ" የሚል ርዕስ ያለው መፅሐፍ ከተነበበላቸው ተማሪዎች መካከል ሙሉተስፋ የተባለችው ተማሪ "ቋንቋው ገብቶናል ታሪኩ ያሳዝናል . . ." ብላ አስተያየት ስትሰጥ በሀሳቧ ከመስማማት ውጪ የተቃወማት የውይይቱ ተሳታፊ የለም፡፡ ሁሉም አወንታዊ አስተያየቶች ሲሆኑ 'ታሪኩ ገብቶናል በቋንቋው በኩል ችግር አላጋጠመንም' የሚል መልዕክት አላቸው፡፡ ቋንቋው ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ቢያካትት ከአማርኛ ትምህርታቸው ጋር የበለጠ እንደሚቀራረብ በመግለጽ ከተሰጡት አስተያቶች ውስጥ ደግሞ የሚከተለው ይጠቀሳል፡፡ "ቋንቋው የሚገባ ነው ከአማርኛ ትምህርታችን ጋር እንዲሄድ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ቢጨመሩበት መልካም ነው " ያለችው ደግሞ ሸዊት ክፍለማርያም የተባለች አስተያየት ሰጪ ነች፡፡ከዚህ ምላሽ እንደምንረዳው በታሪኮቹ ውስጥ የቋንቋ መማሪያ የሚሆኑ ቃላትና ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንዲኖሩ የሚፈልጉ ተማሪዎች መኖራቸውን ነው፡፡

### 4.4.3 ታሪኮቹን ከሌሎች ሁነቶች ጋር ማያያዝ

በተለይ በህፃናት አንባቢያን ምላሽ አሰጣጥ ውስጥ ተመድቦ መታየት ያለበት ህፃናቱ ያነበቡትን ወይም የተነበበላቸውን ታሪክ ከሌላ ሁነት ጋር እያያዙ የሚሰጡት ምላሽ ነው፡፡

በዚህ መሰረት ከሌሎች ሁነቶች ጋር ተያይዘው የሚሰጡ ምላሾች አንዳንዴ ታሪኩን ደራሲው እውነት ለማስመሰል ያደረገውን ጥረት ያመለክታሉ በውይይቱ ወቅት "ቱሲና ቹኪ" በሚለው ታሪክ ውስጥ ያሉት አይጦች መናገራቸው ታሪኩን ‹ውሸት ያስመስለዋል› እና

‹አያስመስለውም› የሚል ክርክር ተነስቶ ነበር፡፡ በዚህ ውይይት ላይ ከቀረቡት መከራከሪያዎች አንዱ አይጦች ስለማይናገሩ ደራሲው የፃፈው የመሰለውን (የፈጠረውን) ነው የሚል ነበር፡፡ ለዚህ የተሰጠው ምላሽ "አይጦች ቋንቋ አላቸው እኛም ቤት ሆነ አያቴ ቤት አይጦች ሲመጡ እንዲሔዱ በቁጣ ሲነገራቸው የሚንሾካሾኩት ነገር አለ፤ ነገር ግን ቋንቋው ባይገባኝም የሚሳደቡ ይመስለኛል" አቤል የተባለ የነገነት ብርሃን ተማሪና የውይይቱ ተሳታፊ በሕይወቱ ያጋጠመውን ሁኔታ ከድርሰቱ ጋር በማያያዝ የሰጠው ምላሽ ነው፡፡ ምህረት አንድ የአሳይ ትምህርት ቤት ተማሪ ነች "የአሰለፈች ሎሚዎች" ላይ በሰጠችው አስተያየት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተመርምሮ ያወቀ ሰው ቫይረሱ በደሙ ውስጥ ቢገኝ ራሱ ላይ መጥፎ ነገር ማድረግ ራሱን ማጥፋት የለበትም የሚል አስተያየት ሰጥታለች በታሪኩ ውስጥ ራስን ስለማጥፋት አንዳች አልተባለም እሷ ከሰማችው ከምታስበው ጋራ አያይዛ የሌለውን ሀሳብ ወደ ውይይቱ አምጥታለች፡፡ ከዚህ ምላሽ የምንረዳው አስተያየት ሰጪዎቹ የታሪኩን እውነትነት ከሚመዝኑባቸው መስፈርቶች መካከል የራሳቸው የቀደመ እውቀት አንዱ እና ዋነኛው መሆኑን ነው፡፡ ይህ ምላሽ ለህጻናቱ የሚጻፉላቸው ታሪኮች ከእድሜአቸው እና ከልምዳቸው (ከክፍል ደረጃቸው)ጋረ የተገናዘበ እንዲሆን የሚጠቁም ነው፡፡

### 4.4.4 የአንባቢያንን ስሜት የሚያንፀባርቁ መልሶች

በአንባቢያን ምላሽ ወቅት ታሪኩን በሚያነቡበት ወይም በሚያዳምጡበት ጊዜ የተሰማቸው ስሜት ይገለፃል፡፡ ". . . እኔም ራሴ ቅድም ፍዝዝ ብዬ እያደመጥኩ ሳለሁ . . . የሆነ ነገር ይመጣል ብዬ ስጠብቅ መፅሐፉ ዝግት ሲል እና ሲቀመጥ እኔ የተጨረሰ እንኳን አልመሰለኝም . . ." ሀያት "ካሳ" የሚል ርዕስ ባለው መፅሐፍ ላይ የሰጠችው አስተያየት በዚህ አስተያየት ተማሪዋ በታሪኩ ተመስጣ (ፍዝዝ) ብላ እያዳመጠች ነበር፡፡ በተጨማሪም "ታሪኩ ለኛ ግን ልብ የሚያንጠለጥል በመሆኑ መሀል ላይ ሲቋረጥ ደስ አይለኝም" የሚል አስተያየትም ተሰጥቷል፡፡ "ታሪኩ ደስ የሚል ታሪክ ነው በሱ ተመሳሳይ ሆኖ ሌላ ታሪክ ቢወጣ አሪፍ ነው፡፡" ታሪኳ አብርሃም በ"ካሳ" ላይ የሰጠችው አስተያየት እነዚህ አስተያየቶች የተነበቡት ታሪኮቹ በመላሾች ላይ ያሳደሩትን ተፅዕኖ መላሾቹም ግለሰባዊ ስሜታቸውን ለመግለፅ የሞከሩበት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ በኩል አስተያየቱ ቢለያይም ታሪኮቹ ሳቢ እንደነበሩ በውይይቱ ወቅት ተገልጿል፡፡

በታሪኮቹ ላይ ውይይት ያደረጉ አብዛኞዎቹ መላሾች በታሪኮቹም ሆነ በገፀባህሪያቱ ላይ በራሳቸው ግምገማ መሰረት ፍርድ ሰጥተዋል፡፡ ሁሉም በውይይቶቹ የተሳተፉ መላሾች ለታሪኮቹ አወንታዊ አስተያየት የሰጡ ሲሆን በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ግን ያላቸውን ቅሬታ ገልፀዋል፡፡

ከነዚህ ውስጥ አንዱ ታሪኮቹ እውነት አይመስሉም የሚል ነው፡፡ በተለይም በዘመናዊ ፋንታሲ መልክ ከቀረቡት መካከል "ቱሲ እና ቹኪ" የሚለው ታሪክ እውነት አይመስልም የሚል ክርክር አስነስቷል፡፡ "ታሪኩ እውነት አይመስልም፡፡ እውነት አይመስልም ያልኩበት ምክንያት አይጦች አያወሩም" ናትናኤል የተባለ የውይይቱ ተሳታፊ የሰጠው አስተያየት ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ታሪኩን በተወሰነ መልኩ ተማሪዎቹ እውነት እንዳይመስላቸው የሚያደርጉ ነጥቦች መኖራቸውን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሌሎች ተማሪዎች ደግሞ አይጦች የራሳቸው ቋንቋ አላቸው፡፡ ይህንን ቋንቋቸውን የሚያውቁ ሰዎች ይኖራሉ፤ ስለዚህ ታሪኩን እውነት በማስመሰል ፅፎታል፡፡ በማለት መከራከሪያቸውን አቅርበዋል፡፡ ይህም ገፀባህሪያቱን በአግባቡ የሳለና አንባቢያኑን ያወቀ ደራሲ በዘመናዊ ፋንታሲ ድርሰት ወቅት ያወጣውን ህግ እስከጠበቀ ድረስ አንባቢያኑ ራሳቸው ትክክል ነው በሚል ይከራከሩለታል በሚል በጥናቱ ምዕራፍ ሁለት የተጠቀሰውን ንድፈ ሀሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡ በሌላ በኩል ክርክሩ መነሳቱ በዚሁ ምዕራፍ ላይ ታሪኩ እውነት አይመስልም በሚል በመጠይቅ ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠውን ምላሽ የሚያጠናክር ሀሳብም ይመስላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ታሪኮቹ ከመላሾቹ ያነሰ እድሜ ላላቸው ህፃናት ሊከብዱ ይችላሉ፡፡ በማለት አስተያየት የሰጡ ተማሪዎች አሉ "1ኛ እና 2ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ሊያስቋቸው አይችሉም፡፡ እዚህ ውስጥ ለእነሱ የሚከብዱ ቃላት ስላሉ ረጃጅም ስለሆኑ ሊከብዳቸው ይችላል ስለዚህ ታሪኮቹ ላይ እድሜ ሊፃፍባቸው ይገባል፡፡" በማለት አስተያየት የሰጠችው ቤዛ በፍቃዱ የተባለች ተማሪ ነች፡፡

በታሪኮቹ አጨራረስ ላይ ቅሬታ ተደጋግሞ ተነስቷል ቤዛ የተባለች ተማሪ "በተረቱ አጨራረስ ላይ ተቃውሞ አለኝ፡፡ በመጨረሻ አካባቢ ልጅቷ ተመርምራ ውጤቷን ሳላወቀችም እቤት ከሔደች በኋላ ተረቱ ይቋረጣል ተመርምራ ውጤቷን አውቃ ከእነርሱ ጋር አብራ ብትኖር ጥሩ ነበር፡፡" በማለት "በአሰለፈች ሎሚዎች" ላይ አስተያየት ሰጥታለች "ቱሲ እና ቹኪ" የሚል ርዕስ ባለው መፅሐፍ ላይ አቤል መጨረሻ ላይ እናትና ልጅ አይጦች

ወደጉድጓዳቸው ከገቡ በኋላ እናትየዋ አይጥ ልጇን ከአሁን በኋላ ምክሬን ስማ ብላ እሱም ቃል ገብቶ በሰላም እየኖሩ ቢያልቅ ደስ ይለኝ ነበር የሚል አስተያየት ሰጥቷል፡፡

"የታሪኩ አጨራረስ አላማረኝም ቤተሰቦቹ አያቱ አላዩትም የሚለው አልተገለፀልኝም መጨረሻው ማማር አለበት፡፡" ያለችው ደግሞ ታሪኳ የተባለችው ተማሪ "ካሳ" የሚል ርዕስ ባለው መፅሐፍ ላይ በሰጠችው አስተያየት ነው፡፡

". . . መፅሐፉ ዝግት ሲል እና ሲቀመጥ እኔ የተጨረሰም እንኳ አልመሰለኝም እና ይህንን የፃፈው ደራሲ ይህንን ነገር አስተካክሎ ለህትመት ቢያበቃው በጣም ጥሩ ነው፡፡" ሃያት "ካሳ" በሚለው መፅሐፍ ላይ የሰነዘረችው አስተያት፤ "አጨራረሱን ቢያሳምር ጥሩ ነበር" አብይሰው "በአሰለፈች ሎሚዎች" ላይ፤ በአጠቃላይ በታሪኮቹ እውነተኛነት፣ በአጨራረሱና እድሜ ባለመፃፉ ላይ አሉታዊ በሆነ መልኩ መስተካከል አለበት የሚል አስተያየት በውይይቱ ተሳታፊዎች ተሰጥቷል፡፡

በታሪኮቹ አጠቃላይ ይዘትና በገፀባህሪያቱ ላይም የሚከተሉት አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡ ታሪኩ ረጅምም አጭርም አይደለም ቋንቋውም ጥሩ ነው ደግሞም ደስ የሚል ታሪክ ነው ያለችው ብሩክታይት "በብልሁ ጠቋሪት" ላይ በሰጠችው አስተያየት ነው፡፡ "የአሰለፈች ገፀባህሪ በጣም የሚያሳዝን ነው በጣም ወድጄዋለሁ" ያለው ደግሞ "የአሰለፈች ሎሚዎች" የሚለው ታሪክ የተነበበለትና በውይይቱ ላይ የተሳተፈው አብይ ሰው ነው "ልጁ እንደ ልጅ ነው የተጫወተው ልጅ የሚያደርገውን ነው የሚያደርገው የልጅነት ገፀባህሪን ስለያዘ እናትየው ደግሞ ያልተማሩና ትልቅ ነገር ስለሆነች የድሮ ነገር ስለሆነች በትንሹ ይሰለቻታል"፡፡ በማለት የገፀባህሪያቱን አሣሣል አስመልክቶ አስተያየት የሰጠው ናትናኤል በ"ቱሲ እና ቼኪ" ላይ ነው፡፡ "ካሳ" በሚለው መፅሐፍ ላይ ደግሞ ታሪኩ በጣም ለልጆች እንደሚገባ ሆኖ ነው የተፃፈው ስሜታችንን እንደሚማርክ ሆኖ ነው የተፃፈው ሚሚሉት በገፀባህሪያቱና በመፃሕፍቶቹ ይዘት ላይ ከተሰጡ አስተያየቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

# 5. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች

## 5.1 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት ውስጥ የተገኙት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በተመረጠው እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ህፃናት አሳዛኝና አስገራሚ እንዲሁም እንስሳት ወይም ሰው ገፀባህሪያት ያሉባቸውን ታሪኮች ወደው ያነቧቸዋል ወይም ያዳምጧቸዋል፡፡

ከተነበቡላቸው ታሪኮች አንዳንዶቹ እውነት የመምሰል ችግር እንዳለባቸው ተማሪዎቹ በመልሳቸው አስታውቀዋል፡፡ ይህ ደግሞ ዘመናዊ ፋንታሲ ባህሪ ባላቸው መፅሐፍት ላይ ጎልቶ እንደሚታየው በዚሁ ጥናት ሂሳዊ ትንተና በተደረገበት ምዕራፍም ተገልጧል፡፡ ይህም ደራሲያኑ አንባቢያኑን በምናብ ወደ ሌላ አለም በመውሰድ በእውነተኛ አለም የማይሆን ነገር እየሆነ እንዳለ አስመስሎ የማቅረብ ችግር እንዳለባቸው ይጠቁማል፡፡ በዚህም በትንተናው ላይ ደራሲዎቹ ዕሁፎቹን ምናባዊ የማድረግ ችግር አለባቸው ተብሎ ከተገለጸው ጋር የሚቀራረብ ውጤት ተገኝቷል፡፡ በዚህ አይነት አፃፃፍ ደራሲያኑ ለታሪኩ ሲሉ ላወጡት ደንብ ያለመገዛት ችግርም ታይቶባቸዋል፡፡

ከመላሾች 85 (47.2 በመቶ) የሚሆኑት በራሳቸውና በወላጆቻቸው ምርጫ፣ 78 (43.4 በመቶ) የሚሆኑት ደግሞ በራሳቸው ምርጫ መፃሕፍት እንደሚገዙላቸው አመልክተዋል፡፡ በዚህም መሠረት ከጠቅላላ መላሾቹ 163 (90.6 በመቶ) በመፃሕፍት ምርጫ ይሳተፋሉ ይህም የሚፈልጉት አይነት መጻህፍት እንዲኖራቸው እድል የሚሰጥ ነው፡፡

ምንም እንኳን በህፃናት መፃህፍት አንባቢያን የራሳቸውን ማጠቃለያ እንዲሰጡ ደራሲያን ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለባቸው ቢባልም በታሪኮቹ አጨራረስ ላይ አሉታዊ አስተያየቶች ተሠጥተዋል፡፡ በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተሳተፉ ህፃናት የመፃህፍቱ አጨራረስ እንዳላስደሰታቸው ገልፀዋል፡፡

ህፃናቱም በሰጡት ምላሽ በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ የህፃናት መፃህፍትን አንብበዋል፡፡ ከሚወዷቸው መፃህፍት ውስጥ በኢትዮጵያውያን ደራሲዎች በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ የሀገር ውስጥ ድርሰቶችን በአንደኛ ደረጃ መርጠዋል፡፡

በውይይቱ ላይ በመፃህፍቱ ቋንቋ አጠቃቀም ዙሪያ ለተነሱ ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ ቋንቋው የሚገባና ግልፅ ነው ቢሉም ለ20 ተማሪዎች ቃላትን ከተመሳሳያቸው ጋር እንዲያዛምዱ በተሰጣቸው ፈተና ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ያመጡት ውጤት ከማለፊያ ነጥብ በታች ነው፡፡ይህም በሂሳዊ ትንተናው ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት አሉባቸው በሚል የተጠቀሰውን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡

በቡድን ውይይቱ ላይ የታሪኮቹን ጭብጦች አስመልክተው አስተያየት የሰነዘሩት የውይይት ተሳታፊዎች በሙሉ የሰጡት ምላሽ ደራሲያኑ ማስተላለፍ የፈለጓቸውን መልእክቶች በትክክል መገንዘባቸውን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ሆኖም በሂሳዊ ትንተናው በመጻህፍቱ ውስጥ ህጻናቱን አንድ አንድ ነጥቦች ከመልካም ስነምግባር ሊያሥወጧቸው የሚችሉ አሉ ተብለው የተጠቀሱት ነጥቦች በውይይቱ ወቅት ህፃናቱ አልጠቀሷቸውም፡፡

ጥብቅ ትስስር ያለው ፐሎት የሌላቸው ገፀባህሪያቱ በአግባቡ ያልተገለፁና መቼታቸው በውል ያልተብራራ እንዲሁም መልካም ያልሆኑ ስነምግባራዊ መልዕክት ያሏቸው መፅሐፍት መኖራቸው በትንተናው ላይ ወቅት ተገልጿል፡፡ በሌላ በኩል ከአንድ መፅሐፍ በስተቀር የአምስቱ መፃሕፍት ቋንቋ (የቃላት አጠቃቀም ቀላልና የሚገባ ነው፡፡ ሁሉም ታሪኮች ከ80 በመቶ በላይ በሆኑት መረጃ ሰጪዎች ተወደዋል፡፡

## 5.2 የመፍትሄ ሃሳቦች

ከላይ በተሰጠው ማጠቃለያ መሠረት በህፃናት ሥነፅሑፍ ላይ የሚታዩትን ችግሮች ለማስወገድ የሚጠቅሙ የመፍትሄ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ተሰጥተዋል፡፡ ህጻናቱ በዘመናዊ ፋንታሲም ሆነ በእውነታዊ ልብወለድ የተፃፉ ታሪኮችን ማንበብ ወይም ማድመጥ ያስደስታቸዋል፡፡ ከልምዳቸው እና ከዕድሜያቸው ጋር የሚሄዱ፣ በማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ የሚያሳዝኑ፣ የሚያስገርሙ ወይም የሚያስቁ ታሪኮች ቢቀርቡላቸው የማንበብ ፍላጎታቸው ከፍተኛ መሆኑ ከምላሻቸው መረዳት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ደራሲያን በስፋት በዚህ መልክ የተደረሱ መፃህፍቱን ማቅረብና ማስተዋወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ታሪኮቹ እውነት አይመስሉም በሚል የተሰጠውን አስተያየት መቅረፍ ይቻል ዘንድ በተለይም የዘመናዊ ፋንታሲ አፃፃፍ የሚጠይቀውን የገፀባሪ አሳሳልና የመቼት አገላለፅ ቢጠቀሙ መልካም ይሆናል፡፡

በተማሪዎቹ ምላሽ መሰረት በአማርኛ ቋንቋ የሚፃፉ የህፃናት ልቦለዶች በአንፃራዊነት በብዛት ይነበባሉ፡፡ በመሆኑም አዳዲስ ሀሳብ ያላቸው ደራሲያን በዚህ መልክ ቢሰማሩ የህፃናቱን ፍላጎት በስፋት ማዳረስ ይችላሉ፡፡

በመፃህፍቱ ላይ የእድሜና የክፍል ደረጃ ቢገለፅ ህፃናቱ መርጠው ለማንበብ ወላጆቻቸውም መርጠው ለመግዛት እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡

የሚፃፉት የህፃናት መፃህፍት ቋንቋና ቃላት ከታሪኮቹና ገፀባህሪያቱ ጋር መገናዘብ ይኖርባቸዋል ከሚለው በተጨማሪ ከአንባቢያኑና ከቋንቋው ደረጃቸው አንፃር መመዘን አስፈላጊ ነው፡፡

በህፃናት መፃህፍት ጥሩ ወይም መጥፎ ብለው የሚፈርጁት ህፃናቱ በመሆናቸው በመፅሐፍ ግገር ወቅት ፍላጎታቸውን መጠየቅ ባላቸው መረጃ መሰረት ለመምረጥ ስለሚረዳቸው በወላጆች ይህ ጉዳይ ሊጤን ይገባዋል አንዳንዴ የወላጆች ምርጫ ብቻ ትክክል ላይሆን ስለሚችል፡፡

በትብብር  የህጻናት መጻህፍት የሚያሳትሙ የንግድ ፣የመንግስትና  የዕርዳታ ድርጅቶች የሚታተሙት መጻህፍት የአንባቢያኑን ዕድሜ እና የክፍል ደረጃ እንዲጻፍባቻ ቢያደርጉ ይመረጣል፡፡

# የተጠቀሱ ምንጮች

መስሉ መዝገቡ፤ "ከ1978 ዓ.ም እስከ 1995 ዓ.ም ታትመው የወጡ የልጆች መፃሕፍት መዘርዝርና አጫጭር መግለጫዎች።" የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የጥናት ጽሑፍ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1996 ዓ.ም። (ያልታተመ)

መስፍን መሰለ ፤ "የልጆች ስነፅሑፍ በኢትዮጵያ።" የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የጥናት ጽሑፍ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1978 ዓ.ም። (ያልታተመ)

ሚካኤል ዳንኤል ፤ ካሳ። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1996 ዓ.ም።

ሺበሺ ለማ ፤ ሊንቻ እና ቢንቻ። አዲስ አበባ፤ አርትስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1995 ዓ.ም።

በስርአተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢኒስቲትዩት የቋንቋዎች ትምህርት ሥርአተ ትምህርት ዝግጅት ቡድን፤ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርቶች ከ5ኛ - 8ኛ ክፍል ተሻሽሎ የተዘጋጀ። አዲስ አበባ፤ በት.መ.ማ.ማ.ድ ታተመ፣ 1995 ዓ.ም።

ተሰማ ሀብተሚካኤል፤ ከሳቴ ብርሃን ተሰማ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1951።

ተስፋዬ ገብረ ማርያም፤ ቷሲና ቹኪ። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች፣ 1997 ዓ.ም።

ታቦር ገብረ መድህን፤ የአስለፈች ሎሚዎች። አዲስ አበባ፤ አርትስቲክ ማተሚያ ድርጅት፣ 1995 ዓ.ም።

አለም እሸቱ፤ ብልሁ ጠቋሪት። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች፣ 2001 ዓ.ም።

አብርሃም አሰፋ፤ የአንቺነሽ ተስፋ። ለንደን፤ ማክሚላን ኢዱኬሽን ሊሚትድ፣ 1997 ዓ.ም።

አብይ በላቸው፤ "በተስፋዬ ሳህሉ ተከታታይ የተረት መፃሕፍት ይዘትና የቋንቋ ትንተና።" የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የጥናት ጽሑፍ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1997 ዓ.ም። (ያልታተመ)

ከብካብ አስፋው፤ "ሂዩመር፣ አድቬንቸርና ፋንታዚ በተመረጡ የሕፃናት ስነፅሁፍ ደራስያን ሥራዎች ውስጥ።" የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የጥናት ጽሑፍ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1996 ዓ.ም። (ያልታተመ)

ኪዳነወልድ ክፊፍሌ፤ <u>መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ</u>። አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948።

ዘሪሁን አስፋው፤ <u>የስነ ፅሑፍ መሰረታውያን</u>። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1992 ዓ.ም።

__________፤ <u>የአጭር ልቦለድ የኪነጥበብ ጥቂት ገጽታዎች እና ሌሎችም 11 ስነጽሑፋዊ መጣጥፎች</u>። አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1986 ዓ.ም። (ያልታተመ)

የህፃናት፣ ወጣቶችና ቤተሰብ ደህንነት ድርጅት፤ <u>የህፃናት መብት ኮንቬንሽን</u>። አዲስ አበባ፤ ስዊድን ህጻናት አድን ድርጅት፣ 1997 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ <u>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ</u>። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1992 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ <u>የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት</u> ። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1987 ዓ.ም።

ደስታ ተክለወልድ፤ <u>ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት</u>። አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም።

ዳንኤል ነጋሽ፤ "የልጆች ልቦለድ አጻጻፍ በታተሙ የሁለት ደራስያን የልጆች ልቦለዶች ምሳሌነት።" የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የጥናት ጽሑፍ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1996 ዓ.ም። (ያልታተመ)

ፊቃደ ሞላ፤ "በቅዳሜ የልጆች ሬድዮ ፕሮግራም የሚተላለፉ ተረቶች ቅርጽና ይዘት ትንተና።" የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የጥናት ጽሑፍ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1991 ዓ.ም። (ያልታተመ)

ፈቃደ ተፈራ፤ "የልጆች ስነጽሁፍ ይዘትና ቋንቋ።" የአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የጥናት ጽሑፍ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1984 ዓ.ም።(ያልታተመ)

Alstetter, Mobel F. "Enjoying Great stories and Classics." Literateure with Children. Ed. Margaret Rasmussen. Papers Presented to Association for Childhood Education on International 1961-62 Membership Service Bulletin No 3 –A. Washington: Childhood Education International, 1961. PP 6-10.

Arbuthnot, May Hill. Children and Book . 3rd ed. Atlanta : Scott Foresman and Company, 1964.

Benton, Micheal. " Readers, Texts, Context." Understanding Children's Literature. Key Essays From the School Edition of the International Companion Encyclopedia of Childeren's Literature. Ed. Peter Hunt. London and New York: Taylor and Francis Group, 2005.

Brown ,Carol, and Care M. Tomlinson. Essentials of children's Literature. Boston: Allyn and Bacon, 1999.

Dereje Melaku. "The State of Children's Literature in Amaharic." Addis Ababa University Department of Foreign Languages and Literature. MA Thesis, 1994. (unpublished)

Ehrlich Bettina "Story and Picture in Children's Book.'' Horn Book Reflections on children's Book and Reading. Ed. Elinor Whiteney. Field Boston: The Horn Book Inc, 1969. PP86-92.

Grenby, M.O. Children's Literature. Edinburgh: Edinburgh university press, 2003.

Horning, Kathleen T. From Cover to Cover. New York: Harper collins publishers,1997.

Lensie Bekele. "Children's Literature Its Impact on the Mind of the child Reader." Addis Ababa University Department of Foreign Languages and Literature. MA Thesis, 2005.(Unpublished)

Misrak Tenna. "A Critical Analysis of Children's Story Books of Alem Eshetu and Tesfaye Gebre Mariam." Department of Foreign Languages and Literature Addis Ababa University. MA Thesis, 2009. (Unpublished)

Norton, Donna E. Through the Eyes of a Child. New Jersey: Prentice – Hall Ice, 1999.

Papalia, Diane E. and Sally Wendkes olds. A Child's World. 5th ed. New York : York Graphic Servies.Ice, 1990.

Perumbulavil Vilasini. "Children's Books and Reading in a Plural Society – Singapore." One Ocean Touching. Paper From the Pacific Rim Conference on Children's Literature Ed. Sheila A. Egoff. London: The Scare Crow Press Inc,1979. PP 60-78.

Rahmetu Beyene. "Social Issues in Selected Amharic Children's Plays A Critical Analysis." Addis Ababa University Department of Foreign Languages and Literature. MA Thesis, 2002. (Unpublished)

Sander, Jacquelyn. "Psychological Significance of Children's Literature." A Critical Approach to Children's Literature. Ed. Sarar Innis Fenwick. Chicago & London: The University of Chicago press, 1967. PP15-22.

Sutherland, zena. Children and Books. Chicago: Wesley Educational publisher, 1967.

Tooze, Ruth. "Story Telling." Literature with Children. Ed. Margaret Rasmussen. Papers Presented to Association for Childhood Education on International 1961-62 Membership Service Bulletin No 3 –A. Washington Childhood Education International, 1961. PP. 37-47.

ኅባሪ 1 መጠይቅ

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር
# የስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

በ5ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚመለስ መጠይቅ

ይህ መጠይቅ የህፃናት ስነፅሁፍ ሂሳዊ ትንተና እና የህፃናት አንባቢዎች አስተያየት በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በሚሰራ የመመረቂያ ጥናት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ነው።

በተቻለ መጠን በጥንቃቄ መልሱን እንድትሰጡ አደራ እላለሁ።

ስለትብብራችሁም አስቀድሜ አመሰግናለሁ።

ማሳሰቢያ፡-

1. ስምና የክፍል ቁጥር መፃፍ አያስፈልግም
2. መልሱን በጋራ (እየተወያዩ) መመለስ የተከለከለ ነው።

ክፍል አንድ

I. አጠቃላይ መረጃ

1. የትምህርት ቤቱ ስም ______________
2. ፆታ ______________
3. እድሜ ______________
4. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ______________

ክፍል ሁለት

II. ትክክለኛውን መልስ የያዘውን አክብብ/ቢ/

1. የተነበበልህ/ሽ ታሪክ ስለምን የሚናገር ነው

   ሀ. ስለ እንስሳ ለ. ስለ ሰው ሐ. ስለ ቁሳቁስ መ. ስለአምላክ

2. ታሪኩ ምን አይነት ስሜት አሳደረብህ/ሽ

   ሀ. አሳቀኝ ለ. አሳዘነኝ ሐ. አስገረመኝ መ. አናደደኝ

3. የተነበበልህን/ሽን ታሪክ ምንያህል ወደድከው/ሽው/

   ሀ. ወድጄዋለሁ

   ለ. እጅግ በጣም ወድጄዋለሁ

   ሐ. አልወደድኩትም

   መ. እጅግ በጣም አልወደድኩትም

4. የተነበበውን ታሪክ ካልወደድከው/ሽው/ ለምን

   ሀ. ታሪኩ እውነት ስለማይመስለኝ

   ለ. ቋንቋው ስላልገባኝ

   ሐ. ባለታሪኮቹን ስላልወደድኳቸው

   መ. ሌላ ምክንያት ካለ ይገለፅ ______________________________.

   ______________________________________________

5. የተነበበው ታሪክ

   ሀ. የሚገባ ነው ሐ. በጣም የሚገባ ነው

   ለ. በመጠኑ የሚገባ ነው መ. ጭራሽ የማይገባ ነው

6. ተመሳሳይ ታሪክ መስማት ትፈልጋለህ/ሽ/

ሀ. እጅግ በጣም እፈልጋለሁ

ለ. በጣም እፈልጋለሁ

ሐ. በመጠኑ እፈልጋለሁ

መ. በጭፁም አልፈልግም

7. የተነበበው ታሪክ

ሀ. በጣም ረጅም ነው

ለ. ረጅም ነው

ሐ. መካከለኛ

መ. አጭር ነው

ሠ. በጣም አጭር

8. ሌላ የተረት መፅሐፍ አንብበህ/ሽ/ ታውቃለህ/ሽ/

ሀ. አውቃለሁ ለ. አላውቅም

9. ምን አይነት ታሪክ ማንበብ ትወዳለህ/ሽ/

ሀ. የእንስሳት የሚያስቅ ታሪክ ሐ. የሰው የሚያስቅ ታሪክ

ለ. የእንስሳት የሚያሳዝን ታሪክ መ. የሰው የሚያሳዝን ታሪክ

ሠ.ሁሉንም

10. የተረት መፃህፍት ሲገዙልህ/ሽ/ በማን ምርጫ ነው

ሀ. በራሴ ምርጫ

ለ. በራሴና በወላጆቼ ምርጫ

ሐ. በወላጆቼ ምርጫ

መ. በሚገዙልኝ ሰዎች ምርጫ

ክፍል ሦስት

III. ትክክለኛውን መልስ ፃፉ

1. ያነበብካቸውን/ሻቸውን/ የተረት መፃህፍት ርዕስ ዘርዝሩ

ሀ. ______________________________

ለ. ______________________________

ሐ. ______________________________

መ. ______________________________

ሠ. ______________________________

2. ሁለት በጣም የምትወዳቸውን/ጃቸውን/ የተረት መፃህፍት ርዕስ ፃፍ/ፊ/

ሀ. ______________________

ለ. ______________________

ክፍል 2 ለተማሪዎች፡ የቀረበ፡ ቃላት
የማዛመጃ፡ 4+5

ከምንባቡ ውስጥ ተውጣጥተው

በ"ሀ" ክፍል ለተዘረዘሩት ቃላት በ"ለ" ክፍል ካሉት ተመሳሳይ ፈልጉላቸው

(የአንቺነሽ ተስፋ)

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ችምግ ________ | ሀ. የምደክመው |
| 2. ተጠናወታት ________ | ለ. የእርሻ መሣሪያ |
| 3. ለበቅ ________ | ሐ. ርኩስ መንፈስ |
| 4. አነጎተ ________ | መ. የምትታለብ ላም |
| 5. ጋኔን ________ | ሠ. እፍኝ |
| 6. የምባክን ________ | ረ. ሰይጣን |
| 7. ጋሬጣ ________ | ሰ. ልምጭ፣ አርጩሜ |
| 8. አጎዛ ________ | ሸ. ጋገረ |
| 9. ማንከራተት ________ | ቀ. ተከሰው /አቃጥለው |
| 10. ጥገት ________ | በ. ተጨነቀ |
| 11. ወገል ________ | ተ. ያባት /ሰፈረባት |
| 12. አቃተተ ________ | ቸ. ለስፌት የሚሆን ሳር |
| 13. አክርማ ________ | ነ. እንቅፋት |
| 14. ቸርክሰው ________ | ኘ. የበግ ቆዳ |
| 15. ምንሚናው ________ | ኃ. ወደ ግራና ቀኝ ማጣፋት |

አባሪ፡ 3

# አሳይ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ የሕዝብ ት/ቤት
# ASSAI PRIMARY & SECONDARY PUBLIC SCHOOL

ቁጥር ክ/282/1-4/03
Ref.No.
ቀን 6/6/2003
Date

*ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ*
*የኢትዮጵያ ሥነ ፅሑፍና ፎክለር ክፍለ ትምህርት*
*__አዲስ አበባ__*

ጉዳዩ :- __መረጃ ስለመስጠት ፤__

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ሥነ ፅሑፍና ፎክለር ክፍለ ትምህርት የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር ተማሪ የሆነው አቶ አለምሰገድ እሸቱ በአሳይ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ የሕዝብ ትምህርት ቤት በመገኘት ስለ ሕፃናት ሥነ ፅሑፍ ሂሳዊ ትንተና እና የህፃናት አንባቢዎች አስተያየት በሚል ርዕስ ለዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሑፍ አስፈላጊውን መረጃ የሰበሰቡ መሆኑን በትህትና እንጠይቃለን።

*ከማክበር ሰላምታ ጋር*

ገበያው ፍቃዱ ብርሌ
ም/ር/መምህር

011-5518807 / 011-5151245 Fax 011-552 9223 ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 02/03 አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
3146 E-mail assai@ethionet.et www.assai.edu.et Kirkos Kifleketema, Kebele 02/03 Addis Ababa - Ethiopia

ቁጥር ነ/ብ/11/205/03..
ቀን 06/10/2003 ዓ.ም

...ዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ
...ት ብርሃን የመጀመሪያ ደረጃ የህዝብ ት/ቤት
Government of Addis Ababa Education Bureau
Kirkos ...
... Primary Public School

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

<u>አዲስ አበባ፤</u>

ጉዳዩ፡- <u>ስለአቶ አለምሠገድ እሸቱ መረጃ አሰባሰብ ይመለከታል።</u>

ከላይ በርዕሡ የተጠቀሱት አቶ አለምሠገድ እሸቱ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሁተለኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት " *የሕፃናት ስነ-ጽሁፍ ሐሣዊ ትንተና እና የሕፃናት አንባቢዎች አስተያየት*" በሚለ ርዕስ ለሚሰሩት ጥናታዊ ፁሁፍ ት/ቤታችን በመምጣት ከአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች ጋር በመሆን ለጥናቱ የሚሆን መረጃ ለመሰብሰብ በ10/08/03ዓ.ም እና 11/08/2003 ዓ.ም በጠየቁት መሠረት የ5ኛ A እና B ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ ክፍል ጊዜ ለሁለት ቀን በ120 ደቂቃ ለጥናቱ የሚሆን መረጃ መሰብሰባቸውን እናሣውቃለን።

"ከሠላምታ ጋር"

መክብብ መንጄ ሶሪ
Mekbib Menje Sori

/ሂይ

'ER AMBA PRIMARY & SECONDARY
Kg-10 PUBLIC SCHOOL
Address
Tel.6 26 03 99 / 626 22 81
P.O.Box 90046
Addis Ababa, Ethiopia

አየር አምባ 1ኛና 2ኛ ደረጃ
የሕዝብ ት/ቤት
አድራሻ
ስልክ 626 03 99/626 22 81
ፖ.ሣ.ቁ. 90046
አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ

ቁጥር አ፩/አ/002/1477/89/03
Ref.No
ቀን 9/10/2003
Date

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ሥነ ፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- መረጃን ስለመስጠት

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ተማሪ የሆኑት ዓለምሰገድ እሸቱ የሁለተኛ ድግሪ መመረቂያ ፅሑፋቸውን " የህፃናት ሥነ ፅሑፍ ሂሳዊ ትንተና እና የህፃናት አንባቢዎች አስተያየት" በሚል ርዕስ ለመስራት በአየር አምባ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ የህዝብ ትምህርት በመገኘት መረጃዎችን በመሰብሰብ ጥናታዊ ፅሑፋቸውን ስለመስራታቸው እያረጋገጥን ስራቸው ውጤታማና የተሳካ እንዲሆንላቸው በመመኘት ይህንን መረጃ የሰጠናቸው መሆናችንን እንገልፃለን።

ከሰላምታ ጋር
ኤሊያስ ገ/ማርያም ካህሳይ
ELIAS G/MARIAM KAHSAY
ርዕስ መምህር
DIRECTOR

ቁጥር ቦ/ህ/ጊ/478/87/8

ቀን 10/10/03

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የኢትዮጵያ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- መረጃ ስለ መስጠት

በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የኢትዮጵያ ሥነፅሁፍ ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር ተማሪ የሆኑት አቶ አለምሰገድ እሸቱ "የህፃናት ሥነፅሁፍ ሂሳዊ ትንተና እና የህፃናት አንባቢያን አስተያየት" በሚል ርዕስ ለሚሰሩት የዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ፅሁፍ በትምህርት ቤታችን ከ5ኛ ክፍል ተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ በጠየቁት መሠረት ተፈቅዶላቸው ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም መረጃውን መሰብሰባቸውን እንገልፃለን፡፡

Addis Ababa City Government Education Bureau Bole Community Primary and Secondary School

ከሠላምታ ጋር

ፍሬወይኒ ታደሰ ኪዳኔ
የመምህራንና የት/ቤት አመራር
ልማት ም/ር/መምህርት

ይህ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ የእኔ ወጥ ሥራ ነው፡፡ ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርስቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም፡፡ ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴንም አረጋግጣለሁ፡፡

አለምሰገድ፡ አሸቱ

ስም

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ሰኔ 2003 ዓ.ም